41

ከሞት በኋላ

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ በዝርዝር የምንነጋገረው መጽሐፍ ቅዱስ ስለ መታን ትንሣኤ ያሰፈረልንን ትምህርቶች በማስመልከት ይሆናል። ትምህርቱንም በቀላሉ ለመከታተል እንችል ዘንድ በቅድሚያ መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ሰው ተፈጥሮ ዘሚናገራቸው ነጥቦች ላይ እናተኩራለን።

የሰው ልጅ ሦስቱ ባሕርያት

ዘሌኖ ተሰሎንቄ 5:2 ላይ እንደሰፈረው ጳውሎስ በዚያ ስለሚገኙት ክርስቲያኖች የሚከተለውን ጸሎት አድርሶ ነበር:- *«የሰላምም ለምላክ ራሱ ሁሉተንተናችሁን ይቀድስ፤ መንፈሳችሁም፥ ሥጋችሁም፥ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ዘመጣ ጊዜ ያለ ነቀፋ ፈጽመው ይጠበቁ።»*

በዚህ ጸሎት መግቢያ ላይ በቅድሚያ የሰፈሩት ቃላት፥ «አምላክ ራሱ ሁለንተናችሁን ይቀድስ» የሚሉት ሲሆኑ፥ «ሁለንተና» የሚለው ቃል ጠቀሜታ ላይ የዋለው ደግሞ የአንድን ሰው የተፈጥሮ ባሕርያት ወይም ስብዕና ለማመልከት ለመሆኑ ግልጽ ነው። ጳውሎስ ስለ እነዚህ ሰብዓዊ ባሕርያት በመቀጠል ሲተነትን «መንፈስ፥ ነፍስና ሥጋ» ስለ መሆናቸው በግሪግ መልኩ አስቀምጦታል።

እንደገናም በዕብራውያን 4:12 ላይ የሚከተለው ሠፍሮ እናነኛለን። *«የእግዚአብሔር ቃል ሕያው ነውና፥ የሚሠራም፥ ሁለትም አፍ ካለው ሰይፍ ሁሉ ይልቅ የተሳለ ነው፥ ነፍስንና መንፈስንም ጅማትንና ቅልጥምንም እስኪለይ ድረስ ይወጋል።»* እንግዲህ በዚህ ጥቅስ ውስጥም ቢሆን የምንመለከተው የሰው ተፈጥሮ ሦስት ራሳቸውን የቻሉ ክፍሎች እንዳሉት ነው። የእነዚህ የሦስቱ ጎብረት ነው አንድን ሰው በተፈጥሮው ሰው ሊያሰኘው የሚችለው።

በመቀጠል ደግሞ የምንመለከተው ሰው በዚህ ዓይነት መልኩ እንዴት ሊፈጠር ቻለ? የሚለውን ጥያቄ ነው። በዘፍጥረት 1:26 ላይ የሚከተለውን እናነባለን:- *«እግዚአብሔርም አለ፥ ሰውን በመልካችን እንደ ምሳሌአችን እንፍጠር ...»* ከጥቅሱ እንደምንረዳው የእግዚአብሔርንና የሰውን ግንኙነት ደረጃ ለመግለጽ ጠቀሜታ ላይ የዋሉት «በመልካችን» እና «እንደ ምሳሌአችን» የሚሉት ሁለት ቃላት ናቸው። መልክ ማለት ደግሞ ውጪያዊ ገጽታ ማለት እንደመሆኑ፥ እንግዲህ የሰው አካላዊ ቅርጽ የሚመሳሰለው ከእንስሳት ጋር ሳይሆን ከፈጣሪው ከእግዚአብሔር ጋር ነው ማለት ነው። ወይም በሌላ አነጋገር ሰው የእግዚአብሔር ምስል ወይም ፎቶግራፍ ነው ማለት ይቻላል። «ምሳሌ» የሚለው ቃል ደግሞ የሚያንጸባርቀው ሰው በውስጣዊው ባሕሪው የአምላኩን ጠባያት የወረሰ መሆኑን ነው። ስለዚህም ነው የሰው ልጅ ወጥ የሆነ አንድ ስብዕና ቢኖረውም እንደ ሦስቱ ሥላሴዎች ሁሉ ሦስት የተለያዩ ባሕርያት ያሉት። ማለትም አንዱ እግዚአብሔር፣ እግዚአብሔር አብ፥ እግዚአብሔር ወልድና እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ተብሎ በአካል፥ በስምና በግብር እንደሚለይ ሁሉ እንደዚሁም ሰው በመንፈስ፥ በነፍስና በሥጋው ይለያል።

ይህን አባባል በጥልቀት ለመረዳት ዘፍጥረት 2:7ን በተጨማሪ መመልከቱ ይጠቅማል። «እግዚአብሔር አምላክም ሰውን ከምድር አፈር አበጀው፤ በአፍንጫውም የሕይወት እስትንፋስ አፍ አሰበት፤ ሰውም ሕያው ነፍስ ያለው ሆነ።» በጥቅሱ ላይ የተስመረባቸውን ሦስት ሐረጎች ለየብቻ ወስደን በምንመለከትበት ጊዜ፥ አሁንም ግልጽ የሚያደርጉልን ነገር ቢኖር ሦስቱን የሰው ባህርያት ነው። ይኸውም ሥጋው ከአፈር የተገኘ መሆኑን ግልጽ ሊያደርግልን፤ መንፈሱና ከዚያም በኋላ ደግሞ ነፍሱ በማይታይና በማይዳሰሰው የእግዚአብሔር እስትንፋስ ስለመፈጠራቸው እናያለን።

መንፈስና ሥጋ መለያየታቸው

ስዚህ ጥናታችን ክፍል በመግቢያነት ልጠቀምበት የፈለግሁት በ2ኛ ቆሮንቶስ 4:18 ላይ የሰፈሩትን የጳውሎስ ቃላት ነው:- *«...የሚታየው የጊዜው ነውና፥ የማይታየው ግን የዘላለም ነው።»* በዚህ ጥቅስ አማካይነት ጳውሎስ ግልጽ ያደረገልን ማንኛውም የሰው ልጅ ተገዝ ሊሆንላቸው የሚችል ሁለት

የምርጫ ዕድሉች መኖራቸውን ነው። ይኸውም በአንድ በኩል ለሚታይና ለሚዳሰሰው፥ ሆኖም ግን ጊዜያዊና ኃላፊ ለሆነው ምድራዊ ፍላጎቱ ማድላት ወይም ስውርና ረቂቅ ለሆነው ለማያዊና ዘላለማዊ ሕይወቱ ቅድሚያ መስጠት ናቸው። ሆኖም ክርስቲያኖች ከእነዚህ ከሁለቱ መስፈርቶች ምርጫቸው ለኋለኛው መሆን እንደሚገባው ጳውሎስ አበክሮ አስገንዝቧል።

እንደዚሁም ሰሎሞን በመጽሐፈ መክብብ 1:3 ላይ፥ *«ዘሠሐይ በታች በሚደክምበት ድካም ሁሉ የሰው ትርፉ ጭንድን ነው?»* በማለት ለምድራዊ ፍላጎቶች ተገዢ የመሆንን ከንቱነት ገልጽዋል። ይህ ሁሉ ልፋት አንድ ሰው በሚሞትበት ጊዜ የሚበንና የሚጠፋ ሲሆን ዘላለማዊነት ሊኖረው የሚችለው ግን መንፈሳዊ ሥራው ብቻ በመሆኑ ነው።

እስቲ እነዚህን ሁለት መሥፈርቶች በምን መልኩ እንደሚያነጻጽራቸው ከዚሁ ከመጽሐፈ መክብብ አንድ ጥቅስ በመውሰድ እንመልከት፦ *«እኔ በልቤ ስለ ሰው ልጆች፦ እንደ እንስሳ መሆናቸውን እንዲያዩ እግዚአብሔር ይፈትናቸዋል አልሁ። የሰው ልጆችና የእንስሳ ሰድል ፈንታ አንድ ነው ድርሻቸውም ትክክል ነው። እንዱ እንደሚሞት ሌላውም እንዲሁ ይሞታል። የሁለቱም አስትንፋስ አንድ ነው፤ ሁሉም ከንቱ ነውና ሰው ከእንስሳ ብልጫ የለውም። ሁሉ ወደ አንድ ቦታ ይሄዳልና፤ ሁሉ ከአፈር ነው፤ ሁሉም ወደ አፈር ይመለሳል። የሰው ልጆች ነፍስ ወደ ላይ እንደምትወጣ የእንስሳም ነፍስ ወደ ታች ወደ ምድር እንደምትወርድ የሚያውቅ ማነው?»* መጽሐፈ መክብብ 3:18-21

ሰሎሞን በዚህ ጥቅስ ውስጥ ሰውና እንስሳን እያመሳሰለ ሲናገር እናያለን። ሁለቱም ከአፈር እንደመፈጠራቸው፥ ተመሳሳይ ሥጋን ለባሽ ናቸውና በሚሞቱበት ጊዜ የሁለቱም አካል ፈራሽ በስባሽ ነው። ይህን እንጂ ከሞት በኋላ በሚጠብቃቸው ዕጣ ፈንታ ደግሞ እንደሚለያዩ ሰሎሞን ግልጽ አድርጎልናል። በቁጥር 21 ላይ እንዳሰፈረው፥ «የሰው ልጆች ነፍስ ወደ ላይ እንደምትወጣ የእንስሳም ነፍስ ወደ ታች ወደ ምድር እንደምትወርድ....» በማለት አነጻጽሯል። ከዚህ የምንረዳው፥ በዘፍጥረት 2:7 ላይ እንደተመለከትነው ሰው በእግዚአብሔር እስትንፋስ የተፈጠረ እንደመሆኑ በሚሞትበትም ጊዜ ያ እስትንፋስ (መንፈስና ነፍስ) በስባሽ ከሆነው ሥጋ በመለየት ወደ ፈጣሪው ይመለሳል ማለት ነው።

ይህንንም በግጠናከር አሁንም ሰሎሞን፦ *«አፈርም ወደ ነበረበት ምድር ሳይመለስ፥ ነፍስም ወደ ተሰጠው ወደ እግዚአብሔር ሳይመለስ ፈጣሪህን አስብ»* መጽሐፈ መክብብ 12:7

ስለዚህ ምንም እንኳን እግዚአብሔር ፍርድን የሚሰጠው በትንሣኤ ጊዜ ቢሆንም፥ ከዚያን በፊት እያንዳንዱ ሰው ወዲያውኑ እንደሞተ ነፍሱ ወደ እግዚአብሔር እንደምትመለስ ነው። ከዚያም ጊዜያዊ ማረፊያ ተሰጥቷት የመጨረሻው ፍርድ እስከሚሰጥበት የዘመኑ ፍጻሜ ድረስ ትጠባበቃለች።

የጻድቃን ከኃጢአት መለየት

ስለዚህ ርዕስ በጥልቀት ከመወያየታችን በፊት በቅድሚያ ልናነሳው የሚገባው ጥያቄ በሥጋ ሞት የተለዩትን ነፍሳት በሞትና በትንሣኤ መካከል ስለሚኖሩበት ሁኔታ ነው። ምንም እንኳን መጽሐፍ ቅዱስ ስለዚህ ጥያቄ የሚመልስልን መልስ የተብራራ ባይሆንም፥ ስለ ሁለት ፍሬ ሐሳቦች በእርግጠኝነት ለመናገር እንችላለን። ይኸውም በቅድሚያ የኃጥአንና የጻድቃን ነፍሳት ወዲያውኑ ለእንዴና ለመጨረሻ ጊዜ የሚለያዩ መሆናቸውንና በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ ከክርስቶስ በፊት በነበሩትና ከእርሱ በኋላ ባሉት የጻድቃን ነፍሳት ሁኔታ መካከል ልዩነት ስለመኖሩ ነው።

ይህንንም በማስመልከት መጽሐፍ ቅዱስ እነዚህ ምሥጢሮች የተጋረዱበትን መጋረጃ አልፎ አልፎ ገለጥ በማድረግ አንዳንድ ጠቃሚ መረጃዎችን ይፈነጥቅልናል። እነሆም ይህን ለማብራራት ያህል በቅድሚያ የምንጠቅሰው ምሳሌ እግዚአብሔር በጨካኙ የባቢሎን ንጉሥ ላይ ያስተላለፈውን ፍርድ አስመልክቶ ኢሳይያስ በምዕራፍ 14:9-11 ላይ የዘገበውን ነው። *«ሲኦል በመምጣትህ ልትገናኝህ በታች ታወከች፤ የሞቱትንም፥ የምድር ታላላቆች ሁሉ ለእንተ አንቀሳቀሰች፥ የአሕዛብንም ነገሥታት ሁሉ ከዙፋናቸው አስነሳች። እነዚህ ሁሉ - አንተ ደግሞ እንደ እኛ ደክመሃልን? እኛንስ መስለሃልን? ጌጥህና የበገናህ ድምጽ ወደ ሲኦል ወረደ፥ በበታችህም ብል ተነጥፎአል፥ ትልም መደረቢያህ ሆኖአል ብለው ይመልሱልሃል።»* ከዚህ ሐተታ ውስጥ ስለ ሙታን ነፍሳት ሁኔታ የምንረዳቸው አንዳንድ ጠቃሚ ነጥቦች አሉ። ለምሳሌ ሙታን ስለ ምድራዊው ሕይወታቸው አንዳንድ ትዝታዎች ሲኖራቸው ስለ መቻሉ እንገነዘባለን። እንደዚሁም የሙታን ነፍሳት እርስ በእርስ ስለ መተዋወቃቸውና በዚያም የቅጣት ቦታ (ሲያል) ውስጥ እንኳን ሆነው በቀድሞው የማዕረግ ደረጃቸው የሚተያዩ ስለ መሆኑ ተገልጿል።

ሕዝቅኤልም ስለሚቹ የግብጽ ንጉሥ ነፍስ ወደ ሲያል መውረድ አስመልክቶ በ32:17-32 ላይ ሰፋ ያለ ሐተታ አትርቧል። በተለይም በቁጥር 18 እና 19 ላይ እግዚአብሔር ራሱ ተናገራቸው ያላቸውን የሚከተሉት ቃላት አስፍሯል፦ *«የሰው ልጅ ሆይ፥ ስለ ግብጽ ብዛት ዋይ በል፥ አርስዋንና የብርቱዎችን አሕዛብ ሴቶች ወደ ጉድጓድ ከሚወርዱ ጋር ወደ ታችኛው ምድር ጣላቸው። በውበት የምትበልጪው ማን ነው? ውረጂ ካልተገረዙም ጋር ተኝ ...»* በመቀጠል ደግሞ ለዚሁ የግብጽ ንጉሥ በሲኦል ውስጥ ይገኙ የነበሩት የሙታን መናፍስት ምን ዓይነት አቀባበል እንዳደረጉለት እንመለከታለን።

«ዮንያላን አለቶች በሲያል ውስጥ ሆነው ከረዳቶቹ ጋር ይናገራታል፤ በሲይፍም የተገደሉት ያልተገረዙ ወርደው ተኝተዋል።» ሕዝቅኤል 32:21

ከዚህ ጥቅስም ቢሆን የምንረዳው ቀደም ሲል እንደተገለጸው ሀሰመታን የምድራዊ ሕይወት ስብዕናቸውን በመጠበቅ እርስ በእርስ የሚተዋወቁ፤ ስላለፈውም ሕይወታቸው በማንሳት የሚወያዩና ቅሬታቸውንም የማገላለጡ ስለ መሆኑ ነው።

እንደዚሁ ሀሰ ወደ አዲስ ኪዳኔ ስናመራም ስለ መታን መናፍስት ሁኔታ ተመሳሳይ ገለጻ ተስጥቶ እናገኛለን። ስዚህም በዓይነተኛ ምሳሌነቱ ልንጠቅሰው የሚገባው ጌታችን ኢየሱስ ራሱ በሉቃስ 16:22-26 ላይ ስለ አልዓዛርና ስለ ባለጠጋው ስው የሰማይ ቤት ሕይወት የተረከውን ነው፦- *«ድሃውም ሞተ፤ መላእክትም ወደ አብርሃም እቅፍ ወሰዱት፤ ባለጠጋውም ደግሞ ሞተና ተቀበረ። በሲያልም በሥቃይ ላይ ሳለ አሻቅቦ አብርሃምን በሩቅ አየ፤ አልዓዛርንም በእቅፉ። እርሱም እየጮኸ፦ አብርሃም አባት ሆይ ማረኝ፤ በዚህ ነበልባል እሠቃያለሁና፤ የጣቱን ጫፍ በውሃ ነክሮ ምላሴን እንዲያበርድልኝ አልዓዛርን ስደድልኝ አለ። አብርሃም ግን፦ ልጅ ሆይ አንተ በሕይወት ሳለህ መልካም እንደተቀበልህ አሰብ አልዓዛርም እንዲሁ ከፉ፤ አሁን ግን አርሱ በዚህ ይጽናናል አንተም ትሰቃያለህ። ከዚህም ሁሉ ጋር ከዚህ ወደ እናንተ ሊያልፉ የሚፈልጉ እንዳይችሉ፤ ወዲያ ያሉ ደግሞ ወደ እኛ እንዳይሻገሩ በእኛና በእናንተ መካከል ታላቅ ገደል ተደርጎአል አለ።»*

ከብሉይ ኪዳን መረዳታችን ባልተለየ መልኩ አሁንም ቢሆን ከዚህ ውስጥ የምናጤነው ፍሬ ነገር አንድ ስው ከሞተ በኋላ ሥጋው ሲቀበር ነፍሱ ግን ወደ ቀጣዩ ሕይወት ከማስታወስ፤ ከመናገር፤ ጸሎቷን ሰመግለጽና ከመሳለስት ችሎታዎቿ ጋር መሸጋገሯን ነው። በተጨማሪም ከዚህ ከጌታችን ገለጻ የምንረዳው ሌላው ታላቅ ቁም ነገር ጻድቃን ነፍሳትን ከኃጥአን ነፍሳት የሚለያቸው ግዙፍ ድንበር መኖሩን ነው። ጻድቃን የሚያርፉበት ሥፍራ (የአብርሃም እቅፍ) ተብሎ መጠራቱም በምድራዊው ሕይወታቸው የአብርሃምን ፈለግ ዘመከተል ራሳቸውን ለእግዚአብሔር በእምነት በማስገዛታቸው ነው።

42

ክርስቶስ አርአያችንና መታመኛችን

እስከ አሁን ስመመልከት የሞክርነው በዘመነ ብሉይ መታን ነፍሳትን ያጠብቃቸው የነበረውን ፅጣ ፈንታ በማስመልከት ሲሆን በመቀጠል ደግሞ ክርስቶስ ራሱ በሞቱና ትንሣኤው መካከል ያስፈባቸውን ልምምዶች ዘአዲስ ኪዳን ላይ በመንተራስ እንከታተላለን።

በሞትና ትንሣኤ መካከል

ስዚህ ጥናታችን ክፍል መግቢያ እንዲሆነን የመረጥኩት ዳዊት ስለ ክርስቶስ መሞት፤ መቀበርና ከመታን መነሳት አስመልክቶ ከሸሀ ዓመታት በፊት የተናገረውን ትንቢት ነው። *«ሁልጊዜ እግዚአብሔርን በፊቴ አየዋለሁ፤ በቀኜ ነውና አልታወክም። ስለዚህ ልቤን ደስ አለው ምላሴም ሐሴት አደረገች፤ ሥጋዬም ደግሞ በተስፋ ታድራለች፤ ነፍሴን በሲያል አትተዋትምና፤ ቅዱስህንም መበስበስን ያይ ዘንድ አትተወውም። የሕይወትን መንገድ አሳየሃኝ፤ ከፊትህ ጋር ደስታን አጠገብኸኝ፤ በቀኝህም የዘላለም ፍሥሐ አለ።»* መዝሙር 16:8-11 ይህን ጥቅስ ዳዊት ስለ ራሱ ሳይሆን ስለ ክርስቶስ

የተናገረው ለመሆኑ ጴጥሮስ በዚሁ በሐዋርያት ሥራ 13:35 ላይ አረጋግጦልናል። እነሆም ከዚህ በመነሳት ከሚከተሉት ድምዳሜዎች ላይ ለመድረስ እንችላለን።

በትድግያ ክርስቶስ በሞተበት ጊዜ አካሉ በመቃብር ውስጥ እንዲያርፍ ቢደረግም ሥጋው ግን መበስበስን ላለማየቱ እንረዳለን። በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ ምንም እንኳን የክርስቶስ ነፍስ ወደ ሲኦል የወረደች ቢሆንም፣ በዚያ እስከ ዕሰተ ትንሣኤው አለመቆየቷን እንገነዘባለን። ይህ በብሉይ ኪዳን የተዘገበው የዳዊት ትንቢት በአዲስ ኪዳንም የተረጋገጠ ለመሆኑ ደግሞ ሉቃስ 23:43ን ብቻ በማስረጃነት መጥቀሱ በቂ ነው። ክርስቶስ ገና በመስቀል ላይ እንዳለ ከጎኑ ከተሰቀሉት ክፋ አድራጊዎች ለአንዱ «*እውነት እልሃለሁ፣ ዛሬ ከእኔ ጋር በገነት ትሆናለህ*» ሲል ነው ቃል የገባለት። ይህም ማለት የክርስቶስ ነፍስ ያመራችው ለጋጥአን ነፍሳት ወደ ተከለለው ማረፊያ ሥፍራ ሳይሆን ወደ ገነት (የጻድቃን መናፈሻ የሆነ የአትክልት ሥፍራ) መሆኑን ነው።

ይህንን መደምደሚያችንን የሚያጠናክርልን ሌላው ጥቅስ ደግሞ በዚሁ ምዕራፍ በቁጥር 46 ላይ የሰፈረው ሌላ ማስረጃ ነው። «*ኢየሱስም በታላቅ ድምጽ ጮኽ አባት ሆይ ነፍሴን በእጅህ አደራ እሰጥሃለሁ አለ። ይህንም ብሎ ነፍሱን ሰጠ።*» እንግዲህ ከዚህም ቢሆን ለመረዳት የምንችለው ምንም እንኳን የክርስቶስ ሥጋ በመቃብር ውስጥ ሊያርፍ ግድ ቢሆንም ነፍሱ በቀጥታ ወደ አባቱ ማምራቷን ነው የምናየው። ክርስቶስም የእኛን ሥጋ ለብሶ ከድንግል ማርያም በመወለዱ፣ እንደ ማንኛውም ሰው ሁሉ የሞት ጽዋ ቀምሶ ይቀበር እንጂ ነፍሱ ግን ከሥጋው ከተለየች በኋላ ሲኦልን ጎብኝታ ወደ ገነት ለመመለሷ ሐዋርያው ጳውሎስና ጴጥሮስ እንደሚከተለው ያረጋግጡልናል። «*ወደ ምድር ታችኛው ክፍል ደግሞ ወረደ ማለት ካልሆነ፣ ይህ ወጣ ማለትስ ምን ማለት ነው? ይህ የወረደው ሁሉን ይሞላ ዘንድ ከሰማያት ሁሉ በላይ የወጣው ደግሞ ያው ነው።*» 1ኛጴጥሮስ 3:18-20

እንግዲህ የክርስቶስ ሲያልን መጎብኘት በዚህ መልኩ እስክ ተረጋገጠ፣ ምናልባት ሊነሳ የሚችለው ጥያቄ ለምን ወደዚያ መውረድ አስፈለገው? የሚለው ሊሆን ይችላል። ለዚህ ደግሞ መልሱ ክርስቶስ የአዳምን ኃጢአት ይሸከም ዘንድ ሥቃዩንም በዚያ መጠን እኩል በእኩል መቅመስ ስላለበት ነው የሚለው ይሆናል። ይሸውም በምድራዊ ሕይወቱ በጎልጎታ በመስቀል ላይ ደሙን ሲያፈስ፣ በሰማያዊ ሕይወቱ ደግሞ ሲያልፍ ሲኦል በመውረድ የኃጥአንን ለቅሶና ሰቆቃ ተጋርቷል ማለት ነው። ይህንንም ካሚላ በኋላ ነበር ክርስቶስ ሞትን ድል በማድረግ መቃብርን ድል አድርጎ የተነሳው። እንግዲህ እኛንም በክርስቶስ ተመሳሳይ ዕድል የሚጠብቀን ለመሆኑ ጳውሎስ በ1ኛ ቆሮንቶስ 15:20-22 ላይ እንደሚከተለው አረጋግጦልናል። «*አሁን ግን ክርስቶስ ላንቀላፉት በኩራት ሆኖ ከሙታን ተነሥቶአል። ሞት በሰው በኩል ስለመጣ ትንሣኤ መታን በሰው በኩል ሆኖአልና።*» እንግዲህ በትንሣኤ ጊዜ ሁሉም ነፍሳት የአርአያቸውን የክርስቶስን ፈለግ በመከተል ከሥጋቸው ጋር ለዘላመኛ ጊዜ በመዋሃድ የሚነሱ ሊሆን፣ በዚያንም ወቅት የሚኖራቸው ሰብዕና አንደ

መጀመሪያው አዳማዊ ተፈጥሮአቸው ሁሉ በመንፈስና በአካል የተሟላ ይሆናል።

ከሞት በኋላ ያለው የክርስቲያን ዕጣ ፈንታ

ይህንን ጥናታችንን የተሟላ ለማድረግ በመቀጠል አዲስ ኪዳን፣ ከዘመነ ፍጻሜ ወይም ከትንሣኤ በፊት የሚሞቱትን ክርስቲያኖች ነፍስ ምን ዕድል እንደሚጠብቃት የሚያስተምረውን ትምህርት በአጭሩ እንዳስሳለን።

ቀደም ሲል እንደተመለከትነው ከክርስቶስ ትንሣኤ በፊት የሞቱትን ጻድቃኖች ነፍስ ታርፍ የነበረው «የአብርሃም አቅፍ» በመባል ከሚታወቀው የገነት ክፍል ነበር። ይሁን እንጂ ከክርስቶስ ትንሣኤ በኋላ በእርሱ አምኖ ለሞተ ለማንኛውም ክርስቲያን ከመንግሥተ ለማያት ወይም ከአግዚአብሔር ማደሪያ የመግባቱ ዕድል ክፍት ሆኖለታል። ይህንንም በማስረገጥ አዲስ ኪዳን በተደጋጋሚ የገለጸው ሲሆን በበኩላችን ግን ጥቂቶቹን ብቻ በምሳሌነት እንጠቅሳለን። በቅድሚያ ስለ መጀመሪያው የክርስትና ሰማዕት እስጢፋኖስ አሟሟት የሚተርከውን የሐዋርያት ሥራ 7:55-56 እና 7:59-60 በመውሰድ እንመለከታለን። «*መንፈስ ቅዱስንም ተሞልቶ ወደ ሰማይ ትኩር ብሎ ሲመለከት የእግዚአብሔርን ክብር ኢየሱስንም በእግዚአብሔር ቀኝ ቆሞ አየና፦ እነሆ፣ ሰማያት ተከፍተው የሰው ልጅም በእግዚአብሔር ቀኝ ቆሞ አያለሁ አለ።*» ሐዋርያት 55-56 «*ጌታ ኢየሱስ ሆይ፣ ነፍሴን ተቀበል ብሎ ሲጠራ ይወግሩት ነበር። ተንበርክኮም ጌታ ሆይ ይህን ኃጢአት አትቁጠርባቸው ብሎ በታላቅ ድምጽ ጮኸ። ይህንንም ብሎ አንቀላፋ .....*» የሐዋርያት ሥራ 59-60

ከዚህ ጥቅስ በቅድሚያ የምንረዳው እስጢፋኖስ ጌታ ኢየሱስን ከአግዚአብሔር ቀኝ በክብር ተሞልቶ ያየው መሆኑን ሲሆን በመቀጠል ደግሞ ነፍሱ ከሥጋው ልትለይ ስትል «ጌታ ኢየሱስ ሆይ፣ ነፍሴን ተቀበል» በማለት በእርግጠኝነት መናገሩን ነው። አንድ አማኝ በሚሞትበት ጊዜ ነፍሱ እንደ እስጢፋኖስ ሁሉ በቀጥታ ወደ ክርስቶስ የምትሄድ ስለመሆኗ ጳውሎስ በ2ኛ ቆሮንቶስ 5:6-8 ላይ ቀጣዩን ማረጋገጫ ሰጥቷል።

«*እንግዲህ ሁል ጊዜ ታምነን፣ በእምነት እንጂ በማየት አንመላለስምና በሥጋ ስናድር ከጌታ ተለይተን በስደት እንዳለን የምናውቅ ከሆንን ታምነናል ይልቁንም ከሥጋ ተለይተን በስደት መኖር በጌታም ዘንድ ማደር ደስ ይለናል።*» እነዚህ የጳውሎስ ቃላት ሁለት ነገሮችን ይጠቁሙናል። ከዚህም የመጀመሪያው አማኙ በምድራዊ ሕይወት እስካለ ድረስ መንፈሱ በአካሉ ውስጥ የምትቆይ መሆኑን ሲሆን ዘሞት ከተለየ በኋላ ግን ከአካሉ በመለየት በእግዚአብሔር ፊት እንደምትቀርብ ነው።

ጳውሎስ በፊልጵስዩስ መልእክቱም ላይም ቢሆን የሚያነጻጽረው በሞት ላቢያ የመንፈስ ነጻ መውጣትና፣ አንድ ሰው ምድራዊ ተልዕኮውን እስከሚያሳካ የመንፈሱን ከሥጋ አለመለየት ጠቀሜታው ነው። ይህንን እንደሚከተለው

አብራርቶት እናያለን፦ «ለእኔ ሕይወት ክርስቶስ፥ ሞትም ጥቅም ነውና። ነገር ግን በሥጋ መኖር ለእኔ የሥራ ፍሬ ቢሆን ምን እንድመርጥ አላስታውቅም። በእነዚህም በሁለቱ እጨነቃለሁ፥ ልሄድ ክክርስቶስም ጋር ልኖር እናፍቃለሁ፥ ከሁሉ ይልቅ እጅግ የሚሻል ነውና፤ ነገር ግን በሥጋ መኖሬ ስለ እናንተ እጅግ የሚያስፈልግ ነው።» ፊሊጵስዩስ 1:21-24

እንግዲህ በምሳሌነት ከጠቀስናቸው ከአስጢፋኖስና ከጳውሎስ ትምህርቶች የምንቀስመው ፍሬ ነገር ጄንኛውም በዚህ በምንኖርበት ዘመን ያለ አማኝ በሚምትበት ጊዜ መንፈሱ ከሥጋው በመለየት በቀጥታ በጌታ በኢየሱስ ፊት የምትቀርብ መሆኗን ነው። ይህንን መሰሉን ዕድል ለመቀዳጀት የተቻሰው ጌታ ኢየሱስ በክፈለልን ካሣ ምክንያት ከኃጢአታችን ሁሉ ነጻ በመውጣታችን ነው። ዳሩ ግን ክርስቶስ በመስቀል ላይ ሞቱ የአዳምን ልጆች ከመቤዠቱ በፊት የሞቱት ጻድቃን ለጊዜው የሚያርፉበት ቦታ ነበር የሚለጣቸው። ሆኖም ግን ያ ቦታ ለክርስቲያኖች ከተከሰለው ገነት የተሰየ ነበር።

ይህንን የትምህርት ክፍል ለማጠናቀቅ የሙታን ትንሣኤ የክርስቶስን ትንሣኤ አርአያነት የተከተለ ነው ለማለት እንችላለን። ይኸውም የመታኑ ነፍስ ከነኑትም ሆነ ከሲያል በእግዚአብሔር ፊት እንድትቀርብ ከመጠራቷም ምድራዊ ሥጋዋን ዳግመኛ የምትለብስ መሆኑንም ነው። በመሆኑም መንፈስና ሥጋ እንደገና በመዋሃድ ሙሉ ስብዕናን ያስገኛሉ።

በትንሣኤ የምንላበሰው ሥጋ የቀድሞውን አካላችንን ስለ መምሰሉ

ይህን ርዕስ ለመረዳት ለሥጋዊው አእምሮአችን በእጅጉ ይከብደዋል። ለምሳሌ አንድ ሰው ከሦስት ሺህ ዓመታት በፊት ሞተ እንበል፤ እንግዲህ የዚህ ሰው ሥጋ አፈርና ትቢያ ለመሆኑ ቅንጣት ታህል የማያጠራጥር ነው። በሌላ በኩል ደግሞ አንድ ሰው አካሉን አመድ ዱቄት ባደረገ ፈንጂ ሳቢያ ሞተ እንበል። ከዚህም በመነሳት ሊቀርብ የሚችለው ጥያቄ እንዲት እንዲህ ዓይነቱ ደብዛው የጠፋ የአንድ ሰው አካል በትንሣኤ ጊዜ ዳግመኛ ተገጣጥሞ የቀድሞውን ገጽታ ሊይዝ ይችላል? የሚለው ነው። ሆኖም የዚህ ጥያቄ መልስ አጭርና ግልጽ ነው። ለእግዚአብሔር አንዳችም የሚሳነው ነገር አለመኖሩ ነው። ደግሞም መጀመሪያም ቢሆን አግዚአብሔር አዳምን እንዲት እንደፈጠረው ስናስታውስ ለእርሱ ማናቸውንም ነገር አድሶ ለመሥራት እንደማያስችግረው እናጤናለን።

ይህንንም በተመለከተ መጽሐፍ ቅዱስ ለማናቸውም ሊነሳ ለሚችል ጥያቄ ግልጽ መልስ የሰጠበት መሆኑን እንመለከታለን። ለምሳሌ መዝሙር 138ን ወስደን ብንመለከት የእግዚአብሔርን ሁሉን አድራኒነት ቁልጭ አድርጎ ያሳየናል። ይህንን አባባላችንን ግልጽ ለማድረግ ከዚሁ መዝሙር በተለይ ከቁጥር 13-16 ያለውን ብቻ በመጥቀስ እንመለከታለን፦ «አቤቱ፥ አንተ ሁላሊቴን ፈጥረሃልና፥ በእናቴም ሆድ ለውረ ሽኖልና። ግሩምና ድንቅ ሆኜ ተፈራአለሁና አመሰግንሃለሁ፥ ሥራህ ድንቅ ነው፥ ነፍሴም እጅግ ታውቀዋለች። እኔ በሥውር በተሠራሁ ጊዜ፥ አካሌም በምድር ታች በተሠራ ጊዜ፥ አጥንቶቼ ከአንተ አልተሠወሩም። ያልተሠራ አካሌን ዓይኖችህ አዩኝ፥ የተፈጠሩ ቀናቸ ሁሉ አንድ ስንኳ ሳይቀር በመጽሐፍህ ተጻፈ።» በዚህ ምንባብ ውስጥ ዳዊት ሲናገር የምንመለከተው ስለ መንፈሱና ስለ ነፍሱ አፈጣጠር ሳይሆን ስለ ሥጋው ወይም አካሉ ነው። ይህንንም በተመለከተ እግዚአብሔር እንዲት እንደ ፈጠረው ሊገልጽ አንደኛ እግዚአብሔር ያንን ሰው ከመፍጠሩ በፊት እንዲት አድርጎ እንደሚፈጥረው በእርሱ ዘንድ የታወቀ ሰመሆኑና፥ እያንዳንዱንም የአካል ክፍሉን የሚያውቀው ስለ መሆኑ ነው።

እርግጥ እንደ ሰው ሁሉ እንሰሳትና ዕፅዋትም መሠረታዊ ከሆኑ ማዕድናት ለመፈጠራቸው በሳይንስም ጭምር የተረጋገጠ ነው። ይሁን እንጂ የሰው አፈጣጠር ደግሞ አንድ በአንድ በእግዚአብሔር መዝገብ ላይ የሰፈረ ስለ መሆኑ ነው ዳዊት የሚያበሥረን። ይህንን ይበልጥ በማረጋገጥ ጌታ ኢየሱስ በማቴዎስ 10:30 ላይ የሚከተለውን ተናግሯል፦ «የአናንተስ የራሳችሁ ጠጉር ሁሉ እንኳ ተቆጥሮአል።» እንግዲህ ይህ ሁሉ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መረጃ ግልጽ የሚያደርግልን የሰውን ልጅ አሀዱ ሊል ሰፈጠረው አምላክ ዳግመኛም በዚያው መልኩ መፍጠሩ የማይሳነው መሆኑን ነው። ስለ እያንዳንዱም ሰው ቅድመ ተፈጥሮ መገዝቡ በእግዚአብሔር እጅ እንደ መገኘቱ መጠን በዚያኑ ሁኔታ ዳግመኛ እንዲፈጠር ማዘዙ የማይከብደው ነው። ምናልባትም ልዩነት ሊኖር ይችላል ብንል እንኳ የመጀመሪያው ተፈጥሮ ደረጃ በደረጃ የማዕድናትን ድብልቅ የጠበቀ ሊሆን የትንሣኤው አካል ግን ከመቅዕበት በትዕዛዝ ብቻ ተሚልቶ ከመገኘቱ ላይ ነው።

በአንድ ሰው በቀድሞው አካሉና ከትንሣኤ በኋላ በሚኖረው አካሉ መካከል ተመሳሳይነት ስለ መኖሩም መጽሐፍ ቅዱስ ግልጽ ያደርግልናል። ለዚህም ዋነኛውና የማያጠራጥረው ማስረጃ የራሱ የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ ነው።

ጌታ ከትንሣኤው በኋላ ለሐዋርያቱ በተገለጸበት ጊዜ ሁሉ ከታላቅ ድንጋጤና ፍርሃት ላይ ወድቀው ነበር። ሆኖም በቅድሚያ እርሱ ራሱ ስለ መሆኑና የለበለውም የቀድሞው አካሉን ዓይነት ለመሆኑ በሚከተለው ሁኔታ አረጋግጠላቸዋል፦ «እኔ ራሴ እንደሆንሁ እጆቼንና እግሮቼን አዩ፤ በእኔ እንደምታዩት መንፈስ ሥጋና አጥንት የለውምና እኔን ዳሰሳችሁ አዩ አላቸው። ይህንንም ብሎ እጆቹንና እግሮቹን አሳያቸው።» ሉቃስ 24:39-40 ይሁን እንጂ ከሐዋርያቱ አንዱ ቶማስ በዚህም አጋጣሚ አልተገኘ ናሮ፥ ሌሎቹ ደቀ መዛሙርት ስለ ጌታ ትንሣኤ የነገሩትን ለማመን አልቻለም። ሆኖም በዮሐንስ 20:27 ላይ እንደምንመለከተው ጌታ ከአንድ ሳምንት በኋላ ቶማስ በተገኘበት ዘመገለጥ፥ እንዲህ ሊል በቀጥታ አነጋግሮታል፦ «ለዚያን ዘኋላ ቶማስን

ጣትህን ወደዚህ አምጣና በጎኔ አግባው፤ ያመንህ እንጂ ያላመንህ አትሁን አለው።»

ከዚህ ከጌታ ትንሣኤ በግልጽ ለመረዳት የምንችለው መታንም በትንሣኤያቸው ወቅት ተመሳሳይ አካል የሚለብሱ መሆናቸውን ነው። የጌታችን የትንሣኤው አካል ከምድራዊው አካሉ የተለየበት ነገር ቢኖር እንደ ቀድሞው የእንቅስቃሴ ውሱንነት የሌለው መሆኑ፤ በማናቸውም ሥፍራ ሊታይ ወይም ሊሰፍር መቻሉ፤ ምንም የሚያግደው ነገር አለመኖሩና ከምድር እስከ ሰማይ ለመመላለስ ብቃት መቀዳጀቱን ነው። እንደዚሁ ሁሉ ደቀ መዛሙርቱም በዕለተ ትንሣኤ የእርሱን የመሰለ አካል የሚቀዳጁ ለመሆኑ እንደሚከተለው ቃል ገብቶላቸዋል፦ *«ወላጆችም ሰንኳ ወንድሞችም ዘመዶችም ወዳጆችም አሳልፈው ይሰጡአችኋል፤ ከእናንተም አንዳንዱን ይገድላሉ፤ በሁሉም ሰለ ስሜ የተጠላችሁ ትሆናላችሁ ከራሳችሁም አንዲት ጠጕር ሰንኳ አትጠፋም፤ በመታገሳችሁ ነፍሳችሁን ታገኛላችሁ።»* በዚህ ጥቅስ ላይ በግልጽ እንደ ሰፈረው የቀድሞው ምድራዊው አካላችን ቢቆረጥ ቢቃጠል፤ ቢመተርና ቢዘለል እንኳ በዘመነ ምዕአት ያንኑ ገጽታ ይዘን የምንነሳ መሆኑን ነው። ሌላው ቀርቶ «ከራሳችሁም አንዲት ጠጕር እንኳ አትጠፋም» በማለት ጌታ ራሱ አረጋግጦልናል።

ለማጠቃለል ያህል መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚያስተምረው ኃያሉ እግዚአብሔር ማናቸውንም ነገር ለማድረግ ጥበቡና ችሎታው ያለው አምላክ እንደ መሆኑ፤ በዕለተ ትንሣኤ ከቀድሞው ምድራዊ አካላችን ጋር ተመሳሳይ የሆነ አዲስ አካል የሚያለብሰን መሆኑን ነው።

43

ስለ ትንሣኤ በብሉይ ኪዳን አስቀድሞ የተነገረ ስለመሆኑ

ከዚህ በመቀጠል ደግሞ ልዩ ትኩረት በመስጠት የምንከታተለው የትንሣኤን እውነትነት በማስመልከት ቀተለይ በብሉይ ኪዳን የሰፈረው መለኮታዊ ቃል ኪዳን ነው። ለዚህም በቅድሚያ ጳውሎስ ሞትና መቀበር፤ ከዚያም ሞትን ድል አድርጎ መነሳት የተናገራቸውን ቁልፍ ቃላት በመጥቀስ ይሆናል፦ *«እኔ ደግሞ የተቀበልሁትን ከሁሉ በፊት አሳልፌ ሰጠኋችሁ እንዲህ ብዬ መጽሐፍ እንደሚል ክርስቶስ ስለ ኃጢአታችን ሞተ ተቀበረም፤ መጽሐፍም እንደሚል በሦስተኛው ቀን ተነሣ።»* 1ኛ ቆሮንቶስ 15:3-4

በዚህ ጥቅስ ውስጥ ጳውሎስ ከአንድም ሁለት ጊዜ «መጽሐፍ እንደሚል» የሚሉትን ቃላት ደጋግሟል። እንግዲህ ትልቁ ጥያቄ ይህ ጳውሎስ «መጽሐፍ» በማለት የጠቀሰው የትኛውን መጽሐፍ በማስመልከት ነው የሚለው ይሆናል። ስለዚህ ደግሞ ያለ ምንም ማመንታት የሚኖረው መልስ ብሉይ ኪዳንን ነው የሚል ይሆናል። ከጳውሎስ መልዕክቶች በፊት የነበረው ብቸኛው የአስራኤላውያን የኃይማኖት መጽሐፍ ይኸው ብሉይ ኪዳን ነበር።

ስለዚህም ከዚህ በማከታተል ትንሣኤን በማለመልከት በብሉይ ኪዳን ውስጥ ከሠፈሩት ዋና ዋና ትንቢቶች አለፍ አለፍ በማለት እንመለከታለን።

በመዝሙረ ዳዊት

እንደሚታወቀው ቀደም ሲል ዳዊት ስለ ራሱ የሚናገር በማለመለል ስለ ክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ በመዝሙር15:8-11 ላይ እንደተነበየ ተመልክተናል።

ኄ

በተመሳሳይ ሁኔታም ዳዊት በመዝሙር 70:20-21 ላይ ስለዚሁ ስለ ክርስቶስ ትንሣኤ አስመልክቶ በቀጥታ ለእግዚአብሔር የተናገራቸውን ቃላት በማስመልከት እንመለከታለን። *«ብዙ ጭንቀትንና መከራን አሳይተኸኛልና፤ ተመልሰህም ሕያውም አደረግኸኝ ከምድር ጥልቅም እንደገና አወጣኸኝ። ጽድቅህንም አብዛው፤ ተመልሰህም ደስ አሰኘኝ፤ ከጥልቅም እንደገና አወጣኸኝ።»*

ይህን እስከተረዳን ዘንዳ በመቀጠል ደግሞ ክርስቶስ እኛን ለመቤዠት ሲል ሊያልፋቸው የሚገባ እምስት ተከታታይ ደረጃዎች መኖራቸውን እናጤናለን። አንደኛ፦ የጭንቀትና የመከራ ፈተና፤ ሁለተኛ፦ ወደ ምድር ጥልቅ የመውረድ ፈተና፤ ሦስተኛ፦ የክርስቶስ ተመልሶ ሕያው መሆን፤ አራተኛ፦ የክርስቶስ ከምድር ጥልቅ መውጣት ማለትም ትንሣኤው፤ አምስተኛ ፦ ከትንሣኤው በኋላ በእግዚአብሔር ቀኝ በመቀመጥ ታላቅ ደስታን መቀዳጀቱን። እነዚህ ከመዝሙረ ዳዊት የተጠቀሱት የሁለቱም መዝሙሮች ትኩረት ማለትም የመዝሙር 15 እና የመዝሙር 70 በክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ ላይ ሲሆን፤ በተቀሩት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ውስጥ ደግሞ ስለ ጠቅላላ የአዳም ልጆች ትንሣኤ የሚናገሩ ትንቢቶችን እናነኛለን።

በኦሪት ዘፍጥረት

በዚህ የትምህርታችን ክፍል ውስጥ ዘቅድሚያ የምንመለከተው እግዚአብሔር በዘፍጥረት 17:8 ላይ ለአብርሃም የገባለትን ቃል ኪዳን ነው፦ *«ለእንግድነት የምትኖርባትን ምድር፤ የከነዓን ምድር ሁሉ ለዘላለም ግዛት ይሆንህ ዘንድ ለአንተና ከአንተ በኋላ ለዘርህ እሰጣለሁ፤ አምላክም እሆናቸዋለሁ»* እግዚአብሔር ለአብርሃም ከገባለት ከዚህ ቃል ኪዳን ውስጥ ከልብ ልናጤናቸው የሚገቡን ሁለት ፍሬ ነገሮች አሉ። እነርሱም፦ አንደኛ የከነዓንን ምድር በቅድሚያ አብርሃም ከዚያ በኋላ ዝርያዎቹ የሚወርሷት መሆኑንና በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ ለዚያች ምድር ባለቤቷ በመሆን የሚቆዩት ለተወሰነ ጊዜ ሳይሆን ለዘለዓለም መሆኑን ነው።

ሆኖም ይህን የትንቢት ቃል ጠለቅ ብለን በምንመረምርበት ወቅት ምንም እንኳ ትንቢቱ ከተነገረ በሺህ የሚቀጠሩ ዘመናት ያለፉ ቢሆንም ሙሉ በሙሉ ተፈፃሚነት አለማግኘቱን እንረዳለን። ለምሳሌ አብርሃም ራሱ በዘለቄታነት የያዘው ሥፍራ ከሳዕር ልጅ ከኤፍሮንም የገዛው የመቃብር ዋሻ ብቻ ሲሆን፤ እንደዚሁም የአብርሃም ዘር የሆኑት እስራኤላውያን እንደተገባላቸው ቃል እስከ እሁን የከነዓንን ምድር ሙሉ በሙሉ በቁጥጥራቸው ሥር አለማዋላቸውን እንመለከታለን። እንበልና እስራኤላውያን ዕድል ቢቀናቸውና መላውን የከነዓን ግዛት ቢቆጣጠሩ እንኳ እሁንም ያ እግዚአብሔር ለአብርሃም የገባው ቃል ኪዳን ተፈጻሚነት እግኝቷል ብሎ ለመናገር እየለደፍርም። እግዚአብሔር የተናገራቸው ቃላት *«የከነዓን ምድር ሁሉ ለዘላለም ግዛትህ ይሆን ዘንድ ለአንተና ከአንተ በኋላ ለዘርህ እሰጣለሁ»* ስለሚልና ዳሩ ግን አብርሃም እንኳንስ መላውን ከነዓንን ሊቆጣጠር፤ ለመቀበሪያ ሥፍራ እንኳ የገዛ በመሆኑ ነው። ታዲያ እግዚአብሔር እንደገባለት የተስፋ ቃል አብርሃም ከነዓንን የሚቆጣጠረው መቼ ይሆን የሚለው ጥያቄ መነሳቱ የማይቀር ነው።

ለዚህም መልሱ እጭርና ግልጽ ነው። ያ የተሰፋ ቃል ተፈጻሚነት የሚያገኘው ከዚያ በግዝ ካገኘው የኤፍሮን የመቃብር ዋሻ፤ በትንሣኤ ሲነሳ ነው። በአሪት ዘፍጥረት በተገባው ቃል ኪዳን መሠረት የአብርሃም የከነዓንን ምድር መውረስ ተፈጻሚነት ሊያገኝ የሚችለው በዚህ ሁኔታ ብቻ ለመሆኑ የእግዚአብሔር ቃል ያረጋግጥልናል። በመሆኑም የአብርሃም ትንሣኤ የሁሉንም የአዳም ልጆች ትንሣኤ የሚያበሥር ነውና የመጽሐፍ ቅዱስ የመጀመሪያ ክፍል በሆነው በአሪት ውስጥ መስፈሩ።

መጽሐፈ ኢዮብ

ጥንታዊነት አላቸው ከሚባሉት የብሉይ ኪዳን መጽሐፍት አንዱ በሆነው በመጽሐፈ ኢዮብም ውስጥ በተመሳሳይ ሁኔታ የትንሣኤ መኖር ተገልጾ እናነኛለን። ምንም እንኳን ባለ ታሪኩ ኢዮብ በአንድ ወቅት ለመራራና የጨለመ ሕይወት ቢዳረግም በእግዚአብሔር ረዳትነት፤ ነፍሱ ዘላለማዊነትን እንደምትቀዳጅና ሥጋውም በትንሣኤ እንደሚነሳ በሚከተሉት ቃላት አረጋግጧል። *«እኔን የሚቤዠኝ ሕያው እንደሆነ፤ በመጨረሻም ዘመን በምድር ላይ እንዲቆም ይህ ቁርበቴም ከጠፋ በኋላ፤ ከዚያን ጊዜ ከሥጋዬ ተለይቼ እግዚአብሔርን እንዳይ አውቃለሁ፤ እኔ ራሴ አየዋለሁ፤ ዓይኖቼም ይመለከቱታል ከእኔም ሌላ አይደለም።* ልቤ በመናፈቅ ዝሎአል።» ኢዮብ 19:25-27

በዚህ በኢዮብ መልእክት ውስጥ ግልጽ የሆኑ አባባሎችን እናጤናለን። ለምሳሌ «ይህ ቁርበቴም ከጠፋ በኋላ» የሚለው የለበሰውን ሥጋ ፈርሶ በስበሶ ወደ ትቢያነት መለወጥ የሚያመለክት ሲሆን፤ «ዓይኖቼም ይመለከቱታል» ማለቱ ደግሞ አዲስ ሥጋ በመልበስ ከእግዚአብሔር ፊት መቅረቡን የሚነግረን

ነው። እንደዚሁም «የሚቤዠኝ ሕያው እንደሆነ» የሚለው ትንቢታዊ ቃል፥ በኋላ ዘመን ወደሚነሳው መሢሕ ክርስቶስ የሚያመለክት መሆኑ ግልጽ ነው።

በትንቢተ ኢሳይያስ

ክክርስቶስ ልደት በፊት ለባት መቶ ዓመታት ያህል ቀደም ብሎ የተነሳው ታላቁ ነቢይ ኢሳይያስ ሲሆን ጌክ እንደ ኢዮብ ሁሉ ስለ ትንሣኤ እውነትነት በማስረገጥ ተናግሯል። ለማስረጃም ያህል በኢሳይያስ 26:19 ላይ የሰፈረውን የሚከተለውን ትንቢት መጥቀሱ ይበቃል፦ *«ሙታንህ ሕያዋን ይሆናሉ፥ ሬሳዎችም ይነሳሉ። በምድር የምትኖሩ ሆይ፥ ጠልህ የብርሃን ጠል ነውና፥ ምድርም ሙታንን ታወጣለችና ንቁ ዘምሩም።»* እንደዚህ አባባል ኢሳይያስ የሚያስተላልፈው መልእክት የራሱን ትንሣኤ ከማብሠር ጎን ለጎን እንደ እርሱ በእግዚአብሔር የሚያምኑ ምዕመናን ጭምር ለጊዜው መሞታቸው ባይቀርም «ሬሳዎችም ይነሳሉ» ሲል በተነበየው መሠረት ለዳግመኛ ጊዜ አዲስ ሥጋን በመልበስ ተነስተው በአምላካቸው ፊት በደስታ እንደሚዘምሩ ነው። ኢሳይያስ «ጠልህ የብርሃን ጠል ነውና» ሲል መናገሩም ልክ እንደ አህል ዘር ሁሉ ፊርሶ በስብሶ ወደ አፈርነት የተለወጠው የሰው አካል በዕለተ ትንሣኤ ብርሃን ተላብሶ የሚነሳ መሆኑን በማብሰር ነው። በጠል የተመሰለው ብርሃንም መንፈስ ቅዱስን የሚወክል ለመሆኑ በኋላ በተነሱት የአዲስ ኪዳን ጸሐፊዎች ተረጋግጧል። ለምሳሌም ያህል ጳውሎስ በሮሜ መልእክቱ 8:11 ላይ የሚከተለውን እንደገለጸ እናያለን፦ *«ነገር ግን ኢየሱስን ከሙታን ያስነሳው የእርሱ መንፈስ በእናንተ በሚኖረው በመንፈሱ ለሚሞተው ለሰውነታችሁ ደግሞ ሕይወትን ይሰጠዋል።»* እንግዲህ ጳውሎስ በማያሻማ መልክ ያሰፈረው መልእክት ግልጽ የሚያደርግልን ጌታ ኢየሱስን ከመቃብር ያስነሳው መንፈስ ቅዱስ፥ በክርስቶስ እምነው የሞቱትን ለምች ሁሉ በተመሳሳይ ሁኔታ መንፈስ ቅዱስ በውስጣቸው በማደር እንደሚያስነሳቸው ነው።

በትንቢተ ዳንኤል

ትንሳኤን በማስመልከት ሌላ ግልጽ ትንቢት ሰፍሮ የምናገኘው በትንቢተ ዳንኤል ውስጥ ሲሆን፥ ይህንንም መልእክት ነቢዩ በቀጥታ ከመልእክቱ ገብርኤል የተቀበለው ስለ መሆኑም መጠቀሱን እናጤናለን።

«በዚያም ዘመን ስለ ሕዝብህ ልጆች የሚቆመው ታላቁ አለቃ ሚካኤል ይነሳልኛ፤ ሕዝብም ከሆነ ጀምሮ እስከዚያ ዘመን ድረስ እንደ እርሱ ያለ ያልሆነ የመከራ ዘመን ይሆናል፤ በዚያም ዘመን በመጽሐፉ ተጽፎ የተገኘው ሕዝብህ ሁሉ ይድናሉ። በምድርም ትቢያ ውስጥ ካንቀላፉት ብዙዎች ይነቃሉ፤ እኩሌቶቹ ወደ ዘላለም ሕይወት፥ እኩሌቶቹም ወደ እፍረትና ወደ ዘላለም ጉስቁልና። ጥበበኞቹም እንደ ሰማይ ጸዳል ብዙ ለምችንም ወደ ጽድቅ የሚመልሱ እንደ ከዋክብት ለዘላለም ይደምቃሉ።» ዳንኤል 12:1-2

የዚህ ጥቅስ የመጀመሪያ ክፍል በተለይ የዳንኤል ወገኖች በሆኑት በእስራኤላውያን ላይ ያተኮረ ሲሆን ይህንኑም ሌላው ነቢይ ኤርምያስ እንደሚከተለው በተመሳሳይ ሁኔታ ገልጾታል፦ *«ወዮ! ያ ቀን ታላቅ ነውና፥ እርሱንም የሚመስል የለምና፥ ያ የያዕቆብ መከራ ዘመን ነው፥ ነገር ግን ከእርሱ ይድናል።»* ኤርምያስ 30:7

ኤርምያስ እንዳመለከተው ምንም እንኳን እንደዚህ ዓይነት የመከራ ዘመን በእስራኤል ታሪክ ታይቶም ተሰምቶም የማያውቅ ቢሆንም ዳሩ ግን በመጨረሻ ላይ እስራኤላውያን ጠፍተው እንደማይጠፉ ነው። ዳንኤልም ቢሆን ይህንኑ በማስረገጥ ነው *«ሕዝብም ከሆነ ጀምሮ እስከዚያ ዘመን ድረስ እንደ እርሱ ያለ ያልሆነ የመከራ ዘመን ይሆናል»* ሲል መግለጹ።

ይህ የመጨረሻው የፈተና ዘመን እጅግ የከፋ ቢሆንም ትሱ ዳሩ ግን እግዚአብሔር ጣልቃ በመግባት ከእስራኤል የተመረጡትን በጸጋ ያድናቸዋል። መልእክቱ ገብርኤልም ይህንኑ በማብሰር ነው *«ብዎድርም ትቢያ ካንቀላፉት ብዙዎቹ ይነቃሉ፤ እኩሌቶቹም ወደ ዘላለም ሕይወት፥ እኩሌቶቹም ወደ እፍረትና ወደ ዘላለም ጉስቁልና።»* ሲል ከገለጸለት በኋላ በመቶጠልም በምድራዊ ሕይወታቸው ለእግዚአብሔር እገልጋይና ታዛዥ የሆኑት *«ጥበበኞቹም እንደ ሰማይ ፀዳል፥ ብዙ ለምችንም ወደ ጽድቅ የሚመልሱ እንደ ከዋክብት ለዘላለም ይደምቃሉ»* በሚል መልኩ ካሣቸውን በመንግሥተ ለማያት የሚከፈላቸው መሆኑን ያስታወቀው።

በትንቢተ ሆሴዕ

ይህን ጥናታችንን ከመደምደማችን በፊት ልንገነዘበው የሚያሻው ሌላ ጠቃሚ ነጥብ ክርስቶስ ከሙታን የሚነሳው በሦስተኛው ቀን ለመሆኑ እሁንም በዚሁ በብሉይ ኪዳን ውስጥ የተጠቀሰ መሆኑን ነው። ይህንንም ታላቅ ምሥጢር የሚያበሥርልን ነቢዩ ሆሴዕ ስለዚሁ ጉዳይ የሚከተሉትን ቃላት አስፍሮልናል፦ *«ኑ፥ ወደ እግዚአብሔር እንመለስ፤ እርሱ ሰብሮናልና፥ እርሱም ይፈውሰናልኛ፤ እርሱ መትቶናል፥ እርሱም ይጠግነናል። ከሁለት ቀን በኋላ ያድነናልኛ፤ በሦስተኛውም ቀን ያስነሣናል፥ በፊቱም በሕይወት እንኖራለን። እንወቅ፥ እናውቅም ዘንድ እግዚአብሔርን እንከተልኛ፤ እንደ ወገግታም ተዘጋጅቶ እናገኘዋለንኛ፤ እንደ ዝናብም ምድርን እንደሚያጠጣ፥ እንደ መጪረሻ ዝናብ ይመጣል።»* ሆሴዕ 6:1-3።

ይህ ትንቢት በቅድሚያ የሚናገረው ራሳቸውን በንስሐ ቦግጠብ ወደ እግዚአብሔር የመለሱትን እማኞች ነው። በመቀጠል ደግሞ «በሦስተኛውም ቀን ያስነሳናል» የሚል አባባል ሠፍሮ እናገኛለን። ምንም እንኳን ይህ ትንቢት በቀጥታ ስለ ክርስቶስ የተነገረ ቢሆንም፥ ዳሩ ግን በንስሐ ወደ እግዚአብሔር የሚመለሱትን ሁሉ የሚያጠቃልል ነው። የክርስቶስ ትንሣኤ ሁሉንም

አማኞች የሚያቅፍ ስመሆኑ ከሚከተሉት የአዲስ ኪዳን ጥቅሶች ስመገንዘብ እንችላለን፡፡

ሁሉም አማኞች በክርስቶስ ትንሣኤ ስለ መታቀፋቸው

በሮሜ 6:6 ላይ ጳውሎስ «*አሮጌው ሰውነታችን ከእርሱ ጋር እንደተሰቀለ፥ ...*» (ማለትም ከክርስቶስ ጋር) ካለ በኋላ እንደገና በገላትያ 2:20 ላይ ደግሞ፡- «*ከክርስቶስ ጋር ተሰቅዬአለሁ .... *» ሲል ጽፏል፡፡

ከእነዚህና ከሌሎችም የአዲስ ኪዳን ጥቅሶች በግልጽ የምንረዳው ክርስቶስ ራሱን ከእኛ ከኃጢአተኞች ጋር አንድ ያደረገ መሆኑን ነው፡፡ የእኛን ኃጢአት በመሸከሙ ሳቢያ እንደ ኃጢአተኛ ተቆጥሮ፥ ተከሶ ተወቅሶ የሞት ቅጣት ተፈጽሞበታል፡፡ እውነታው ይህ እስከሆነ ዘንዳ ደግሞ፥ ከእኛ ከአማኞች የሚጠበቀው በእምነት ራሳችንን ከክርስቶስ ጋር አንድ እንድናደርገው ነው፡፡ ይህንንም እስከፈጸምን ድረስ ክርስቶስን የምንመስለው በሞቱና በመቀበሩ ብቻ ሳይሆን፥ በትንሣኤውም ጭምር ይሆናል፡፡

ይህን ከክርስቶስ ጋር የመመሳሰላችንን ነገር አሁንም ጳውሎስ በኤፌሶን መልእክቱ 2:4-7 ላይ እንደሚከተለው አጉልቶ ገልጾታል፡- «*ነገር ግን ለእግዚአብሔር በምህረቱ ባለጠጋ ስለሆነ ከወደደን ከትልቅ ፍቅሩ የተነሳ በበደላችን ሙታን እንኳ በሆንን ጊዜ ከክርስቶስ ጋር ሕይወት ሰጠን፥ በጸጋ ድናችኋልና፥ በሚመጡ ዘመናትም በክርስቶስ ኢየሱስ ለእኛ ባለው ቸርነት ከሁሉ የሚበልጠውን የጸጋውን ባለ ጠግነት ያሳይ ዘንድ፥ ከእርሱ ጋር አስነሳን በክርስቶስ ኢየሱስም በሰማያዊ ሰፍራ ከእርሱ ጋር አስቀመጠን፡፡*»

ክርስቶስ የእኛን ኃጢአት ለማስተሰረይ ከመሞቱ ጋር ራሳችንን በእምነት አንድ አስካደረግን ድረስ፥ ወዲያውኑ በእግዚአብሔር ቀኝ ከተቀመጠው ክርስቶስ ጋር በድል አድራጊነት ስማችን ይመዘገባል፡፡ በሞቱ እርሱን መስሰናልና በትንሣኤውም ከርሱ ጋር አንድ እንሆናለን፡፡ ራሱም ጌታችን ለደቀ መዛሙርቱ ያረጋገጠላቸው ይህንኑ ስመሆኑ ከሚከተለው ዮሐንስ 14:19 እንረዳለን፡- «*... እኔ ሕያው ነኝና እናንተ ደግሞ ሕያዋን ትሆናላችሁ፡፡*» ስለዚህም ነው በትንቢተ ሆሴዕ 6:2 ላይ፥ «*በሦስተኛውም ቀን ያስነሳናል፥ በፊቱም በሕይወት እንኖራለን*» ተብሎ በሰፈረው ትንቢት ልናምንበት ግድ የሚሆነው፡፡ ይሁን እንጂ ይህን ዕድል ስመቀዳጀት አሁንም በዚሁ በትንቢተ ሆሴዕ እንደ ተጠቀሰው «ወደ እግዚአብሔር ልንመለስ እግዚአብሔርንም ልንከተል» ግድ ነው፡፡ ይህን አባባል የሚያጠናክርልን ደግሞ በትንቢተ ሚልክያስ 4:2 የሰፈረው የሚከተሰው ጥቅስ ነው፡- «*ነገር ግን ስሜን ለምትፈሩት ለእናንተ የጽድቅ ጸሐይ ትወጣላችኋለች፥ ፈውስም በክንፎቿ*

ውስጥ ይሆናል፡፡ እናንተም ትወጣላችሁ፥ እንደ ሰባም አምሳሳ ተፈነጫላችሁ፡፡»

መጨረሻው ልንገነዘበው የሚያሻው ሆሴዕ የክርስቶስን ትንሣኤ እንደምን ከመንፈስ ቅዱስ መውረድ ጋር እንዳያያዘው ነው፡- «*እንደ ዝናብም ምድርንም እንደሚያጠጣ እንደ መጨረሻ ዝናብ ይመጣል፡፡*» በዚህ ምንባብ ፊተኛና ኋለኛ ዝናብ ተብሎ የተመሰለው መንፈስ ቅዱስ ነው፡፡ የዚህን ትንቢት ፍጻሜ በአዲስ ኪዳን ተዘግቦ እናገኘዋለን፡፡ በጰንጠቆስጤ ዕለት ክጌታ ኢየሱስ ትንሣኤ ከአምሳ ቀናት በኋላ የእግዚአብሔርን የዕውቀት መንገድ ሲከተሉ ለነበሩት ደቀ መዛሙርት አዘነበላቸው፡፡ በዚህ ምዕራፍ የብሉይ ኪዳን ነቢያት ስለ ጻድቃን ትንሣኤ የተናሩትን ስንዳስስ ተመሳሳይ አሳብ ጎልቶ ይታያል፡፡ እርሱም በብሉይ ኪዳን ዘመን የነበሩ ቅዱሳን በትንሣኤ መካተታቸውን ነው፡፡

ሰምሳሉ ያህል እግዚአብሔር በመጀመሪያ ለአብርሃም ቀጥሎ ደግሞ ለዘሩ ከነዓንን የዘላለም ርስት አድርጎ እንደሰጣቸው አይተናል፡፡ ጳውሎስም ለክርስቲያኖች የሚከተለውን ተናግሯል፡- «*እናንተም የክርስቶስ ከሆናችሁ እንኪያስ የአብርሃም ዘር እንደ ተሰፋውም ቃል ወራሾች ናችሁ*» ገላትያ 3:29፡፡ በአዲስ ኪዳን የአብርሃም ዘር የሆኑትን በትንሣኤ አብርሃም ይቀድማቸዋል፡፡ ኢዮብም ስለ ራሱ የሚከተለውን ብሏል፡-«*እኔ ግን የሚቤዠኝ ሕያው እንደሆነ በመጨረሻም ዘመን በምድር ላይ እንዲቆም ይህ ቁርበቴም ከጠፋ በኋላ በዚያን ጊዜ ከሥጋዬ ተለይቼ እግዚአብሔርን እንዲይ አውቃለሁ*» ኢዮብ 19:25-26 በሚቤዠው ዘመታመኑ በጻድቃን ትንሳዔ እንደሚካፈል አምኗል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ ኢሳይያስ አርሱ ራሱ ስለሚካፈልበት ደስታ የታጀበ ትንሣኤ ተናግሯል፡፡ «*ሙታንህ ሕያዋን ይሆናሉ፡፡ ሬሳዎችም ይነሳሉ፡፡ በምድር የምትኖሩ ሆይ ጠልህ የብርሃን ጠል ነውና ምድር ሙታንን ታወጣለችና ንቁ ዘምሩም*» ኢሳ. 26:19፡፡ መልአኩ ገብርኤል ሰዳንኤል የጻድቃንና የኃጥአን ትንሣኤ እንዳስ ጠቁሞታል፡፡ ከዚህ በኋላ መልአኩ ሰዳንኤል ስራሱ «*አንተ ግን እስከ ፍጻሜው ድረስ ሂድ አንተም ታርፋለህ፤ በፃኑም መጨረሻ በሰባ ከፍልህ ትቆማለህ*» አለው ዳንኤል 12፡፡

ዘግልጽ እንደ ሰፈረው ዳንኤል በጻድቃን ትንሣኤ ይካፈላል፡፡ ሆሴዕም ትንሣኤን በተመለከተ በተናገረው ትንቢት እንዲህ ብሏል፡- «*ከሁለት ቀን በኋላ ያድነናል በሦስተኛውም ቀን ያስነሳናል፡፡ በፊቱም በሕይወት እንኖራለን፡፡*» ሆሴዕ 6:2፡፡ ሆሴዕ ራሱ በትንሣኤ እንደሚነሳ ተናግሯል፡፡ በተጨማሪ ግን የአዲስ ኪዳንን ማረጋጫ ስማግኘት የሚከተሉትን የጌታ ኢየሱስ ቃላት እናስተውል፡፡ «*እላችኋለሁ ብዙዎች ከምስራቅና ከምዕራብ ይመጣሉ ከአብርሃምና ከይስሐቅ ከያዕቆብም ጋር በመንግሥተ ሰማያት ይቀመጣሉ.....*» ማቴዎስ 8:11፡፡

ጌታ ኢየሱስ እንደተናገረው አማኞች ከተሰያየ አቅጣጫና የሕይወት ዘርፍ በትንሣኤ ከአብርሃም፥ ከይስሐቅና ከያዕቆብም ጋር ወደ አንድነት ይመጣሉ፡፡ ይህ የሚያሳየን በብሉይ ኪዳንና በአዲስ ኪዳን የነበሩ አማኞች በጻድቃን ትንሣኤ ይካፈላሉ፡፡

በዚህ ትንሣኤ የሚካፈሉ ሁሉ አንድ የጋራ ባሕርይ አላቸው፣ አርሱም በክርስቶስ የማዳን መስዋዕትነት ያላቸው እምነት ነው። ሆኖም ግን በአርጌውና በአዲሱ ታል ኪዳን ውስጥ ባሉት ቅዱሳን መካከል ልዩነት አለ። በብሉይ ኪዳን አማኞች በተለያየ ትንቢታዊ መገለጦች ወደ ፊት ሲመለከቱ ያልቀረበ መስዋዕትን ያዩ ነበር። በአዲስ ኪዳን ግን አማኞች የክርስቶስ ሞትና ትንሣኤን የሚያሳዩ ታሪካዊ እውነታዎችን የኋልዮሽ በመመልከት ነው።

በሚቀጥሉት ጥናቶቻችን የምናካሂደው፣ የጻድቃን ትንሣኤ፣ የብሉይ ኪዳን አማኞችንና የአዲስ ኪዳንን ቅዱሳኖች እንደሚያካትት በመረዳት ነው።

ለዚህ ተጨባጭ የሆነውን ማስረጃ የምናገኘው በአዲስ ኪዳን ውስጥ እንደተገለጸው የመንፈስ ቅዱስ በዕለተ ጰንጠቆስጤ መውረድ ነው። ይህም ተፈጻሚነት ያገኘው ከክርስቶስ ትንሣኤ ከሃምሳ ቀናት በኋላ ለመሆኑም ሌላው ልናጤነው የሚገባ ነጥብ ነው።

44

ክርስቶስ አርአያችን (ክርስቶስ የትንሣኤ በኩር)

ባለፈው ምዕራፍ ውስጥ ልዩ ትኩረት በመስጠት የተከታተልነው በብሉይ ኪዳን ውስጥ ትንሣኤን በማስመልከት ስለተነገሩት ትንቢቶች ነው። ከዚያም ትምህርታችን ሦስት ፍሬ ነገሮችን እንደጨበጥን እርግጠኛ ነኝ። ከነዚህም የመጀመሪያው፡- እንደምን ክርስቶስ ራሱ ሞትን ድል አድርጎ እንደሚነሣ፣ ሁለተኛ፡- በክርስቶስ የሚያምኑ ሁሉ እነርሱም በትንሣኤ እንደሚነሱና ሦስተኛ፡- ታጥአንም ስፍርድ ይቀርቡ ዘንድ በተመሳሳይ ሁኔታ የሚነሱ መሆናቸውን ነው።

ወደ አዲስ ኪዳን ብንመጣም በእነዚህ በሦስት ፍሬ ሐሳቦች ላይ ከብሉይ ኪዳን ያልተለየ መልዕክት ስፍሮ እናገኛለን። ከዚህም በተጨማሪ በአዲስ ኪዳን ውስጥ አንዳንድ ጠለቅ ያሉ ማብራሪያዎች ለፍረው እናገኛለን።

የትንሣኤ ሦስት ተከታታይ ገጽታዎች

በዚህ ክፍለ ትምህርታችን መግቢያ የምናደርገው በዮሐንስ 5:25 ላይ ጌታችን ራሱ የተናጋራቸውን ቃላት በመጥቀስ ይሆናል፦ *«እውነት እውነት እላችኋለሁ፤ ሙታን የእግዚአብሔርን ልጅ ድምፅ የሚሰሙበት ሰዓት ይመጣል አርሱም አሁን ነው፤ የሚሰሙትም በሕይወት ይኖራሉ።»*

ከዚህም በመቀጠል በዚሁ ምዕራፍ በቁጥር 28 እና 29 ላይ ጌታችን እንደገና የሚከተሉትን ቃላት እንደ ተናገረ እናስተውላለን፦ *«በመቃብር ያሉቱ ሁሉ ድምፁን የሚሰሙበት ሰዓት ይመጣል፤ መልካምም ያደረጉ ለሕይወት ትንሣኤ፤ ክፉም ያደረጉ ለፍርድ ትንሣኤ ይወጣሉ፤ በዚህ አታድንቁ።»*

ጌታችን በእነዚህ ሁለት ጥቅሶች ውስጥ፤ «ሙታን» እና «በመቃብር ያሉት ሁሉ» በሚሉት ሁለት ገለጻዎች መጠቀሙን እንመለከታለን። ከዚህም በመነሳት በበኩላችን ልንደርስበት የምንችለው ድምዳሜ፤ ጌታችን «ሙታን» በማለት የጠቀሳቸው የሞቱትን ሳይሆን በመንፈስ የሞቱትን ሲሆን፤ ይህም በጳውሎስ የኤፌሶን መልእክት 2:1 ላይ እንደሚከተለው ቀርቦ እናገኛለን፦ *«በዘይሳችሁና በኃጢአታችሁ ሙታን ነበራችሁ....»*

እንግዲህ ከዚህ አጭር ማብራሪያ የምንረዳው ጳውሎስ የሚናገረው በአካል ስለ ሞቱት ሳይሆን ሕያዋን ሆነው ዳሩ ግን በኃጢአት ለተዘዘሉት ነው። እንደገናም ጳውሎስ በኤፌሶን 5:14 ላይ እነዚህን ሙታን በሚከተለው መልኩ ሲጠቅሳቸው እናያለን፦ *«ስለዚህ አንተ የምትተኛ ንቃ፤ ከሙታንም ተነሳ፤ ክርስቶስም ያበራልሃል፤ ይላል።»* ከዚህ በመነሳት ጌታችን በዮሐንስ 5:35 ላይ የተናገረው ስለ እንደዚህ ዓይነቶቹ ሰዎች ለመሆኑ መረዳቱ አይከብደንም፦ *«እውነት እውነት እላችኋለሁ፤ ሙታን የእግዚአብሔርን ልጅ ድምፅ የሚሰሙበት ሰዓት ይመጣል አርሱም አሁን ነው የሚሰሙትም በሕይወት ይኖራሉ።»*

ጌታ ኢየሱስ የእግዚአብሔርን ልጅ ድምፅ የሚሰሙበት ሰዓት ይመጣል ማለቱ የወንጌልን በመላው ዓለም መሰበክ የሚያበሥር ሲሆን የምሥራቹን ቃል ሰምተው ያመኑበት ኃጢአታቸው ይቅር እንደሚባልላቸውና ዘላለማዊውንም መንግሥት እንደሚወርሱ ተገልጽዋል። ይህን አባባል በዮሐንስ 5:28-29 ላይ እንደሚከተለው ከሠፈረው ጋር ስናነጻጽረው ልዩነት አንዳለው እንረዳለን። *«በመቃብር ያሉት ሁሉ ድምፁን የሚሰሙበት ሰዓት ይመጣል፤ መልካምም ያደረጉ ለሕይወት ትንሣኤ ክፉም ያደረጉ ለፍርድ ትንሣኤ ይወጣሉና፤ በዚህ አታድንቁ።»* ይህ ጥቅስ ቀደም ሲል ከሰፈረው በሦስት ዋና ዋና ነገሮች ይለያል ይኸውም፦ እንደኛ፦ «ድምፁን የሚሰሙበት ሰዓት ይመጣል» የሚለው ሐረግ ሲጠቀስ ቀደም ባለው ጥቅስ ውስጥ ግን፤ *«... የእግዚአብሔርን ልጅ ድምፅ የሚሰሙበት ሰዓት ይመጣል አርሱም አሁን*

ነው።» በሚል ሁኔታ ተብራርቶ እናያለን። ስለዚህ የሁለተኛው ጥቅስ ትንቢት መሉ በሙሉ መፈጸሙን ጊዜ የሚያመለክት ስለ መሆኑ ለመረዳት እንችላለን።

ሁለተኛ፦ አሁንም በሁለተኛው ጥቅስ ውስጥ «በመቃብር ያሉት» የሚለው ሐረግ መጠቀሱን እንመለከታለን፦ ይህም እንግዲህ ያለ ጥርጥር የሚያመለክተው በሥጋ ሞተው ወደ ተቀበሩት ነው። በፊተኛው ምንባብ ድምፁን የሚሰሙት በክፉል ሲሆን በዚህኛው ግን በመቃብር ያሉት ሁሉ ይሰሙታል።

ሦስተኛ፦ በሁለተኛው ጥቅስ ውስጥ «ለፍርድ ትንሣኤ» የሚል ሐረግ እናያለን። ስለዚህ ይህም እንደገና የሚያመለክተው ከመቃብር እንደሚነሱ ነው።

ስለዚህ ከዚህ ንጽጽር በአጭሩ ለመደምደም የምንችለው፤ ጌታችን በመጀመሪያው ጥቅስ የተናገረው በኃጢአት ስለ ሞቱት ሲሆን በሁለተኛው ግን ሥጋዊ ሞትን ስለ ቀመሱት መሆኑን ነው።

በሁለተኛው ምንባብ ኢየሱስ ስለ ሁለት የተለያዩ የትንሣኤ ዓይነቶች ይናገራል። አንደኛ፤ የሕይወት ትንሣኤ ሁለተኛ፤ የፍርድ ትንሣኤ። ይህም በዘሌይ ኪዳን በትንቢተ ዳንኤል 12:1-3 ከተገለጸው ጋር ይስማማል።

«በዚያም ዘመን ስለ ሕዝብህ ልጆች የሚቆመው ታላቁ አለቃ ሚካኤል ይነሳል።[1] ሕዝብም ከሆነ ጀምሮ እስከዚያ ዘመን ድረስ እንደ እርሱ ያለ ያልሆነ ያመከራ ዘመን ይሆናል። በዚያም ዘመን በመጽሐፉ ተጽፎ የተገኘው ሕዝብህ ሁሉ አያንዳንዱ ይድናል። በምድርም ትቢያ ውስጥ ካንቀላፉቱ ብዙዎች ይነቃሉ። እነኩሌቶቹ ወደ ዘላለም ሕይወት እኩሌቶቹም ወደ እፍረትና ወደ ዘላለም ንስቅልና። ጥበበኞችም እንደ ሰማይ ወዳል ብሩ ሰዎችንም ወደ ጽድቅ የሚመልሱ እንደ ከዋክብት ለዘላለም ይደምቃሉ።»

ዘሁለቱም አገላለጽ፤ ትንሣኤው ሁለት ደረጃዎች አሉት። እነርሱም የጻድቃንና የሙታን ናቸው። በተጨማሪም ጌታ ኢየሱስ በዳንኤል ያልተገለጠ አንድ እውነትን ሲናገር እናያለን። ሙታንን ወደ ትንሣኤ የሚጠራው ድምፅ የእግዚአብሔር ልጅ የሆነው ክርስቶስ ራሱ መሆኑን ነው።

ከዚህ በመቀጠል ደግሞ በ1ኛ ቆሮንቶስ 15:22-24 ላይ ትንሣኤን በማስመልከት የሚከተለው ሐሳብ እንደሠፈረ እናያለን፦ *«ሁሉ በአዳም እንደሚሞቱ እንዲሁ ሁሉ በክርስቶስ ደግሞ ሕያዋን ይሆናሉና። ነገር ግን አያንዳንዱ በራሱ ተራ ይሆናል፤ ክርስቶስ እንደ በኩራት ነው። በኋላም በመምጣቱ ለክርስቶስ የሆኑት ናቸው። በኋላም መንግሥቱን ለእግዚአብሔር ለአባቱ አሳልፎ በሰጠ ጊዜ ኃይልንም ሁሉ ሥልጣንን ሁሉ ጌይልንም ሁሉ በሻረ ጊዜ ፍጻሜ ይሆናል።»*

ጳውሎስ «እያንዳንዱ በራሱ ተራ ይሆናል» ሲል መጥቀሱ በሚከተሉት ሦስት ዋና ዋና ምክንያቶች መሆኑን እንረዳለን። የመጀመሪያው የትንሣኤ ባለ ተራ ራሱ ክርስቶስ ሲሆን ይህም በኩርነቱን የሚያረጋግጥልን ነው። በሁለተኛ ደረጃ ባለተራ የሚሆኑት ደግሞ ከምድራዊ ኃጢአታቸው በእምነት በመዳን የክርስቶስ ወገን የሆኑት አማኞች ናቸው። በመጨረሻ የሚነሱት ግን ክክርስቶስ የሺህ ዘመን ግዛት በኋላ መንግሥቱንና ሥልጣኑን ለአባቱ በሚያስረክበበት ወቅት የሚነሱትንና ለፍርድ የሚቀርቡትን የሚመለከት ነው።

በዚህ ወቅት ከሚነሱት አብዛኛዎቹ በዳንኤልና በጌታ በኢየሱስ አስቀድመው እንደ ተናገረ ዕድል ፈንታቸው በሙታን ትንሣኤ ነው። ሦስተኛውን በተመለከተ ጳውሎስ በ1ኛ ቆሮንቶስ ብዙ አይናገርም። ነገር ግን በራዕይ 20 ላይ ያሉትን ተጨማሪ ማብራሪያዎች እናያለን። አስክዚያ ድረስ የመጀመሪያዎቹን ሁለቱን በተመለከተ ጳውሎስ የተናገረውን እንመርምር።

የክርስቶስ ምሳሌነት (የበኩራት አምሳልነት)

ጳውሎስ የክርስቶስን ትንሣኤ የመከር በኩራትን ለእግዚአብሔር ከማቅረብ ጋር ያመሳስለዋል። ይህንንም በቀላሉ ለመረዳት ያስችለን ዘንድ ስለዚህ መስዋዕት አቀራረብ በኦሪት ዘሌዋውያን ያስፈረውን ሥነ ሥርዓታዊ መመሪያ እንጠቅሳለን።

«እግዚአብሔርም ሙሴን እንዲህ ብሎ ተናገረው፦ ለእስራኤል ልጆች እንዲህ ብለህ ንገራቸው ወደ ምሰጣችሁ ምድር በገባችሁ ጊዜ፥ መከሩንም ባጨዳችሁ ጊዜ የእናንተን መከር በኩራት ነዶ ወደ ካህኑ አምጡ እነርሱም ነዶውን በእግዚአብሔር ፊት እንዲሰምርላችሁ ይወዝውዘው በማግሥቱ ከሰንበት በኋላ ካህኑ ይወዝውዘው።» ዘሌዋውያን 23:9-11 ይህ በጥቅሱ ውስጥ የሰፈረው የሚወዘወዘው በኩራት ነዶ የክርስቶስ ምሳሌ ነው። ስለ ምን ስለ ሰው ልጆች ኃጢአት የቀረበው መስዋዕት እርሱ ነውና።

ይህንን በማጠናከር ነው ጳውሎስ በሮሜ 4:25 *«ስለ እኛም ነው እንጂ፥ ስለ በደላችን አልፎ የተሰጠውን እኛን ስለ ማፅደቅም የተነሳውን ጌታችንን ....»* ሲል የተናገረው የክርስቶስ ትንሣኤ ያረጋገጠው የጌታን ጻድቅነት ብቻ ሳይሆን በእርሱ ለሚያምኑ ሁሉ በእግዚአብሔር ፊት ከክርስቶስ ጋር ጻድቅ ሆነው እንዲቆጠሩ አድርጓል።

ከዚህ በተጨማሪ የበኩራት ነዶ የሚወዘወዘው በሰንበት ማግስት ነበር። ሰንበት የሳምንቱ ሰባተኛ ቀን በመሆኑ ቀን የሳምንቱ የመጀመሪያ ቀን ይሆናል። ይህ ደግሞ ጌታ ከሞት የተነሳበት ዕለት ነው። በመጨረሻም የበኩራት ነዶው ድልንና አምልኮን ያመለክታል። ምክንያቱም የበኩራት መገኘት መከሩ በሰላም እንደሚሰበሰብ ያሳያል። በተመሳሳይ መልኩ ጌታ ኢየሱስ ከሙታን በኩር ሆኖ መነሳቱ ቀሪዎቹ ሙታን በትንሣኤ እንደሚነሱ ዋስትና ነው። ከዚህ ጋር

አብሮ በብሉይ ኪዳን ስለ ክርስቶስ ትንሣኤ የተነገረ አንድ ትንቢታዊ መገለጥ አለ።

በዚሁ ዘመክር በኩራት መሥዋዕትነት ላይ ልንመለከተው የሚገባው ሌላ ጥቅስ በሉቃስ 12:24 ላይ የሰፈረውን ነው። በዚህም ጥቅስ ጌታችን እንደምን ራሱን ከተዘራ የእህል ፍሬ ጋር በማመሳሰል እንዳነጻጸረው እናያለን፦ *«አውነት እውነት እላችኋለሁ፥ የስንዴ ቅንጣት በምድር ወድቃ ካልሞተች ብቻዋን ትቀራለች። ብትሞት ግን ብዙ ፍሬ ታፈራለች።»*

ይህን በእህል ዘር የተመሰለውን የክርስቶስ ትንሣኤ በመንፈሳዊው ዓለም ወስደን ስንመለከተው እጅግ ከፍ ያለ ትርጉም ያለው ሆኖ እናገኘዋለን። ይኸውም ክርስቶስ የተቀበረው ብቻውን ቢሆንም ዳሩ ግን በትንሣኤው አማካይነት ለመላው የሰው ዘር ቤዛ መሆኑን ነው። ጌታ በመስቀል ላይ ባይሞት ኖሮ በአገልግሎቱ ፍሬ ባልታየም ነበር። በመሞቱ፥ በመቀበሩና ከሙታን በመነሳቱ ብቻ ነው ከእግዚአብሔር ጋር በመታረቅ የጸደቁትን የኃጢአተኞች መክር ፍሬ ያገኘው። ይህ ስደቀ መዛሙርቱ ያቀረበውን የስንዴ ዘር ምሳሌ በምድር ውስጥ መሞት መቀበርና ፍሬ ማፍራት እውነት የተናገረው ራሱ ጌታ ኢየሱስ ነው።

ምንም እንኳ አንድ የስንዴ ዘር ብትዘራም ስትበቅል ግን አንድ ፍሬ ብቻ ሳትሆን ብዙ ፍሬ ያላት ተክል ትሆናለች። ጌታ ኢየሱስ በዘረው ምሳሌ እንደ ገለጸው አንዲ ስንዴ የምታፈራው ሠላሳ፣ ስልሳ ወይም መቶ ፍሬዎችን ሊሆን ይችላል።

ይህ የተፈጥሮ ሕግ በክርስቶስ ትንሣኤም ውስጥ ይሠራል። ጌታ ኢየሱስ የተቀበረው ብቻውን ነው ሲነሳ ግን ብቻውን አልነበረም። ይሁን እንጂ ይህን መስለን ታላቅ ዕድል በወቅቱ የነበሩት የአይሁድ ካህናትና አጋሮቻቸው አላጤኑትም ነበር። ስለ ክርስቶስ በመስቀል ላይ ተሰቅሎ መሞትና ከዚያም በኋላ ስለነበረው ሁኔታ ማቴዎስ በ27:50-53 ላይ የሚከተለውን አስፍሮልናል፦ *«ኢየሱስም ሁለተኛ በታላቅ ድምጽ ጮኸ፥ ነፍሱንም ተወ። እነሆም የቤተ መቅደስ መጋረጃ ከላይ እስከ ታች ከሁለት ተቀደደ፤ ምድርም ተናወጠች፥ ዓለቶችም ተሰነጠቁ፥ መቃብሮችም ተከፈቱ፥ ተኝተው ያንቀላፉትም ብዙ ሥጋዎች ተነሡ። ከትንሣኤውም በኋላ ከመቃብሮች ወጥተው ወደ ቅድስት ከተማ ገቡና ለብዙዎች ታዩ።»*

ምንም እንኳን እነዚህን ሁሉ ድርጊቶች በማከታተል በአንድ ዓረፍተ ነገር ውስጥ የተጠቃለሉ ቢሆንም ዳሩ ግን የተከናወኑት ክርስቶስ በክርስ መቃብር ለቆየባቸው ሦስት ቀናት ውስጥ ነበር። ክርስቶስ ተሰቅሎ የሞተው ከአይሁድ ሰንበት ቀደም ብሎ ባለው ቀን ማለትም በዕለተ አርብ ሲሆን የተነሣው ደግሞ አሁንም ለአይሁድ የመጀመሪያው ቀን በሆነው በዕለተ አሁድ ነበር። ሙታንም መቃብራቸውን ፈንቅለው የተነሡት ከክርስቶስ ትንሣኤ በኋላ ለመሆኑ፥ *«... ከትንሣኤውም በኋላ (ስለጌታችን ትንሣኤ) ከመቃብሮች*

ወጥተው ወደ ቅድስት ከተማ ገቡና ለብዙዎች ታዩ።» በማለት ግልጽ አድርጎልናል። ስለዚህ ከዚህ በመነሣት ለመደምደም የምንችለው፥ በመክር በኩራት የተመለሰው የክርስቶስ ትንሣኤ ተፈጻሚነት ማግኘቱን ነው። እንደዚሁም ክርስቶስ ብቻውን ሳይሆን አያሌዎችንም ከርሱ ጋር ከመቃብር ለማስነሳቱ የተረጋገጠ ይሆንልናል።

ሌላው አስገራሚ ነጥብ ደግሞ ማቴዎስ *«... ከመቃብሮች ወጥተው ወደ ቅድስት ከተማ ገቡና ለብዙዎች ታዩ።»* በማለት ከክርስቶስ ጋር በትንሣኤ ስለ ተነሡት የብሉይ ኪዳን ዘመን ጻድቃን የተረከው ነው። እንግዲህ ይህ ማለት እነዚህ ጻድቃን ከትንሣኤ የተቀዳጁትን እካል ክርስቶስ ከትንሣኤው በኋላ ከለዘለዓለሙ ጋር አንድ ዓይነት ነበረ ማለት ነው። መቃብሮቹ የተከፈቱበትን ሰዓት አናውቅም። የተነገረን ነገር ጌታ ኢየሱስ ቀሞት ከተነሳ በኋላ መነሳታቸውን ነው። በዚህ መንገድ በብሉይ ኪዳን የነበረው የበኩራት ምሣሌ በክርስቶስ ሙሉ በሙሉ ተፈፅሟል። ክርስቶስ የተቀበረው ብቻውን ነበር፤ ከሞት ሲነሣ ግን ብቻውን አልነበረም። ብዙዎች ከእርሱ ጋር ተነስተዋል። የሞትን፥ የሲያልንና የለይጣንን ሽንፈት ለማወጅ እንደሚወዛወዘው ነዶ በኩራት በመሆን ለአማኞች ትንሣኤ ዋስትና ሆነዋል።

ከክርስቶስ ጋር ስለ ተነሱት የብሉይ ኪዳን ቅዱሳን የሚነሱ ሁለት ጥያቄዎች አሉ። የመጀመሪያው «ከሞት የተነሱት በብሉይ ኪዳን የነበሩት ቅዱሳንን ያጠቃልላል ወይ? በብሉይ ኪዳን የነበሩት ቅዱሳን ሁሉ ተነስተዋል ወይ? ለዚህ ጥያቄ መልሱ አይደለም ነው። ምክንያቱም ማቴዎስ «ብዙ ሥጋዎች ተነሡ» ማለቱ ሁሉም አለመነሳታቸውን ያመለክታል። ይህን መደምደሚያ ጴጥሮስ በሐዋርያት ሥራ 2:29 ላይ በዕለተ ጰንጠቆስጤ አስረግጦታል። *«ወንድሞች ሆይ ስለ አባቶች አለቃ ስለ ዳዊት እንደ ሞተም እንደ ተቀበረም ለእናንተም በግልጥ እናገር ዘንድ ፍቀዱልኝ መቃብሩም እስከ ዛሬ በእኛ ዘንድ ነው።»* ከሞት አልተነሳም ነበር። ስለዚህ በመጀመሪያው ትንሣኤ የተነሡት የብሉይ ኪዳን ቅዱሳን ሁሉ ሳይሆኑ የተወሰኑት ብቻ ናቸው።

ሁለተኛው ጥያቄ «ከተነሱ በኋላ ምን ሆኑ? የሚለው ነው? እንደ ተነገረን እነዚህ ለእንዲና ለመጨረሻ ጊዜ አገልግሎቱ ካስነሳቸው ይሰያል። ከሞት መልሰ ወደ ሕይወት ከመምጣት በፊት ይመሩት የነበረውን ዓይነት ሕይወት እንዲኖሩ አድርጓቸዋል። እንደገና ለሞት ኃይልና ስለሥጋ ድክም የተጋለጡ በመሆናቸው በጊዜ ርዝመት ሞተው ተቀብረዋል። ወደ ምድራዊ ሕይወት ተመለሱ እንጂ ዳግመኛ ላይሞቱ ትንሣኤን አላገኙም። በሌላ መልኩ ከጌታ ኢየሱስ ጋር ከሞት የተነሱት ከእርሱ ጋር ትንሣኤን አግኝተዋል። ወደ አዲስ ሕይወት መጥተዋል። ጌታ ኢየሱስ ያለውን ዓይነት አዲስ መንፈሣዊ አካል አግኝተዋል ማቴዎስ 27:53። *«ተንሥተው ከነበሩትም ከትዱሳን ብዙ ሥጋዎች ተነሡ ከትንሣኤውም በኋላ ከመቃብሮች ወጥተው ወደ ቅድስት ከተማ ገቡና ለብዙዎች ታዩ።»*

እነዚህ ቃላት እንደሚያመለክቱት ቅዱሳኑ ክርስቶስ ከትንሣኤው በኋላ የነበረውን ዓይነት እካል ነበራቸው። በፈለጉት ጊዜ የመታየትና ደግሞም የመሰወር ችሎታ እላቸው። ለምድራዊው ሥጋ ውስንነት ተገዥነታቸው አከተመለት። ይህ ከሆነ ደግሞ እንደገና ወደ መቃብር ወርደው መበስበስ እንደማያስፈልጋቸው ግልጽ ነው። ትንሣኤ የተላበሰ እካልን ይዘው ለእንዲና ለመጨረሻ ጊዜ ከሞት በመነሣታቸው ደግሞ ወደ መቃብር አይወርዱም። ከትንሣኤ በኋላ እነዚህ ቅዱሳን ምን ሆኑ? የአዲስ ኪዳን መጻሕፍት ለዚህ ጥያቄ ቁርጥ ያለ መልስ አይሰጡንም። ሆኖም ግን ትንሣኤውን በመሰለ ትንሣኤ ከተነሱ ከእርሱ ጋር አብረው ማረጋቸውን መገመት ይቻላል። እስኪ ጌታ ስለ ማረጉ የሚነግሩንን ምንባቦች እንቃኛቸው። የሐዋርያት ሥራ 1:9 *«ይህንም ከተናገረ በኋላ እነርሱ እያዩት ከፍ ከፍ አለ ደመናም ከዓይናቸው ሰውሮ ተቀበለችው።»* ጌታ ወደ ሰማይ ካረገ በኋላ በሄደበት እኳኋን ተመልሶ እንደሚመጣ መላዕክት ለደቀ መዛሙርት ተገልጠው ዋስትና ለጥተዋቸዋል። የሐዋርያት ሥራ 1:11 *« የገሊላ ሰዎች ሆይ ወደ ሰማይ እየተመለከታችሁ ስለ ምን ቆማችኋል? ይህ ወደ ሰማይ የወጣው ኢየሱስ ወደ ሰማይ ሲሄድ እንዲያችሁት እንዲሁ ይመጣል አሉአቸው።»* ይህ የሚያሳየው በኢየሱስ ወደ ሰማይ ማረግና ዳግም ምፅአት መካከል መመላለል መኖሩን ነው። ሲሄድ እንዲያችሁት እንዲሁ ይመጣል። ይህ ምን ያመለክተናል? ማርቆስ 13:26 እና ሉቃስ ምንባቦችም እንደሚጠቁሙት ጌታ የሚመጣው በደመና ነው። ዘካርያስ 14:5 እና ይሁዳ 14 ላይ ጌታ ከቅዱሳን ጋር እንደሚመጣ ተጽፏል።

እነዚህን ሁለት ምንባቦች በማጣመር «ክርስቶስ በደመና ከቅዱሳን ጋር» እንደሚመጣ እንገነዘባለን። በተጨማሪም የጌታ ዕርገት ዳግም ምጽአት እንደሚመሳሰሉ እናውቃለን። ጌታ በደመና እንደተነጠቀ በደመና እንደሚመጣ የሚናገረውን ተመሳሳይ እከያ ስንፈልግ ቅዱሳንን ይዞ በደመና እንደሚመጣ ሁሉ ቅዱሳንም ከእርሱ ጋር አብረው ማረጋቸውን እናያለን።

ይህም ከሆነ በክርስቶስ ዳግም ምፅአት ጊዜ ከእርሱ ጋር አብረው እንደሚመለሱ የተገገረላቸው ቅዱሳን እነርሱ ናቸው ማለት ነው። ጳውሎስም በ1ዎን በሰብራውያን 12:1-2 ላይ፥ *«እንግዲህ እነዚህን የሚያህሉ ምስክሮች እንደ ደመና ዙሪያችን ካሉልን፤ እኛ ደግሞ ሸክምን ሁሉ ቶሎም የሚለጠንን ኃጢአት አስወግደን፥ የእምነታችንንም ራስና ፈጻሚውን ኢየሱስን ተመልክተን፥ በፊታችን ያለውን ሩጫ በትዕግሥት እንሩጥ።* እርሱ ነውርን ንቆ በፊቱም ስላለው ደስታ *በመስቀል ታግሦ በእግዚአብሔር ዙፋን ቀኝ ተቀምጦአልና።»* ሊል የጻፈው የቅዱሳንን ከክርስቶስ ጋር መገኘት በማብሠር ነው። እኛም የዘመኑ ምዕመናን በእነዚህ መሰሎች የብሉይ ቅዱሳን የተከበብን መሆናችንን በማጤን ይበልጥ ከኃጢአታችን ነፅተን ክርስቶስን ለመምሰል ልንጥር ይገባል።

«እነዚህ እንደ ደመና በዙሪያችን ያሉት ምስክሮች» ብሎ የዕብራውያን ጸሐፊ የሚጠራልን አነማንን ነው? ዓውደ ምንባቡን ስናጤነው በምዕራፍ 11 የተዘረዘሩትን የእምነት አርበኞች ያመለክተናል። በዘመኑ የእምነትን ሩጫ ለማሮጥ ክርስቲያን በብሉይ ኪዳን የነበሩ ቅዱሳን እንደ ደመና ምስክሮች ሆነው

ከበውታል። በዚህ መንገድ የደመና ምሳሌ ለብሉይ ኪዳን ቅዱሳን መገለጫ ሆኖ እናገኘዋለን።

እስከ አሁን እንዳየነው ጌታ ወደ ሰማይ ባረገ ጊዜ ከእርሱ ጋር ዝምት የተነሡትን የብሉይ ኪዳን ቅዱሳን ይዟቸው በደመና ማረጉ መጽሐፍ ቅዱሳዊና አግባብ ያለው ነው። በብሉይ ኪዳን የነበረው የበኩራት ምሳሌ ትንሣኤውና እርገቱ ሙሉ በሙሉ ተፈጽሟል ማለት ነው። ይህ ደግሞ የዳግም ምጽአቱ ተስፋ ዋስትና ነው። ሆኖም ግን ይህ ድምዳሜ እንደ ቤተ ክርስቲያን ዶክትሪን (ትኖና) የሚለፍር ሳይሆን በቅዱሳት መጻሕፍት የተነገሩትን በማነፃፀር የተደረሰበት ማጠቃለያ ነው።

45

የክርስቶስ ዳግም ምፅአትና ለእርሱ የተመረጡ አማንያን

ባለፈው ምዕራፍ ውስጥ በመጠኑም ቢሆን ለመዳሰስ የሞከርነው የትንሣኤ በኩራት ስለ ሆነው ክርስቶስ በአዲስ ኪዳን ውስጥ የተገለፀው ሁሉ እንደ ምን ከብሉይ ኪዳኑ የመከር በኩራት ጋር እንደሚመሳሰል ነው። በመቀጠል ደግሞ አሁንም ሐዋርያው ጳውሎስ በ1ኛ ቆሮንቶስ 15:23 ላይ «... *በኋላም በመምጣቱ ለክርስቶስ የሆኑት ናቸው*» ሲል ስለተናገረላቸው እናያለን።

የእውነተኛ አማኝ መለያዎች

የክርስቶስ ዳግም ምጽአት በቅድሚያ ቤተ ክርስቲያንን በማስመልከት ይሆናል። ይኸውም ራሷ እንደ ሙሽራ እርሱም እንደ ሙሽራ ሆነው የሚገናኙ በመሆናቸው ነው። ቀጥሎም ደግሞ ክርስቶስ የእርሱ የሆኑትን ፍለጋ የሚመጣ ከመሆኑ ላይ ነው። እንደዚህ መሰሎቹ ክርስቲያኖች ከእንግዲህ የማንም ሳይሆኑ የክርስቶስ ንብረቶች ናቸው። ስለዚህም መሰሉ ዕድል የበቁት ልዩ ማኅተም የሚታተምባቸው ስለመሆኑ ጳውሎስ በ2ኛ ጢሞቴዎስ 2:19 ላይ እንደሚከተለው ገልጾታል:- «*ሆኖም ጌታ ለእርሱ*

የሆኑትን ያውቃል፥ ደግሞም የጌታን ሰም የሚጠራ ሁሉ ከዓመፃ ይራቅ የሚለው ማኅተም ያለበት የተደላደለ የእግዚአብሔር መሠረት ቆሞአል።»

በቅድሚያ ለእርሱ የሆኑትን የሚያውቅ ጌታ ራሱ ብቻ ነው። ሆኖም ግን ውጪያዊ አካሄዳቸው አንድ የጋራ ገጽታ አለው። ይኸውም «ከአመጻ መራቅ» ነው። ይህን ውጪያዊ ማኅተም (ከአመጻ መራቅ) የሌለው ማናቸውም ሰው ጌታ የእርሱ እንደሆኑ ከተናገረላቸው መካከል አይደለም። ስለ እነዚህ ሰዎች ተጨማሪ መለያ አሁንም ጳውሎስ በገላትያ 5:24 የሚከተለውን ነጥብ አስፍሮልናል፦ *«የክርስቶስ ኢየሱስም የሆኑት ሥጋን ከክፉ መሻቱና ከሥሮቱ ጋር ሰቀሉ።»* ስለዚህ ለዓለሚዊ ምቾትና ድሎት የሚያደሉ፥ ብሎም ራሳቸውን ለብልጠትና ወንድሞቻቸውን ለመነዳት የማይመለሱ ሁሉ ያን መለሱን ማኅተም የማግኘት ዕድል አያኖራቸውም ማለት ነው።

ክርስቶስ የሚመጣው እንደ ሌባ ነው። የሚመጣውም ለመሰረቅ ሳይሆን የእርሱ የሆኑትን ብቻ ሊወስድ ነው። ይህንን በአእምሯችን ይዘን በዳግም ምጽአት ጊዜ የሚፈፀሙትን ዋና ዋና ክንውኖች እንዳስሳለን።

የክርስቶስ ዳግም ምጽአት የመጽሐፍ ቅዱስን ትንቢቶች ከያዙት ምዕራፎች አንዱና ተቀዳሚው ነው ለማለት ይቻላል። አንዳንድ ሊቃውንት በጥናት ደረስንበት እንዲመሉትም ከሆነ ስለ ክርስቶስ ሥጋ ሆኖ ወደ ምድር መምጣት ከተነገሩት ትንቢቶች የዳግም ምጽአቱ ትንቢቶች በአምስት እጥፍ እንደሚበልጡ ነው።

የክርስቶስ ዳግም ምጽአት ለተለያዩ ዓላማዎች ስለመሆኑ አሁንም በመጽሐፍ ቅዱሳችን ውስጥ ተዘርዝሮ የምናገኘው ነው። እግዚአብሔር በዘላለም ምክሩ በዳግም ምጽአቱ የሚከናወኑ ብዙ ነገሮች አሉ። ምንም እንኳ ከእግዚአብሔር ጥቅል ዕቅድ ጋር የተያያዙ ቢሆንም ዓላማዎቹ አንዱ ከሌላው የሚለዩበት ነገር አለ። እያንዳንዳቸው ግን ትልቁ ትኩረታቸው ከመጻሕፍት የክርስቶስን ዳግም ምጽአት በተመለከተ የተናገሩት ላይ ነው። ዘመቀጠልም የምናተኩረው በነዚህ ነጥቦች ላይ ነው።

አምስቱ የክርስቶስ ዳግም ምጽአት ዓላማዎች

አምስቱ የክርስቶስ ዳግም ምጽአት ዋና ዋና ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው። አንደኛ፦ ክርስቶስ ሙሽራው የሆነችውን ቤተ ክርስቲያንን ፍለጋ ይመጣል። ይህም ማለት ደግሞ ክርስቲያኖችን ማለት ሲሆን ከእነርሱም ጋር እንድም በንጥቀት፥ አለበለዚያም በትንሣኤ አንድ ይሆናሉ። ኢየሱስ ራሱ ስለዚሁ ተስፋ በዮሐንስ 14:3 ላይ የሚከተለውን ቃል ኪዳን ለደቀመዛሙርቱ ገብቷል፦ *«እኔ ባለሁበት እናንተ ደግሞ እንድትሆኑ ሁለተኛ እመጣለሁ። ወደ እኔም እወስዳችኋለሁ።*

ሁለተኛ፦ ክርስቶስ እስራኤልን ለማዳን ይመጣል። ይኸውም በእርሱ በማመን ከታላቁ የመከራ ዘመን በሕይወት ያመለጠትን እስራኤላውያን የሚመለከት ሲሆን፥ ለዚህ በማስረገጫነት የምንጠቅሰው ደግሞ አስቀድሞ በኢሳይያስ የተተነበየው ተስፋና ጳውሎስ በሮሜ 11:26-27 የጠቀሰውን ይሆናል፦ *«እንደዚሁም እስራኤል ሁሉ ይድናል፥ እንዲህ ተብሎ እንደ ተጻፈ፦ መድኃኒት ከጽዮን ይመጣል ኃጢአትን ያስወግዳል። ኃጢአታቸውንም ስወስድላቸው ከእነርሱ ጋር የምገባው ኪዳን ይህ ነው።»*

ሦስተኛ፦ ክርስቶስ ሐሰተኛ ክርስቶስንና ራሱን ሰይጣንን ለማስወገድ ይመጣል። *«በዚያን ጊዜም ጌታ ኢየሱስ በአፉ መንፈስ የሚያጠፋውን፥ ሲመጣም በመገለጡ የሚሽረው ዓመጸኛ ይገለጣል»* 2ተሰሎንቄ 2:8።

አራተኛ፦ ክርስቶስ በአሕዛብ መንግሥታት ላይ ለመፍረድ ይመጣል። ስለዚህ ደግሞ ራሱ ትንቢት ተናግሯል። *«የሰው ልጅ በክብሩ በሚመጣበት ጊዜ ከእርሱም ጋር ቅዱሳን መላዕክት ሁሉ በዚያን ጊዜ በክብሩ ዙፋን ይቀመጣል። አሕዛብም ሁሉ በፊቱ ይሰበሰባሉ፤ እረኛም በጎቹን ከፍየሎቹ እንደሚለይ እርስ በእርሳቸው ይለያቸዋል»* ማቴዎስ 25:31-32።

አምስተኛ፦ ክርስቶስ በምድር ላይ የሺህ ዓመት መንግሥቱን ለመመሥረት ይመጣል። ይህም የሚቴዎስ 25ን ምንባብ የሚያጠቃልል ሲሆን በኢሳይያስ 24:23 ትንቢት ተነግሯል። *«የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔርም በጽዮን ተራራና በኢየሩሳሌም ላይ ይነግሣልና፥ በሽማግሌዎቹም ፊት ክብር ይሆናልና፤ ጨረቃ ይታወክል ጸሐይም ያፍራል።»* በትንቢተ ዘካርያስ 14:9 ላይ ደግሞ የሚከተለው ትንቢት ተነግሯል፦ *«እግዚአብሔርም በምድር ሁሉ ላይ ይነግሣል፤ በዚያን ቀን እግዚአብሔር አንድ ስመ ም አንድ ይሆናል።»*

እንደዚሁም ክርስቶስ በምድሪቱ ስለሚነግሥበት የሺህ ዓመት ግዛቱ በራዕይ 20 ላይ የሚከተለው ተዘግቦ እናገኛለን። *«ዘፋኖችንም አየሁ፥ በእነርሱም ላይ ለተቀመጠ ዳኝነት ተሰጣቸው፤ ስለ ኢየሱስም ምስክርና ስለ እግዚአብሔር ቃል ራሶቻቸው የተቆረጠባቸውን ሰዎች ነፍሳት፥ ለአውሬውና ለምስሉም ያልሰገዱትን ምልክቱንም በግምባራቸው በእጆቻቸው ላይ ያልተቀበሉትን አየሁ፥ ከክርስቶስም ጋር ሺህ ዓመት ኖሩና ነገሡ።»*

ክርስቶስ ዳግም የሚመጣበት አምስት ዓላማዎች እንደሚከተለው እናጠቃልላቸዋለን

1. ክርስቶስ እውነተኛ አማኞችን ሊወስድ ለቤተክርስቲያን ይመጣል።
2. ለእስራኤል ደህንነት ይመጣል።
3. ሐሰተኛውን ክርስቶስንና ሰይጣንን ሊያስወግድ ይመጣል።
4. በአሕዛብ መንግሥታት ላይ ለመፍረድ ይመጣል።
5. በምድር ላይ የሺህ ዓመት መንግሥቱን ሊመሰርት ይመጣል።

የክርስቶስን ዳግም ምፅአት ለምን ዓላማ እንደ ሆነ በአጭሩ የተመለከትን ሲሆን በመቀጠል ደግሞ ስለ አማኞች ትንሣኤና መነጠቅ በአጭሩ እንዳስሳለን።

የክርስቶስን ዳግም ምፅአት ዓላማዎችን በተመለከተ በመጽሐፍ ቅዱስ አማኞች መካከል ስምምነት ቢኖርም የሌሎቹን አመጣጥ በተመለከተ ግን ብዙ ውይይትና አንዳንዱም አለመግባባት ይታያል። አነዚህ ሁሉ ዓላማዎች የሚፈጽሙት ክርስቶስ ሲመጣ በአንዱ ነው ወይም በመሐከላቸው የጊዜ ልዩነት ይኖራል? ይህ ከሆነ ደግሞ ቅደም ተከተሉ እንዴት ነው? አንዳንዶቹ ተደራርበው ይሆን የሚፈጸመት? በዚህ ጥናታችን አሳስፈላጊና አጨቃጫቂ ጥያቄዎችን እንነካቸውም። ከክርስቶስ ዳግም ምፅአት ጋር የተያያዘውን የጻድቃንን ትንሣኤ ብቻ እንዳስሳለን።

የአማኞች መነጠቅና ትንሣኤ

ጳውሎስ በ1ኛ ተሰሎንቄ 4:13-18 ላይ፥ ክርስቲያኖች እንደምን ክርስቶስን በዳግም ምፅአቱ ጊዜ እንደሚቀበሉት በማብራራት ጽፏል፦ *«ነገር ግን ወንድሞች ሆይ ተስፋ እንደሌላቸው እንደ ሌሎች ደግሞ እንዳታዝኑ፥ አንቀላፍተው ስላሉት ታውቁ ዘንድ እንወዳለን። ኢየሱስ እንደሞተና እንደተነሣ ካመንን እንዲሁም ዘኢየሱስ ያንቀላፉትን እግዚአብሔር ከርሱ ጋር ያመጣቸዋልና ዘጌታ ቃል የምንላችሁ ይህ ነውና እኛ ሕያዋን ሆነን ጌታ እስኪመጣ ድረስ የምንቀር ያንቀላፉትን እንቀድምም። ጌታ ራሱ በትዕዛዝ በመላዕክትም አለቃ ድምፅ በእግዚአብሔርም መለከት ከሰማይ ይወርዳልና፥ በክርስቶስም የሞቱ አስቀድመው ይነሣሉ፥ ከዚያም በኋላ እኛ ሕያዋን ሆነን የምንተረው ጌታን በአየር ለመቀበል ከእነርሱ ጋር ደመና እንነጠቃለን። እንደዚሁም ሁልጊዜ ከጌታ ጋር እንሆናለን። ስለዚህ እርስ በእርሳችሁ በዚህ ቃል ተጽናኑ።»*

የዚህ የጳውሎስ መልዕክት ተቀዳሚ ዓላማ ዘመድ አዝማድ የሞተባቸውን ክርስቲያኖች ለማጽናናት ነው። እነዚህም ሰዎች በክርስቶስ አምነው እስከሞቱ ድረስ በትንሣኤ ለመነሳታቸው የማያጠራጥር መሆኑን ለመግለጽ በሕይወት ያሉትን ሐዘን እንዳይለማቸው ያበረታታቸዋል። የሙታንንም ትንሣኤ በማስመልከት ጳውሎስ ሦስት ደረጃዎች እንደሰጠው እናያለን። በቅድሚያ ትንሣኤን የሚያውጁ ሦስት የተሰያዩ ድምጾች ይሰማሉ። የመጀመሪያው የሚሰማው ድምጽ የጌታችን የራሱ ድምጽ ሲሆን ይህም በዮሐንስ 5:28-29 ላይ፥ *«በመቃብር ያሉት ሁሉ ድምጹን የሚሰመበት ሰዓት ይመጣልና፤ መልካምም ያደረጉ ለሕይወት ትንሣኤ ክፉም ያደረጉ ለፍርድ ትንሣኤ ይወጣሉና በዚህ አትደነቁ»* ሲል በተናገረው መሠረት የሚፈጸም ይሆናል።

ከዚህ በመቀጠል የሚሰሙት ድምጾችም የመላዕክት አለቃ ድምጽና የእግዚአብሔር መለከት ድምጾች የተባሉት ናቸው። የመላእክት አለቃ የተባለው በአመዛኙ ብሥራትን በመናገር የታወቀው ገብርኤል ሲሆን እንደሚቸል ሲታመን፥ የመለከቱ መነፋት ዓላማ ደግሞ ለእግዚአብሔር ወገኖች የተሰበሰቡ ጥሪ ለማስተላለፍ ነው።

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንደምናየው የመለከት ዋና ጥቅም በአስቸጋሪ ጊዜ የእግዚአብሔርን ሕዝብ በአንድነት ለመሰብሰብ ነው። በዚህ ወቅት የመለከቱ ድምጽ የእግዚአብሔር ሕዝብ ከሰማይ እነርሱን ለመገናኘት ወደ ወረደው ወደ እግዚአብሔር በአንድነት መሰብሰባቸውን ያመለክታል። በተመሳሳይ ሁኔታም በምድር ላይ ሁለት ነገሮች ተፈፃሚነትን ያገኛሉ። በቅድሚያ የሞቱት አማኞች በትንሣኤ ሲነሱ በመቀጠል ደግሞ በሕይወት ያሉት በቅጽበተ ዓይን ለማያዊ አካልን ይለብሳሉ። ከዚህ በኋላ እነዚህ የአማኞች ስብስባ ማለትም ከሞት የተነሱትና በመለወጥ ለማያዊ አካልን የለበሱ በአንድነትና በቅጽበት በእግዚአብሔር መለኮታዊ ኃይል ከምድር ወደ ለማይ ይነጠቃሉ። በደመና ይነጠቃሉ። በዚያም ከጌታ ጋርና እርስ በእርሳቸውም ይገናኛሉ። ከዚህ ክስተት በኋላ ጌታና የተቤዣቸው አማኞች ለዘለዓለም በአንድነትና በማይበጠስ ህብረት ይኖራሉ።

እዚህ ላይ ጳውሎስ በዚህ ምንባብ ውስጥ የተጠቀመባቸውን ሁለት የግሪክ ቃላት ልዩ ትርጉምን አስፈላጊነት እናያለን። ጳውሎስ (እንነጠቃለን) ብሎ ሲናገር የተጠቀመበት የግሪክ ግስ ሃርፖዞ (harpazo) ሲሆን ይህም የሚያመለክተው ድንገተኛ በቅጽበት የሆነና ኃይለኛ አያያዝን ነው። ይህ ቃል በአዲስ ኪዳን ውስጥ አራት ጊዜ በጥቅም ላይ የዋለ ሲሆን የሚገልጠውም ሰዎች ወደ ለማይ መነጠቃቸውን ነው።

በተጨማሪ ይህ ቃል በሐዋርያት ሥራ 8:39 ላይ በጥቅም ላይ የዋለ ሲሆን «የጌታ መንፈስ ፊልጶስን ነጠቀው» ሲል እናገኛለን። ኢየሱስ በዮሐንስ 10:12 ላይ የበጎችን በተኩላዎች «መነጠቅ» ለማሳየት ተጠቅሞበታል: አንደገናም በማቴዎስ 13:19 ላይ በመንገድ ዳር የተዘራውን ዘር ወፎች አንደሚነጥቁት ለማመልከት ተጠቅሞበታል። በይሁዳ ቁጥር 23 ላይ ለዎችን ከእሳት ለመታደግ ይህ ቃል በጥቅም ላይ ዋለ።

በተለምዶ የመጽሐፍ ቅዱስ መተርጎሙን ሃርፖዞን በንጥቀት ይተረጉሙታል። በእርግጥም ንጥቀት የሃርፖዞን መሠረታዊ ትርጉም የያዘ ነው። ጳውሎስ ይህንን ቃል የተጠቀመው የአንድን ቅጽበታዊ ድንገተኛና ኃይለኛ ድርጊት ስሜት ለመስጠት በማሰብ ነው። ይህ ድርጊት በተለይ የሚያመለክተው የሌባን ድርጊት ነው።

ለምሳሌ በራዕይ 16:15 ላይ ራሱ ጌታ *«እነሆ እንደ ሌባ ሆኜ እመጣለሁ...»* ሲል የገለጸው ሲሆን በማቴዎስ 24:42-43 ላይ ደግሞ የሚከተለውን ብሏል፦ *«ጌታችሁም በምን ሰዓት እንዲመጣ አታውቁምና*

እንግዲህ ንቁ ያን ግን እወቁ ባለቤት ከሌሊቱ በየትኛው ክፍል ሌባ እንዲመጣ ቢያውቅ ኖሮ፤ በነቃ ቤቱም ሊቆፈር ባልተወም ነበር።»

እርግጥ የጌታንና የቀማኛ ሌባን አመጣጥ ልናመሳስለው አይገባም። ስለምን ጌታ የሚወስደው የራሱ የሆኑትንና በደሙ መፍለስ የዋጃቸውን ብቻ ሲሆን፤ ሌባ ግን የሌላውን ንብረት ስለሚዘርፍ ነው።

በሌላም በኩል በዚያን ወቅት ሞትን ያልቀመሱ አማኞች ከመቅጽበት በመቀየር ጌታን ለመቀበል ወደ ሰማይ ይነጠቃሉ። ይህንንም በማስመልከት ጳውሎስ በ1ኛ ቆሮንቶስ 15:51-52 ላይ እንዲከተለውን ይነግረናል፦ *«እነሆ፤ አንድ ምሥጢር እነግራችኋለሁ፤ ሁላችን ልናንቀላፋም ነገር ግን የኋለኛውም መለከት ሲነፋ ሁላችን በድንገት በቅጽበት ዓይን እንለወጣለን፤ መለከት ይነፋልና ሙታንም የማይበሰብሱ ሆነው ይነሳሉ እኛም እንለወጣለን።»* መለወጣችንም በምን ረገድ እንደሚሆን በማብራራት ጳውሎስ ሰውጡ በምንለብሰው አዲስ አካል ብቻ ላይሆን ዘላለማዊነትንም በመቀዳጀት ጭምር ስለ መሆኑ ያበስረናል።

ምስክሮችና ሰማዕታት

በራዕይ 11 ላይ በመጨረሻው የመከራ ዘመን ከጥልቁ በሚወጣው አውሬ በሰማዕትነት ስለሚያልፉ ስለ ሁለቱ ምስክሮች እናነባለን። *«ለወገኖችና ለነገዶችም ለቋንቋዎችም ለአሕዛብም የሆኑ ሰዎች ሦስት ቀን ተኩል በድናቸውን ይመለከታሉ። በድናቸውም ወደ መቃብር ሊገባ አይፈቅዱም። እነዚህም ሁለት ነቢያት በምድር የሚኖሩት ስላሠቃዩ በምድር የሚኖሩት በእነርሱ ላይ ደስ ይላቸዋል፤ በደስታም ይኖራሉ እርስ በርሳቸውም ስጦታ ይለጣጣሉ። ከሦስቱ ቀን ተኩል በኋላም ከእግዚአብሔር የወጣ የሕይወት መንፈስ ገባባቸው በእግሮቻቸውም ቆሙ፤ ታላቅም ፍርሃት በሚመለከቱት ላይ ወደቀባቸው። በሰማይም ወደዚህ ውጡ የሚላቸውን ታላቅ ድምፅ ሰሙ፤ ጠላቶቻቸውም እየተመለከቱአቸው ወደ ሰማይ በደመና ወጡ።»* ከዚህ ሐተታ በግልጽ የምንረዳው ሰዎቹ ትንሣኤን የተቀዳጁ ስመሆናቸው ነው። ይኸውም የመቀበር ዕድል ባያገኙ እንኳን ሰዎች ከሞቱ ከሦስት ቀናት በላይ ቢሆናቸውም በጠላቶቻቸው ፊት ወደ ሰማይ ስማረጋቸው ተረጋግጧል።

ከዚህም በመቀጠል ራዕይ 20:4-6ን ስንመለከት ስለ እነዚህ ለማዕታት ተጨማሪ ማብራሪያ ተሰጥቶበት እናገኛለን፦ *«ዙፋኖችንም አየሁ፤ በእነሱም ላይ ለተቀመጡት ዳኝነት ተሰጣቸው፤ ስለ ኢየሱስም ምስክርና ስለ እግዚአብሔር ቃል ራሶቻቸው የተቆረጡባቸውን ለሰዎች ነፍሳት፤ ለአውሬውና ለምስሉም ያልሰገዱትን ምልክቱንም በግምባራቸው በእጆቻቸውም ላይ ያልተቀበሉትን አየሁ፤ ከክርስቶስም ጋር ሺህ ዓመት ኖሩና ነገሡ። የቀሩቱ ሙታን ግን ይህ ሺህ ዓመት እስኪፈጸም ድረስ በሕይወት አልኖሩም። ይህ የፊተኛው ትንሣኤ*

ነው። በፊተኛው ትንሣኤ ዕድል ያለው ብፁዕና ቅዱስ ነው፤ ሁለተኛው ሞት በእነርሱ ላይ ሥልጣን የለውም፤ ዳሩ ግን የእግዚአብሔርና የክርስቶስ ካህናት ይሆናሉ፤ ከእርሱም ጋር ይህን ሺህ ዓመት ይነግሣሉ።»

እነዚህ በታላቁ የመከራ ዘመን የመሥዋዕትነትን ሞት የሚቀበሉ ለማዕታት ከክርስቶስ ጋር ለሺህ ዓመት እንደሚነግሡ መገለጹን ተመልክተናል። ይህ ተፈጻሚ የሚሆነው በመጀመሪያው ትንሣኤ ወቅት ለመሆኑ ዮሐንስ በግልጽ አስፍሮታል።

እንግዲህ ክርስቶስ ትንሣኤ አንስቶ በታላቅ መከራ ወቅት እስከሚፈጸም እስከዚህ እስከ ምስክሮችና ለማዕታት ትንሣኤ ድረስ ያለው (የመጀመሪያው ትንሣኤ) በመባል ስታወቅ ይህንን ዕድል የተቀዳጁት ሁሉ ብፁዓንና ቅዱሳን ተብለው ስመጠራት የበቁ ይሆናሉ።

ለማጠቃለልም ይህንን የመጀመሪያውን ትንሣኤ በአራት በመክፈል ልናየው እንችላለን፦ አንደኛ፦ የትንሣኤ በኩራት የሆነውን የክርስቶስን ትንሣኤ ተከትለው ከሞት ለመነሣት የበቁት የብሉይ ኪዳን ቅዱሳን፤ ሁለተኛ፦ በክርስቶስ በማመን ጸንተው የቆዩ ክርስቲያን አማኞች ክርስቶስን በዳግም ምፅአቱ ወቅት በደመና ለመቀበል ከሞት የሚነሡበትና የሚነጠቁበት፤ ሦስተኛ፦ በታላቁ መከራ ወቅት የሁለቱ ምስክሮች ለሦስት ቀናት ተኩል ላይቀበሩ ከቆዩ በኋላ ከሞት በመነሣት ወደ ሰማይ ማረግ፤ አራተኛ፦ በመከራው ዘመን ማብቂያ ላይ የሁሉም የመከራው ዘመን ለማዕታት ትንሣኤና፤ ከክርስቶስም ጋር በምድር ለሺህ ዓመታት መንገሥና በአሕዛብ ላይ መፍረድ ናቸው።

ከዚህ በመቀጠል ደግሞ የመጨረሻውን የትንሣኤ ገጽታ እንመለከታለን።

46

የመጨረሻው ዘመን

አሁን ደግሞ የትንሣኤውን የመጨረሻ ትዕይንት እናያለን። ጳውሎስ እንዳመሰከተው የእውነተኛ አማኞች ትንሣኤ የዓለምን ፍፃሜ ይቀድማል። «በክርስቶስም የሞቱ አስቀድመው ይነሣሉ።» ክዚህ በኋላም በሚከተለው የሺህ ዓመት መንግሥት ጋር አብሮ ይሄዳል።

የዓለም ፍጻሜ በክርስቶስ የሺህ ዓመቱ የምድር አገዛዝ ማብቂያ ላይ የሚከሰት ስመሆኑ ጳውሎስ በ1ኛ ቆሮንቶስ 15:23-27 ላይ እንደሚከተለው አስፍሮታል።

«ነገር ግን እያንዳንዱ በራሱ ተራ ይሆናል፤ ክርስቶስ እንደ በኩራት ነው፤ በኋላም በመምጣቱ ለክርስቶስ የሆኑ ናቸው። በኋላም መንግሥቱን ለአባቱ ለእግዚአብሔር አሳልፎ በሰጠ ጊዜ አለቅነትም ሁሉና ሥልጣንን ሁሉ ኃይልንም በሻረ ጊዜ፤ ፍጻሜ ይሆናል። ጠላቶቹን ሁሉ ከእግሩ ቢታች እስኪያደርግ ድረስ ሊነግሥ ይገባዋልና። የኋለኛው ጠላት የሚሻረው ሞት ነው፤ ሁሉን ከእግሩ በታች እስገዝቶአልና።»

በሺህ ዓመቱ ማብቂያ ላይ ክርስቶስ ለአንድ ሺህ ዓመት በምድር ከነገሠ በኋላ እግዚአብሔር አባቱ ጠላቶቹን ሁሉ ከእግሩ ሥር ያስገዛለታል። ከነዚህም ጠላቶቹ የመጨረሻው ሞት ይሆናል። ክዚያም በኋላ ክርስቶስ መንግሥቱንና ሥልጣኑን ለአባቱ በማስረከብ እንደ ልጅነቱ አራሱን በአባቱ

ሥር ያደርጋል። ይህንንም የሚገልጽልን ጥቅስ 1ኛ ቆሮንቶስ 15:28 ነው። *«ሁሉ ከተገዛለት በኋላ ግን እግዚአብሔር ሁሉ በሁሉ ይሆን ዘንድ በዚያን ጊዜ ልጁ ራሱ ደግሞ ሁሉን ላስገዛለት ይገዛል።»*

ይህን የዘመን ፍጻሜ ትንቢታዊ ሥዕል ስናጠና፤ በእግዚአብሔር አብና በእግዚአብሔር ወልድ መካከል ያለውን ፍጹም ሕብረት እንመለከታለን። በመጀመሪያ እግዚአብሔር አብ በሺህ ዓመት ጊዜ ወልድ (ክርስቶስ) በእርስ እንደተሾመ ሁሉን እንዲገዛና እንዲያስተዳድር ፈቀደ። በሺህ ዓመቱ መንግሥት ፍጻሜም አብ ጠላቶቹን ሁሉ ለክርስቶስ ያስገዛለታል። የመጨረሻውም ጠላት ሞት ይሆናል። ክርስቶስም አብ ያስገዛለትንና ራሱን ጭምር ለአብ ሥልጣን ያስገዛል። በዚህ መንገድ ይላል ጳውሎስ እግዚአብሔር አብ ክርስቶስ «ሁሉ በሁሉ» ይሆናል።

ይህም የመጨረሻው የሥልጣን ርክክብ እግዚአብሔር ሰፍጥረቱ ላዘጋጀው ዕቅድ ማጠናቀቂያ ይሆናል። የዚህንም አፀብ ድንቅ የእግዚአብሔር ዓላማ አስመልክቶ ጳውሎስ በኤፌሳን 1:9-10 ላይ የሚከተለውን ይነግረናል፦ *«በክርስቶስ ለማድረግ እንደወደደው እንደ አሳቡ፤ የፈቃዱንም ምሥጢር አስታውቆናልና፤ በዘመን ፍጻሜ ይደረግ ዘንድ ያለውን ሁሉ በክርስቶስ ለመጠቅለል ነው።»*

ይሁን እንጂ ይህን የእግዚአብሔር ዕቅድ ለማስናከል ስይጣን አንድና የመጨረሻውን መከራውን እንደሚያደርግ በዮሐንስ ራዕይ 20:7-10 ላይ እንደሚከተሰው ተገልጽዋል፦ *«ሺህም ዓመት ሲፈጸም ለይጣን ከእስራቱ ይፈታል በአራቱም በምድር ማዕዘን ያሉትን አሕዛብ ጎግንና ማጎግን፤ እንዲያስታቸው ለሰልፍም እንዲያስከትታቸው ይወጣል። ቁጥራቸውም እንደ ባሀር አሸዋ የሚያህል ነው። ወደ ምድርም ሰፋት ወጡ፤ የቅዱሳንንም ሠፈርና የተወደደችውን ከተማ ከበቡ፤ እሳትም ከሰማይ ከእግዚአብሔር ዘንድ መርዳ በላቻቸው። ያሳታቸውም ዲያብሎስ እውሬውና ሐሰተኛው ነቢይ ወዳለበት ወደ እሳትና ወደ ዲን ባሀር ተጣሉ፤ ለዘላለምም እስከ ዘላለም ቀንና ሌሊት ይሰቃያሉ።»*

ዮሐንስ በዚህ ራዕዩ ውስጥ «የቅዱሳን ሠፈር» እና «የተወደደችውም ከተማ» ዘማለት የገለጻት በሺህ ዓመቱ የክርስቶስ ግዛት ዘመን ዋና ከተማ የምትሆነውን ኢየሩሳሌምን ነው። በዚህን ጊዜ ሰይጣን በጥልቁ ውስጥ ታስሮ ይቆያል። ነገር ግን በፍጻሜው ላይ አሕዛብን ለአመፅ አንዲገፋፋ ይለቀቅና አመፁም ኢየሩሳሌምን ለማጥቃት በሚደረግ መክራ ይጠናቀቃል። እግዚአብሔር ጣልቃ በመግባት እሳትን ከሰማያት ያዘንባል። አመፅ መሉ በሙሉ ይደመሰሳል። ሰይጣንም በእሳት ባህር ይጣላል። በዚያም ከሐሰተኛው ነቢይ ጋር ሰዘለዓለም ይሰቃያል። ሁለቱም ወደ እሳት ባህር የሚጣሉት ጌታ በተመሰበትና የሺህ ዓመት መንግሥቱን በጀመረ ጊዜ ነው።

የመጨረሻ ትንሣኤ

ከዚህ በመቀጠል ዮሐንስ የሚገልጽልን ስለ መጨረሻው ትንሣኤ ሲሆን ይህንንም በራዕይ 20:11-15 ላይ እንደሚከተለው አስፍሮታል፦ *«ታላቅና ነጭ ዙፋንን በእርሱም ላይ የተቀመጠውን አየሁ፥ ምድርና ሰማይም ከፊቱ ሸሹ ሥፍራም አልተገኘላቸውም። ሙታንንም ታናናሾችንና ታላላቆችን በዙፋኑ ፊት ቆመው አየሁ፥ መጻሕፍትም ተከፈቱ፤ ሌላ መጻሕፍም ተከፈተ እርሱም የሕይወት መጽሐፍ ነው። ሙታንም በመጻሕፍት ተጽፎ እንደነበረ እንደ ሥራቸው መጠን ተከፈሉ። ባሕርም በእርሱ ውስጥ ያሉትን ሙታን ሰጠች፥ ሞትና ሲኦልም በእነርሱ ዘንድ ያሉትን ሙታን ሰጡ፥ እያንዳንዱም እንደ ሥራው መጠን ተከፈለ። ሞትና ሲኦልም በእሳት ባህር ውስጥ ተጣሉ። ይህም የእሳት ባህር ሁለተኛው ሞት ነው። በሕይወትም መጽሐፍ ተጽፎ ያልተገኘው ማንኛውም በእሳት ባሕር ውስጥ ተጣለ።»*

ከዚህ ቅደም ተከተል እንደምንረዳው ትንሣኤ የሚፈጸመው በመጀመሪያ ነው። ከዚያ ፍርድ ይከተላል። ይህ መመሪያ በትንሣኤው የተለያዩ ደረጃዎች ሲፈጸም ይታያል። ሰዎች ክፉም ሆነ መልካም የሚያደርጉት በሥጋቸው ስለሆነ እንደ ሥራቸው ተገቢውን ፍርድ ለመቀበል በእግዚአብሔር ፊት የሚቆሙት በሥጋቸው ነው። ቀደም ሲል እንዳየነው በክርስቶስ ያመኑቱ ከሺህ ዓመት መንግሥት በፊት ይነሳሉ። ይህ የብሉይ ኪዳንንና የአዲስ ኪዳንን ቅዱሳን ያጠቃልላል። በሺህ ዓመት መንግሥት ማብቂያ ላይ የሚነሱት ሳያምኑ በኃጢአታቸው የሞቱት ናቸው።

ከዚህ ጋር በተያያዘ መልኩ ዮሐንስ በሺህ ዓመት መንግሥት ማብቂያ ላይ የሚነሱትን «ሙታን» ብሎ ይጠራቸዋል። እንዲህ ብሏልና «ሙታንንም ታናናሾችንና ታላላቆችን በዙፋኑ ፊት ቆመው አየሁ።» ይህ አገላለጽ የጻድቃንን ትንሣኤ ለመግለጽ ከተጠቀመባቸው ቃላቶች ይለያል። እነርሱን በተመለከተ ያለው የሚከተለውን ነው *«ከክርስቶስም ጋር ሺህ ዓመት ኖሩና ነገሡ።»* ራዕይ 20:4።

ትንሣኤ ስላገኙት ቅዱሳን ዮሐንስ የሚነግረን መነሳታቸውን ብቻ ሳይሆን በሕይወት መኖራቸውንና በትንሣኤም ሙሉ በሙሉ (በመንፈስም በሥጋም) ሕይወት ማግኘታቸውን ነው። ከዚህ ውጪ ግን ሺህ ዓመቱ ሲፈጸም የተነሱት አሁንም ሙታን ናቸው። አካላቸው ከመቃብር ቢወጣም በመንፈላቸው ግን ሙት ናቸው። በኃጢአት ሞተው ከእግዚአብሔር መገኘት ርቀው ከእርሱ ጋር ያላቸው ኅብረት ተቋርጧል። በእግዚአብሔር ፊት የቀረቡት ለመጨረሻ ጊዜ ፍርዳቸውን ለመስማት ነው።

ከዚህ በኋላ ፍጻሜያቸው የእሳት ባሕር ነው። «ሁለተኛ ሞት» እርሱም የመጨረሻውና የዘላለም ቅጣት የሆነው ከእግዚአብሔር ርቀው ለመለወጥም ሆነ ለመመለስ ተስፋ የሌለው ጥፋት ነው።

ከእነዚህ ሁሉ መጽሐፍ እንደሚናገር መልሰው ወደ ሕይወት የሚመጡና የማይፈረድባቸው በሁለት ምድብ የሚከፈሉ ሰዎች አሉ። ከእነዚህም አንዷ ንግሥት አዜብና በጌታ ኢየሱስ የተጠቀሱት የነነዌ ሰዎች ናቸው (ሉቃስ 11:31-32)።

«ንግሥት አዜብ ከዚህ ትውልድ ሴቶች ጋር ተነሥታ ትፈርድባቸዋለች። የሰለሞንን ጥበብ ለመስማት ከምድር ዳር መጥታለችና እነሆም ከሰለሞን የሚበልጥ ከዚህ አለ። የነነዌ ሰዎች በፍርድ ከዚህ ትውልድ ጋር ተነስተው ይፈርዱበታል። በዮናስ ስብከት ንስሐ ገብተዋልና። እነሆም ከዮናስ የሚበልጥ ከዚህ አለ።»

ከላይ ባየናቸው ምሳሌዎች የዚህ ትውልድ ሰዎች (በክርስቶስ በኩል የቀረበላቸውን ምህረት የገፉ) ከሞት የሚነሱ ለኩነኔ ነው። ከእነርሱ ጋር ከተነሱት በፍርድ ቀን ምህረትን የሚቀበሉ አሉ። እነርሱም ንግሥተ አዜብና የነነዌ ሰዎች ናቸው።

ከብሉይ ኪዳን ቅዱሳን በተለየ መልኩ እነዚህ ሁለት ቡድኖች የክርስቶስን መሰዋዕትነት መገለጥ በትንቢትና በጥላነት (በምሳሌነት) እንደተናገረው ስላልተገለጠላቸው አምነው ደህንነት ማግኘት አይችሉም።

በመጨረሻም ክርስቶስ ዳግም በሚመጣበት ጊዜ ትንሣኤን አያገኙም። ለተገለጠላቸው ውስን ብርሃን ምላሽ በመስጠታቸው ግን በሺህ ዓመት መንግሥት ማብቂያ ላይ ከኩነኔ ነጻ ወጥተው የትንሣኤ ሕይወት ያገኛሉ።

እንደ ንግሥተ አዜብና እንደነነዌ ሰዎች ዓይነት ሌሎች ሰዎች ይኖሩ ይሆን? ካሉ እነማን ናቸው? ስንት ናቸው? ለዚህ ጥያቄ መልስ የምናገኘው ሁሉን አዋቂ ከሆነው ከእግዚአብሔር ብቻ ነው። አንድ ግልጽ ነገር ግን አለ። የክርስቶስን ወንጌል ሰምተው ያልተቀበሉት ሁሉ ለዘላለም ከእግዚአብሔር ምህረት ርቀው እንደሚጋባቸው ነው።

ሁለተኛ ምድብ ውስጥ የሚካተቱና በኋለኛው ትንሣኤ ከኩነኔ የሚያመልጡት ክርስቶስ በሺህ ዓመት መንግሥት በምድር ላይ ሲኖር የሞቱት ጻድቃን ናቸው። ይህንን የሺህ ዓመት መንግሥት በተመለከተ የሚከተለውን ትንቢታዊ ቃል በኢሳይያስ 65:20 ላይ እናገኛለን። *«ከዚያም ወዲያ ጥቂት ዘመን ብቻ የሚኖር ሕፃን ወይም ዕድሜውን ያልፈጸመ ሽማግሌ አይገኝም። ጎልማሳው የመቶ ዓመት ሆኖት ይሞታልና። ኃጢአተኛውም የመቶ ዓመት ሆኖት የተረገመ ይሆናልና።»*

ኢሳይያስ በዚህ ምንባብ የሚያመለክተን በሺህ ዓመት መንግሥት የምድር ላይ ኑሮ የቱንም ያህል የሰው ዕድሜ ቢራዘምም ጻድቃንና ኃጥአን ለሥጋዊ ሞት ተገዢ መሆናቸውን ነው። ከዚህ መደምደም የምንችለው ብሺህ ዓመት መንግሥት የሚሞቱት ጻድቃን በዘመኑ ማብቂያ ላይ እንደሚነሱ ሲሆን አብረዋቸው ከሚነሱት ኃጥአን ጋር ግን የእግዚአብሔር ፍርድ

አይሆንባቸውም። ወደ ራዕይ 20 ገልጠን በዮሐንስ ስለ ትንሣኤ ፍጻሜ የሚያወራውን ሙሉ ስዕል ማየት እንችላለን። ራዕይ 20:13 *«ባሕርም በእርሱ ውስጥ ያሉትን ሙታን ሰጠ ሞትና ሲያልም በእነርሱ ዘንድ ያሉትን ሙታን ሰጡ እያንዳንዱም እንደ ሥራው መጠን ተከፈለ።»*

ከእነዚህ በስተቀር የተቀሩት ሙታን በተመሳሳይ ጎራ ይመደባሉ። በዚህ ውስጥ እያንዳንዱን ሰው ያካትታል። ማንም የሚቀር የለም። በእግዚአብሔር የተፈጠረው ዓለም በውስጡ የያዛቸውን ሙታን እንዲሰጥ በመለኮታዊ ሥልጣን ይታዘዛል። ዮሐንስ በዚህ ምንባብ የጠቀሳቸው «ባህር» እና «ሲያል» ናቸው።

«ሄደስ» የሚለው የግሪክ ቃል በብሉይ ኪዳን ከተጠቀሰው ከዕብራይስጡ «ሲያል» ጋር ተመሳሳይ ነው። ሄደስም ሆነ ሲያል የሙት መንፈስ ከትንሣኤና ከፍርድ ቀን በፊት በጊዜያዊነት የሚቆዩበት ሥፍራ ነው። ከጊለኖው ትንሣኤና ከፍርድ በኋላ የማያምኑ ኃጥአን ወደ እሳት ባህር ይጣላሉ። በብሉይ ኪዳን ለዚህ ለእሳት ባህር የተሰጠው ስም ሲያል ሳይሆን ገሃነም ነው። ስለሆነም በሲያል፣ ሄደስ፣ ገሃነምና የእሳት ባህር መካከል ልዩነት አለ። ሲያል ከሥጋ የተለዩ መንፈሶች በጊዜአዊነት ታስረው የሚቆዩበት ሥፍራ እንጂ ሥጋዊ አካል የሚኖርበት አይደለም። ገሃነም ደግሞ ከትንሣኤ በኋላ በማያቋርጥ ቅጣት ሙሉ የሆነው የኃጢአተኞች አካል ማለትም መንፈሱ ነፍሱና ሥጋው በአንድነት የሚለቃየበት ቦታ ነው። የሲያልና የገሃነም ልዩነት በራዕይ 20:14 ላይ ተገልጸአል «ሞትና ሲያልም በእሳት ባሕር ውስጥ ተጣሉ»።

ሞትና ሲያል ስብዕና ያላቸው ስለመሆኑ

ለመሆኑ ዮሐንስ ሞትና ሲያል በማለት የጠቀሰው ምንን ለማመልከት ይሆን? የሚል ጥያቄ ሲነሣ ስለሚችል የዚህን መልስ በአጭሩ እንመለከታለን።

ዮሐንስ ስለ እነዚህ ሁለት ነገሮች ማንነት በራዕይ 6:8 ላይ የሚከተለውን አስፍሮ እናገኛለን፦ *«አየሁም፣ እነሆም ሐመር ፈረስ ወጣ፣ በእርሱም ላይ የተቀመጠው ስሙ ሞት ነበር። ሲኦልም ተከተለው።»*

እንግዲህ ዮሐንስ እንደገለጸው ሞትና ሲያል በፈረስ ላይ የሚቀመጡ ከሆነ ስብእና አላቸው ማለት ነው። ምንም እንኳን ሞት በአንድ በኩል የሕይወት መቋረጥን የሚያስከትል ቢሆንም ሆኖም ግን የሰይጣን ዋናው አጋፋሪና ታማኝ አገልጋይ ስለመሆኑ አሌ የማይባል ነው። እንደዚሁ ሁሉ ሲያልም ኃጥአን የሚጋበዙበት የቅጣት ሥፍራ ቢሆንም በዚያኑ መጠን ደግሞ እርሱ የሰይጣን አገልጋይ የሆነ እርኩስ መንፈስ ነው።

ስለሆነም ሞትና ሲያል የሰይጣንን መንግሥት የሚያገለግሉ የጨለማ መላዕክት ሲሆኑ ልዩነታቸውም እንደዚህ ነው፦ ሞት በመጀመሪያ ያለጽድቅ የሞቱ ለዎች መንፈሶችን ሁሉ ይሰበስባል። ሲያል ደግሞ እነዚህን መንፈሶች በተመደቡበት የእሥራት ቦታ ያስቀምጣቸዋል። በዚህ ምክንያት በሰዎች መካከል ሞት ሲሄድና ሲያል ሲከተለው ዮሐንስ ተመለከተ።

ይህ በራዕይ ላይ ያለው ምስል ጌታ ኢየሱስ የተናገረውን ለማስተዋል ፍንጭ ይሰጣል። *«እውነት እውነት እላችኋለሁ ቃሌን የሚጠብቅ ቢኖር ለዘላለም ሞትን አያይም»* ዮሐንስ 8:51።

እዚህ ቦታ ላይ ኢየሱስ የሚለው አማኞች የሥጋ ሞትን አይቀምሱም አይደለም። እርሱ የሚለው አማኝ «ሞትን አያይም» ነው። ይህ አባባሉ የነፍስ ከሥጋ መለየትን ተከትሎ የሚመጣውን ሞት አያመለክትም። «ሞትን አያይም» ሲል የሚያመለክተው ስሙ ሞት የተባለውን የጨለማ መልዓክና ሌላውን የጨለማ መልዓክ (መልዓክ ጽልመት) ሲያልን ነው።

ኢየሱስ የሚለው ከሥጋ የተለየው የአማኝ መንፈስ በእነዚህ በሁለቱ የጨለማ መላዕክት በሞትና በሲያል ተጽእኖ ሥር እንደማይሆን ነው። ይልቁንም እንደ ምስኪኑ አልአዛር የአማኝ መንፈስ (ነፍስ) የብርሃን መላዕክት የሆኑ የእግዚአብሔር መላእክትን ይገናኛሉ። በእነርሱም ታጅቦ ገነት ይገባል። ይህን በአእምሮአችን ይዘን የሚከተለውን የጳውሎስና የዮሐንስ አነጋገር ማስተዋል እንችላለን።

ጳውሎስ በ1ኛ ቆሮንቶስ 15:26 ላይ ስለሞት ሲናገር፣ *«... የኋለኛው ጠላት የሚሻረው ሞት ነው»* በማለት ሲጠቁም፣ ዮሐንስም በራዕይ 20:14 ላይ *«ሞትና ሲያልም በእሳት ባህር ውስጥ ተጣሉ»* በማለት ገልጸአል።

የነዚህን ምንባባት ቀዳሚ ምልከታ ሞትና ሲያል ስብዕና ያላቸው የሰይጣን አገልጋዮች መላዕክተ ጽልመት መሆናቸውንና የእግዚአብሔርና የሰው ዘር ጠላቶች መሆናቸውን ነው። ከእግዚአብሔር ጠላቶች ሁሉ የመጨረሻውን ፍርድ የሚቀበለው ሞት ነው። ከሲያል ጋር በመሆን ወደ እሳት ባሕር ይጣላል። በዚያም አለቃቸውን ለሰይጣንን የእርሱን ተከታዮችና አገልጋዮች የሆኑ ሰዎችና መላዕክተ ጽልመት ይገናኛሉ።

በዚህም የመጨረሻ የፍርድ ሂደት የመጨረሻዎቹ የእግዚአብሔር ጠላቶች ለዘላለም ከእግዚአብሔር ሕልውና ፊት ይጠፋሉ።

47

የአሁኑ ሥጋችን ይለወጥ ይሆን?

በዚህ በመጨረሻ ምዕራፍ ላይ የምናተኩረው ክርስቲያኖች ክትንሣኤ በኋላ የሚላበሱት አካል ምን ዓይነት ሊሆን ይችላል በሚለው ላይ ነው።

ባለፉት ጥናቶቻችን እንዳመለከትነው በሞተው በተቀበረው ሰውነትና በሚነሳው ሰውነት መካከል ቀጥተኛ ቀጣይነት አለ። መሠረታዊው የትንሣኤ አካል ከተቀበረው አካል ጋር ተመሳሳይ ነው። ስለሆነም እንዲህ ማለት እንችላለን። ትንሣኤ ማለት የተቀበረው ያው ሰውነት መነሳት እንጂ ሙሉ በሙሉ አዲስ ሰውነት መፍጠር አይደለም።

ሆኖም ግን ይህን እውነታ ከጨበጥን የሚከተለውን ታላቅ እውነታ መጨመር አለብን። ይኸውም የአማኝ የትንሣኤ አካል አስደናቂና የተወሰኑ ለውጦች ይኖሩታል።

የእህል ዘር ምሳሌነት

ቀደም ሲል ለማሳየት እንደተሞከረው አንድ ሰው ከትንሣኤ በኋላ የሚላበሰው ገላው፣ በምድራዊ ሕይወቱ ወቅት ከነበረው ሙሉ በሙሉ የተቀየረ እንደማይሆን ነው። ይህን እንጂ አንዳንድ የተሰዩና ብርቅዬ ባህርያት የሚንጸባረቁበት ለመሆኑ ደግሞ የማይካድ ነው። ይህንንም በማጠናከር

ጳውሎስ እንደሚከተለው ይነግረናል፦ *«ነገር ግን ሰው፣ ሙታን እንዴት ይነሣሉ? በምንስ ዓይነት አካል ይመጣሉ? የሚል ይኖር ይሆናል። አንተ ሞኝ፣ አንተ የምትዘራው ካልሞተ ሕያው አይሆንም። የምትዘራው ሰንዴ ቢሆን ስሌላም ዓይነት የአንዱ ቢሆን፣ ቅንጣት ብቻ ነው እንጂ የምትዘራው የሚሆነውን አካል አይደለም፤ እግዚአብሔር ግን እንደ ወደደ አካልን ይሰጠዋል፣ ከዘሮችም ለእያንዳንዱ የገዛ አካሉን ይሰጠዋል።»* 1ኛ ቆሮንቶስ 15:35-38

ከዚህ ከጳውሎስ መግለጫ የምንረዳው ሦስት ፍሬ ነገሮችን ነው። አንደኛ በተዘራው ፍሬና በኋላ በሚበቅለው ተክል ቀጥታ ግንኙነት ያለ መሆኑን፣ ሁለተኛ ታዳጊው ተክል በመጠኑም ሆነ በአንዳንድ ገጽታዎቹ ከተዘራው ፍሬ የሚለይ መሆኑንና፣ ሦስተኛ ያም ሆኖ ግን በተዘራው ፍሬና በመጨረሻም ላይ ተክሉ በሚያፈራው ፍሬ መካከል የባህርይ ተመሳሳይነት መኖሩን ነው። ስለዚህ ልክ እንደዚሁ ሁሉ አንድም ሰው ከሞት ወደ ትንሣኤ በሚሸጋገርበት ጊዜ ተመሳሳይ የሆኑ ለውጦች እንደሚከሰቱ ነው። ልክ ተክሉ ከዘሩ የተለየ አዲስ ቅርጽና ቁመና ይዞ እንደሚበቅል ሁሉ በትንሣኤ የተነሳውም ሰው ለየት ያሉ ባህርያት ይንጸባረቅበታል። ዞሮ ዞሮ ግን ውስጣዊ ይዘቱ የማይሻር የማይቀየር ይሆናል። ምናልባትም ይህን አባባላችንን ይበልጥ ግልጽ የሚያደርግልን አሁንም ጳውሎስ በ1ኛ ቆሮንቶስ 15:39-44 ላይ ያሰፈረው ይሆናል፦ *«ሥጋ ሁሉ አንድ አይደለም፤ የሰው ሥጋ ግን አንድ ነው፣ የእንስሳም ሥጋ ሌላ ነው የወፎችም ሥጋ ሌላ ነው፣ የዓሣም ሥጋ ሌላ ነው። ደግሞ ሰማያዊ አካል አለ ምድራዊ አካል አለ፣ ነገር ግን የሰማያዊው አካል ክብር ልዩ ነው፣ የምድራዊውም አካል ክብር ልዩ ነው። የጸሐይ ክብር አንድ ነው፣ የጨረቃም ክብር ሌላ ነው። የከዋክብትም ክብር ሌላ ነው በክብር አንዱ ኮከብ ከሌላው ይለያልና።»* በማለት ጳውሎስ ከገለጸ በኋላ በሚከተለው ሁኔታ ይደመድመዋል፦ *«ይህ የሚበሰብሰው የማይበሰብሰውን ሊላበስ ይህም የሚሞተው የማይሞተውን ሊላበስ ይገባዋል።»*

ይህ በትንሣኤ ጊዜ የአማኝ ሰውነት የሚያልፍበትን ለውጥ በተመለከተ በጳውሎስ የተሰጠው ትንታኔ በሚከተሉት መንገዶች ሊገለጥ ይችላል።

1. ጳውሎስ አሁን ባለው የፍጥረት ሥርዓት እንኳ በፍጥረታት መካከል የተለያየ ተፈጥሮና እቋም እንዳለ ይገልጣል። ለዚህም ዋና ዋና የሆኑትን ክፍሎች ለምሳሌ እንስሳትን፣ አሦችንና ወፎችን ያነሳል። ይህ ዝርዝር ከዘመናዊ ሳይንስ ጋር የሚስማማ ነው። በዘመናዊ ሳይንስ ድምዳሜ መሠረት በሰው ዘር መካከል ያለው የደም ኬሚካላዊ ውሕደት የጎላ ልዩነት የሌለ ሊሆን ነገር ግን በእንስሳትና በሰው መካከል በዚህ ረገድ ሰፊ ልዩነት አለ።

2. ጳውሎስ በዚህ ምድር ላይ ከምናውቃቸው እካላት በላይ ክፍ ያለ አካል እንዳለ ያመለክታል። ይህንንም አካል <መልአካዊ> ወይም <ሰማያዊ>

እካል ብሎ ይጠራዋል። ይህም ከጊዜያችን የሳይንስ ግኝቶች ጋር ስምምነት ያለው ነው። ሳይንስ ሰዎችን በሕዋው ሳይ ለማስቀመጥ ተሳክቶለታል። ሆኖም ግን በጠፈር ላይ ባላቸው ቆይታ በሕይወት ለማቆየት እነርሱን በምድራዊ ከባቢ አየር ሁኔታ ውስጥ ማቆየት የግድ ነው። ልክ እንደዚሁ ከምድር በራቀ በሰማያዊ ሃገር ሳይ ሰው እንዲኖር አሁን ካለው ሁኔታ በተለየ ሁኔታ መታጠቅ አለበት። ለዚህ ዘላለማዊ ቤት ግን በራሱ ምንም ማድረግ ስለማይችል ሰው በእግዚአብሔር ሳይ መደገፍ አለበት።

3. ጳውሎስ እኛ ልናያቸውና ልንረሃናቸው የሚለያዩ ለማያዊ እካላት እንደሆኑ ይገልጥልናል። ጸሐይ የራሷን ብርሃን ታፈልቃለች ጨረቃ የጸሐይን ብርሃን መልሳ ታኃጸባርቃለች። በከዋከብት መካከልም በብርሃናቸው የተለያየ ሥርዓት አለ። በእማኞም የትንሣኤ እካል ዘንድ በትንሣኤ ጊዜ እንዲህ ዓይነት የክብርና የሥርዓት ልዩነት እንዳለ ጳውሎስ ይናገራል።

ይህም በዳንኤል 12:2-3 ስለ ትንሣኤ በተነገረው ትንቢት ሳይ አስቀድሞ ተነግሯል። *«ብዎድርም ትቢያ ውስጥ ካንቀላፉት ብዙዎች ይነቃሉ፤ አኩሌቶቹ ወደ ዘላለም ሕይወት፥ አኩሌቶቹም ወደ አፍረትና ወደ ዘላለም ጉስቁልና። ጥበበኞቹም እንደ ሰማይ ጸዳል፥ ብዙ ሰዎችንም ወደ ጽድቅ የሚመልሱ እንደ ከዋክብት ለዘላለም ይደምቃሉ።»*

ዳንኤል በዚህ ቦታ ሳይ አስቀድሞ የሚነግረን በትንሣኤ ጊዜ በቅዱሳን መካከል ለለሚኖረው የብድራትና የክብር ልዩነት ነው። ለሌሎች የእግዚአብሔርን እውነት በማሳወቅ ታማኞችና ትጉሆች የሆኑ እንደ ከዋክብት ይደምቃሉ።

የእነዚህ በከበረ እካል የሚነሱ ቅዱሳን እንደነዚያ ከዋክብት የአብርሃም ቃል ኪዳን ፍጻሜዎች ናቸው። *«ወደ ሜዳም አወጣውና፦ ወደ ሰማይ ተመልከት ከዋክብትንም ልትቆጥራቸው ትችል እንደሆነ ቁጠር አለው። ዘርህም እንደዚህ ይሆናል አለው»* ዘፍጥረት 15:5።

መለኮታዊ የሆነውን የእግዚአብሔር ቃል ዘርን በልባቸው የተቀበሉ አብርሃም እንዳደረገው ለእግዚአብሔር የተስፋ ቃል ከታዘዙት የአብርሃም ዘሮች ጋር ይጠቃለላሉ። በአርግጥም ይህ በእምነት ከልቡ የተቀበለው የማይጠፋው የእግዚአብሔር ቃል ዘር እማኝ በጸድቃን ትንሣኤ እንዲነሳ ያደርገዋል።

የእግዚአብሔር የመጨረሻ ተስፋ የሚፈጸምበት በትንሣኤ ቀን እማኞች ሁሉ ለእግዚአብሔር ቃል ባላቸው እምነት መሠረት እግዚአብሔር ለአብርሃም እንዳሳየው ከዋክብት በቁጥር የበዙ የከበሩና በክብራቸውም የተለያዩ ይሆናሉ።

ከዚህም መለኮ መግለጫ በመነሳት ከእምስት ድምዳሜዎች ሳይ ለመድረስ እንችላለን።

አንደኛ፦ ምድራዊ ሥጋችን ፈራሽ፥ በስባሽ፥ ለእርጅና ለሕመም የተጋለጠ ሆኖ ሳለ፥ እዲሱ ሥጋችን ከዚህ መለኮ ድክመትና ጉስቁልና የነፃ የፀዳ ነው።

ሁለተኛ፦ ምድራዊ ሥጋችን ሟች ሲሆን፥ አዲሱ ግን ሞት የማይደፍረውና ዘላለማዊ ነው።

ሦስተኛ፦ የእሁኑ ለውነታችን ክብር የሌለው ለውነት ሲሆን በፊል. 3:21 ሳይ «የተዋረደ ሥጋ» ተብሎ ተጠርቷል። የእሁኑ የሰው ልጅ ለውነት የኃጢአትና ለእግዚአብሔር ያለመታዘዙ ውጤት ነው። ለለሆነም የማያቋርጥ የውርደት ምንጭና ውድቀትን የሚያስታውስ የእካላዊ ድካምና ጉድለት ውጤት ሆኗል። ሰው ምንም ያህል በሳይንስና በሥነ ጥበብ ታላላቅ ለኬቶችን ቢያስመዘግብም በለውነቱ ውስንነትና ቁላዊ ፍላጎት ያለማቋረጥ በዝቅጠኝነት ሁኔታ እንዲሆን አድርጎታል። እዲሱ የትንሣኤ እካል ግን የውበትና የክብር እካል የሚሆን ሲሆን ከእሁኑ የሰው ውስንነት ነጻ ይሆናል።

አራተኛ፦ ምድራዊ ሥጋችን ለሞት ያለብንን ተገዢነት ሲያመለክት አዲሱ ለውነታችን ግን የእግዚአብሔርን ሉዓላዊነት የሚያንጸባርቅ ነው።

አምስተኛ፦ ምድራዊ ሥጋችን ተገዢነቱ ለምድራዊ ፍላጎታችን <ማለትም ለነፍሣችን> ሲሆን እዲሱ ለውነታችን ግን ከእግዚአብሔር ጋር በቀጥታ ለሚያገናኘን መንፈሳችን ነው። በመጀመሪያው የእግዚአብሔር ዕቅድ መሠረት ሰው መንፈስ፥ ነፍስና ሥጋ ያለው እንዲሆን ነበር። ከነዚህ ሦስት የሰው ሕላዊያት ውስጥ የሰው መንፈስ ከእግዚአብሔር ጋር ለመገናኘትና ሕብረት ለማድረግ ችሎታ ሲኖረው ሌሎችን የሰው ባህርያት ማለትም ነፍስንና ሥጋን ለመቆጣጠር እቅም ነበረው። ሆኖም ሰው በውድቀት ምክንያት ወደ ፈተና የሚያዘነብል ስለሆነ ነፍስና ሥጋ ተቆጣጣሪነቱን በእጃቸው አደረጉ። ይህም በሰው ውስጣዊ ስብዕናና ውጫዊ ሰውነት ሳይ ሲደረስበት የማይቻል ሰውጥ እደረገ። የሰው እካል «ተፈጥሯዊ (ነፍሳዊ)» ሆነ። ስለሆነም የእካሱ ብልቶችና ተግባራቸው ለነፍሳዊና ዝቅተኛ ለሆነው እርካታ ብቻ የሚያገለግሉ ለመንፈሱ እርካታ ግን ችሎታ የሌላቸው ሆኑ።

በተወሰነ መንገድ ይህ <(ተፈጥሮአዊ) (ነፍሳዊ)> እካል የሰው መንፈስን የሚወስን እሥር ቤት ነው። ሆኖም ግን የትንሣኤው እካል «መንፈሣዊ» ይሆናል። ከፍ ያለውን የሰውን የመንፈስ እርካታ ለማካሄድ ፈጽሞ ይችላል። ይህን እዲሱን ለውነት በመልበስ የሰው መንፈስ እንደገና የእማኝ የትንሣኤ እካል በመንፈስ ቁጥጥር እንዲሆንና በለምምነትና በፍጽምና እንዲጓዝ ስብዕናውን ሁሉ ይቆጣጠራል።

ጳውሎስ በአሮጌውና በአዲሱ ሰውነት መካከል ያለውን ልዩነት የአዳምን ሰውነትና የክርስቶስን የትንሣኤ አካል በማነጻጸር አማኝም በትንሣኤ አንደ ጌታ የትንሣኤ አካል እንደሚኖረው በመናገር ያጠቃልለዋል።

«የፊተኛው ሰው ከመሬት መሬታዊ ነው፤ ሁለተኛው ሰው ከሰማይ ነው። መሬታዊው እንደሆነ መሬታውያን የሆኑት ደግሞ እንዲሁ ናቸው። ሰማያዊ እንደሆነ ሰማያውያን የሆኑት ደግሞ እንዲሁ ናቸው። የዚህንም የመሬታውያን መልክ እንደ ሰበሰን የሰማያዊውን መልክ ደግሞ እንለብሳለን.....» 1ኛ ቆሮንቶስ 15:47-49፡

የአሁኑ የሰው አካል በመጀመሪያ ከተፈጠረውና የሰው ዘር ሁሉ ከተገኘበት ከአዳም ተፈጥሮ ጋር አንድ ነው። ነገር ግን የአማኝ የትንሣኤ አካል የሚመሳሰለው በአዲስ ተፈጥሮ ከኃጢአትና ከውጤቱ በአርሱ አምነው በተዋጁት፤ የአዲሱ ዘር ሁሉ ላይ ራስ ከሆነው ከክርስቶስ ጋር ነው።

ጳውሎስ ስለ አማኝ የትንሣኤ አካል ተመሳላይ መግለጫ ይሰጠናል። *«እኛ እገራችን በሰማይ ነውና፤ ከዚያም ደግሞ የሚመጣ መድኃኒትን እርሱም ጌታን ኢየሱስ ክርስቶስን እንጠባበቃለንና፤ እርሱም ሁሉን እንኳ ለራሱ ሊያስገዛ እንደሚችልበት አሠራር፤ ክቡር ሥጋውን እንደሚመስል የተዋረደውን ሥጋችንን ይለውጣል»* ፊልጵስዩስ 3:20-21።

ቃል በቃል ሲተረጎም የመጨረሻው ትርጉም የሚናገረው ክርስቶስ የእርሱን የከበረ አካል ይመስል ዘንድ የተዋረደውን አካላችንን ይሰውጠዋል። በ1ኛ ዮሐንስ 3:2 ተመሳላይ የሆነና በክርስቶስ ምጽአት ጊዜ የአማኞች መለወጥ አንዱት እንደሚሆን የሚናገር ምንባብ እናገኛለን። *«ወዳጆች ሆይ፤ አሁን የእግዚአብሔር ልጆች ነን ምንም እንደምንሆን ገና አልተገለጠም። ዳሩ ግን ቢገለጥም እርሱ እንዳለ ስለምናየው እርሱን እንድንመስል እናውቃለን።»*

ክርስቶስ በሚመለስበት ጊዜ በሕይወት ያሉት ክርስቲያኖችና በዚህም ምክንያት ትንሣኤ የሚያስፈልጋቸው በዚያው ጊዜ ቅጽበታዊና ተአምራዊ የሆነ ለውጥ በሕይወታቸው ይከናወናል። *«እነሆ፤ እንድ ሚሥጢር እነግራችኋለሁ ሁላችን እናንቀላፋም ነገር ግን በኋለኛው መለከት ሲነፋ ሁላችን በድንገት በቅጽበት ዓይን እንለወጣለን፤ መለከት ይነፋልና ሙታንም የማይበሰብሱ ሆነው ይነሣሉ እኛም እንለወጣለን።»* 1ቆሮንቶስ 15:51

ጳውሎስ «ሁላችን አናንቀላፋም» ሲል «ሁላችንም አንሞትም» ለማለት ነው። በመቀጠልም «ሁላችን እንለወጣለን» ይላል። በሌላ አነጋገር አውነተኞች አማኞች ሁሉ የተነሱም ወይም በሕይወት የተነጠቁም ቢሆኑ ቅጽበታዊና ተአምራዊ የሆነው ለውጥ በለውነታቸው ውስጥ ይከናወናል።

ክርስቶስ ከትንሣኤው በኋላ ያለውን አካል ባህርይ በተመለከተ ወንጌላት የተወለኑና እጅግ የሚያስደንቁ ፍንጮችን ይሰጡናል። ከነዚህም መካከል አኛ

አሁን በምድራዊ አካላችን እንዳለንበት ሁኔታ ለቦታና ለጊዜ ውሱንነት የሚገዛ አልሆነም። በፈቀደው ጊዜ የሚገለጥና የሚሰወር በተዘጋ ቤት የሚገባ በተለያዩ ቦታዎች በተለያዩ ሁኔታዎች የሚገለጥ ወደ ሰማይ የሚያርግና ተመልሶ ወደ ምድር የሚወርድ ሆኗል። በነዚህና ገና ወደፊት በሚገለጡ በሌሎች ሁኔታዎች ከትንሣኤና ከንጥቀት በኋላ የተዋጀ አማኝ አንደጌታው ይመስላል። እስከ አሁን የተናገርነው ስለአማኞች የትንሣኤ አካል ነው። ስላልተዋጁና ከነኃጢአታቸው ስለሞቱ ያልዳኑ ሰዎች ትንሣኤስ? መጽሐፍ ቅዱስ በግልጥ አንደሚያሳየን አነርሱም በራሳቸው መንገድ ሰፍርድና ለቅጣት ይነሣሉ። ምን ዓይነት የትንሣኤ አካል ለብሰው እንደሚነሱ መጽሐፍ ቅዱስ በግልጥ ስለሚነግረን ምንም መልስ ላንመልስ እናልፈዋለን።

የትንሣኤ ልዩ ጠቀሜታ

ይህን የጥናታችንን ክፍል ለማጠናቀቅ፤ ስለምን ትንሣኤ በክርስትና እምነት ውስጥ ቀዳሚ ሥፍራ እንዳለው፤ ሦስት ማስረጃዎችን በመጥቀስ እናጠቃልላለን፦

አንደኛ፦ ትንሣኤ የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ማንነት ማረጋገጫችን ነው። ይህንንም ጳውሎስ በሮሜ 1:14 ላይ እንደሚከተለው ያስረግጥልናል፦ *«..... እንደ ቅድስና መንፈስ ግን ከሙታን መነሳት የተነሳ በኃይል የእግዚአብሔር ልጅ ሆኖ ስለ ተገለጠ ስለ ልጁ ነው። እርሱም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።»*

ቀደም ሲል ክርስቶስ በሁለት ሽንጎዎች ላይ ማለትም በሃይማኖታዊው በአይሁድ ሽንጎና በዓለማዊው የሮማ ገዢ በጲላጦስ ሸንጎ ቀርቦ ነበር። እነዚህ ሸንጎዎች ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን ካለመቀበላቸውም በላይ ሞት ፈርደውበታል። ከዚህም በተጨማሪ የኢየሱስን መቃብር ከመክፈት ለመከላከል ግንባር ፈጥረው ነበር። ለዚህም የአይሁድ ሸንጎ ልዩ ማህተም ሲያዘጋጅ የሮማው ገዢ ደግሞ የታጠቁ ወታደሮች መቃብሩን እንዲጠብቁ አዘጋጅቶ ነበር።

ሆኖም ግን በሦስተኛው ቀን እግዚአብሔር ጣልቃ ገባ። ማህተሙ ተሰበረ፤ የታጠቁ ጠባቂዎች በድን (ሽባ) ሆኑ፤ ኢየሱስም ከመቃብር ወጣ። በዚህ ሁኔታ እግዚአብሔር የሮማ ገዢንና የአይሁድ ሸንጎን ውላኔ ገለበጠ። በይፋም ክርስቶስ ኃጢአት የሌለበት የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ ገለጠ።

ሁለተኛ፦ ሌላው የትንሣኤ ጠቀሜታ እግዚአብሔር መሐሪና ይቅር ባይ አምላካችን ለመሆኑ ማረጋገጫችን በመሆኑ ነው። ለዚህም በማስረጃነት አሁንም ሮሜ 4:25 ላይ የሰፈረውን እንጠቅሳለን፦ *«..... ስለ እኛም ነው እንጂ ስለ በደላችን አሳፎ የተሰጠውን እኛን ስለ ማጽደቅም የተነሳውን ጌታችንን ኢየሱስ ከሙታን ባስነሳው ሰምናምን ለእኛ ይቆጠርልን ዘንድ አለው።»*

ይህ የሚያመለክተው የኃጢአተኛው መጽደቅ የተደገፈው በክርስቶስ ከሙታን ተሰይቶ መነሳት ላይ መሆኑን ነው። ክርስቶስ በመስቀል ወይም በመቃብር ቢቀር ኖሮ እግዚአብሔር ሰኃጢአተኞች መዳንና የዘላለም ሕይወት የገባው ተስፋ አይፈጸምም ነበር። ሰኃጢአተኞች ይቅርታን፤ ሰላምን፤ የዘላለም ሕይወትንና በኃጢአት ላይ ድልን የሚያመጣው የተነሳውን ክርስቶስን በእምነት መቀበልና ስለ እርሱም መመስከር ነው። *«ኢየሱስ ጌታ እንደሆነ በአፍህ ብትመሰክር እግዚአብሔርም ከሙታን እንዳነሳው በልብህ ብታምን ትድናለህ»* ሮሜ 10:9።

ፍ

መዳን በሁለት ነገሮች ላይ የተመረኮዘ ነው

1. ኢየሱስ ጌታ እንደሆነ በይፋ ብመመስከር ላይ፣
2. እግዚአብሔር ከሙታን እንዳነሳው በልብ በማመን፤ በክርስቶስ ለማያምኑ ምንም ዓይነት መዳን የላቸውም።

አመክንዮና አእምሮአዊ ምጥቀት ሌላ ድምዳሜን እያስገኙም። ክርስቶስ ከሞት ካልተነሳ ኃጢአተኛውን ይቅር የሚልበትና የሚያድንበት ኃይል የለውም። ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚነግረን እርሱ ተነስቷል። ስለሆነም መነሳቱ ለይቅር ባይና ለማዳን ኃይሉ አመክንዮአዊ ማረጋገጫ ነው።

«ስለ እነርሱም ሊያማልድ ዘወትር በሕይወት ይኖራልና። ስለዚህ ደግሞ በእርሱ ወደ እግዚአብሔር የሚመጡትን ፈፅሞ ሊያድናቸው ይችላል» ዕብራውያን 7:25።

እግዚአብሔር ለሰጠን ደህንነት የክርስቶስ ትንሣኤ ምክንያታዊ ፍጹምና አስፈላጊ ነው።

«ክርስቶስም ካልተነሳ እንግዲያስ ስብከታችን ከንቱ ነው። እምነታችሁም ከንቱ ናት።» 1ቆሮንቶስ 15:14

«ክርስቶስም ካልተነሳ እምነታችሁ ከንቱ ናት፤ እስከ አሁን ድረስ በኃጢአታችሁ ላላችሁ» 1ቆሮንቶስ 15:17

የጊዜያችን የክርስትና ሁኔታ ይህን ግልጥ የሆነ የመጽሐፍ ቅዱስ እንጋገር ያረጋግጥልናል። የክርስቶስን ሰብአዊና አካላዊ ትንሣኤ የሚክዱ «የሥነ መለኮት ሊቃውንት» የፈጠሩትን ያህል ሊፈላሰፉ ይችላሉ። ነገር ግን ወደ ሰላም ደስታና የኃጢአት ይቅርታ ልምምድ ግን መቼም አይመጡም።

ሦስተኛ፦ የመጨረሻው ትንሣኤ ጠቀሜታ ለእኛ ለክርስቲያኖች የተስፋችን መቋጫና የዓላማችን ግብ በመሆኑ ነው። ጳውሎስም በፊልጵስዩስ 3:10-12 ላይ የሚያረጋግጥልን ይህንኑ ነው።

«እርሱንና የትንሣኤውን ኃይል እንዳውቅ፤ በመከራውም እንድካፈል፤ ወደ ሙታንም ትንሣኤ ልደርስ ቢሆንልኝ፤ በሞቱ እንድመስለው እመኛለሁ። አሁን እንዳገኘሁ ወይም አሁን ፍጹም እንደሆንሁ አይደለም፤ ነገር ግን ለሰ እርሱ በክርስቶስ ኢየሱስ የተያዝሁበትን ያን ደግም እይዛለሁ ብዬ እፈጥናለሁ።»

በተሰይም ሁለቱን ሐረጎች ማለትም «የትንሣኤውን ኃይል እንዳውቅ» እና «ወደ ሙታን ትንሣኤ ልደርስ» የሚሉትን እናስተውል። ጳውሎስ በዚህ ዓለም ላይ የሚገኝ ማናቸውም ነገር ሁሉ የእምነቱና የድካሙ ሁሉ ድምር ከሆነው የሙታን ትንሣኤ እንዳይከለክለው ይጨነቃል። በዚህ ሁኔታ ማናቸውም ክርስቲያን ከጳውሎስ ዝንባሌ ጋር አንድ መሆን አለበት። ትንሣኤ ከሌለ የክርስቲያን እምነትና ሕይወት ስህተት ይሆናል። *«ለዚች ሕይወት ብቻ ክርስቶስን ተስፋ ያደረግን ከሆነ ከሰው ሁሉ ይልቅ ምስኪኖች ነን»* 1ቆሮንቶስ 15:14።

እነሆም እኛም እንደ ጳውሎስ የእግዚአብሔርን ጸጋና በረከት እንቋደስ ዘንድ በትንሣኤ ጠቀሜታ ልናምንበት ይገባል።

ክፍል 7

ዘላለማዊ ፍርድ

«.... የጻድቅህም ፍርድ ሁሉ ለዘላለም ነው»
መዝሙር 118:160

48

የሁሉም ዳኛ እግዚአብሔር

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የምንዳስሰው ደግሞ በዕብራውያን 6:1-2 ላይ ከስፈሩት ከስድስቱ የክርስትና እምነት መሠረታዊ አስተምህሮዎች የመጨረሻው ስለሆነው ስለ ዘላለማዊ ፍርድ ነው።

ስለሰላም ያህል ስድስቱን አስተምህሮዎች፥ በቅድሚያ በቅደም ተከተላቸው እንመለከታለን፦

1. ከሞተ ሥራ ንስሐ
2. በእግዚአብሔር እምነት
3. ስለ ጥምቀቶች
4. እጆችን ስለ መጫን
5. ስለ ሙታን ትንሣኤ
6. ዘላለማዊ ፍርድ

ከዚህ በመቀጠል በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የምናተኩረው የዘላለማዊ ፍርድን ሁለት ገጽታዎች በማስመልከት ይሆናል። ከነዚህም በመጀመሪያ፥ መጽሐፍ ቅዱስ የሁሉም ዳኛ ስለሆነው ስለ እግዚአብሔር በሚናገረው ላይ የምናተኩር ሲሆን በማስከተል ደግሞ እግዚአብሔር ፍርዱን የሚያስተላልፍባቸውን መንገዶች በመተንተን ይሆናል።

ፍርድና ምሕረት

መጽሐፍ ቅዱስ ስለ እግዚአብሔር ፈራጅነት ለሚያስተምረን ትምህርት መግቢያ ይሆን ዘንድ በቅድሚያ የምንመለከተው በዕብራውያን 12:22-24 ላይ የለፈረውን ጥቅስ ነው። «ነገር ግን ወደ ጽዮን ተራራና ወደ ሕያው እግዚአብሔር ከተማ ደርሳችኋል፥ ወደ ሰማያዊቱም ኢየሩሳሌም በደስታም ወደ ተሰበሰቡት ወደ አእላፋት መላእክት፥ በሰማያትም ወደ ተጻፉ ወደ በኩራት ማኅበር፥ የሁሉም ዳኛ ወደ ሚሆን ወደ እግዚአብሔር፥ ፍጹማንም ወደ ሆኑት ወደ ጻድቃን መንፈሶች፥ የአዲስም ኪዳን መካከለኛ ወደ ሚሆን ወደ ኢየሱስ፥ ከአቤልም ደም ይልቅ የሚሻለውን ወደ ሚናገር መርጨት ደም ደርሳችኋል።»

እነኚህ የተጠቀሱት ሦስቱም ቁጥሮች እያንዳንዳቸው በሦስት የተለያዩ ርዕሶች ላይ ያተኩሩ ናቸው። የመጀመሪያው ቁጥር 22 ስለ እግዚአብሔር ማደሪያ ሲነግረን ሁለተኛው ቁጥር 23 ደግሞ እግዚአብሔር በዚህ በማደሪያው አብረውት እንዲኖሩ የፈቀዳላቸው እነማን ስለመሆናቸው ይገልፅልናል። በሦስተኛ ደረጃ በቁጥር 24 ላይ የሰፈረው መልእክት ስለ ራሱ ስለ እግዚአብሔር ማንነት የሚያስረዳን ነው።

በተጨማሪም እነዚህ ሦስት ክፍሎች፥ እያንዳንዳቸው በሦስት ንዑሳን ክፍሎች የተከፈሉ ስለመሆኑም እናጤናለን። በቅድሚያ ለእግዚአብሔር ማደሪያ፥ የጽዮን ተራራ፥ የሕያው እግዚአብሔር ከተማና ለሰማያዊቱ ኢየሩሳሌም የሚሉ መጠሪያዎች የተሰጡት ስለመሆኑ ስንመለከት፥ በዚህ በእግዚአብሔር ማደሪያ ስመኖር የተፈቀደላቸው ደግሞ፥ አእላፋት መላዕክት <ማለትም ከሰይጣን ጋር ያላበሩትና በዘመነ ኖኅ ከኃጢአተኞች ጋር ያልተባበሩት>፥ በሰማያት የተጻፉ የበኩራት ማኅበር <የአዲስ ኪዳን ቅዱሳኖች> እና ፍጹማን የሆኑት የጻድቃን መንፈሶች <የብሉይ ኪዳን ቅዱሳን> ስለመሆናቸው እንረዳለን።

በሦስተኛም ደረጃ ስለ እግዚአብሔር ማንነት በማስመልከት፥ የሁሉም ዳኛና የአዲስ ኪዳን መካከለኛ የሆነው ኢየሱስ፥ ከአቤልም ደም ይልቅ የሚሻለው የመረጨት ደም በሚል መልኩ መገለጹን እናጤናለን። ይህ የሚያመለክተን እግዚአብሔር ዳኛ ብቻ ሳይሆን ራሱ አስታራቂና የፍጥረት ሁሉ ቤዛ መሆኑን ነው።

በእምነት ዓይንና በመጽሐፍ ቅዱስ ብርሃንነት ይህን ሁኔታ ስንዳስሰው በመካከል አስፈሪ ብቸኛና ግርማን የተሞላ «የሁሉ ፈራጅ እግዚአብሔርን» እናገኛለን። በዚህ ቦታ ላይ እግዚአብሔር ራሱን የገለጠልን በሉአላዊነቱና በዘላለማዊ ሥልጣኑ እንደ ዳኛ ማለትም የሁሉ ዳኛ፥ የሰማይና የምድር ዳኛ የመላእክትና የሰዎች ዳኛ በመሆን ነው።

ሆኖም ግን እግዚአብሔር እንደ ዳኛ ብቻ ቢገለጥ ኖሮ ሰንጢአተኛ ለው ማለትም ለብሉይ ኪዳን የፍጹማን መንፈሶችም ሆነ በአዲስ ኪዳን ዳግም ለተወለዱ ቅዱሳን ሥፍራ ባልኖረ ነበር። በምህረቱ የእግዚአብሔር ቃል መገለጥ ከዳኛው ከእግዚአብሔር ወደ ብቸኛው ና በቅዱሱ በኢየሱስ ክርስቶስ በጠፋው ኃጢአትን በተሞላው ለው መካከል መግባት ወደሚችለው ወደሚያስታርቃቸው ወደ መካከለኛው ወደ ኢየሱስ ይመራናል። ይህም የሚያጠቃልለው የእርቅ ዋጋና መሣሪያ በሆነው በኢየሱስ ደም መገለጥ ነው።

ምንባቡ የኢየሱስ ደምን በተቃርኖ የሚያስተያየው ከአቤል ደም ጋር ነው። በዚህም ውስጥ ሦስት የተቃርኖ ነጥቦች አሉ።

1. የአቤል ደም የፈሰሰው ያሰፈቃዱ በወንጀለኛ ድንገተኛ አደጋ ሲሆን፥ የኢየሱስ ደም ግን በራሱ ፈቃድ በነጻ ለሰው ልጅ ቤዛነት ዋጋ የተሰጠ ነው።

2. የአቤል ደም የተረጨው በምድር ላይ ሲሆን የኢየሱስ ደም ግን በሰማይ በምህረቱ መክደኛ ፊት ነው።

3. የአቤል ደም በበቀል በገዳዩ ላይ ወደ እግዚአብሔር የሚጮህ ሲሆን የኢየሱስ ደም ግን ሰንጢአተኛው ምህረትንና ይቅርታን ይለምናል።

ስለዚህ የእግዚአብሔር የሁሉ ዳኛ በመሆን መገለጥ በክርስቶስ ደም መናናስና በመካከለኛነቱ አገልግሎት በኩል በተገለጠው የእግዚአብሔር ምሕረትና ጸጋ መገለጥ ጋር የተገናኘ ነው። የእግዚአብሔር ዳኝነት በምህረቱና በጸጋው መዋብ መጽሐፍ ቅዱስ በዘህ ርዕስ ከሚያስተምረው ጋር አንድ ነው።

ስለ እግዚአብሔር ዳኝነት ብዙ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ጥቅሶችን መደርደር ይቻላል። ለምሳሌ ከአሪት ዘፍጥረት ብንጀምር አብርሃም እግዚአብሔርን፥ «የምድር ሁሉ ፈራጅ በቅን ፍርድ አይፈርድምን?» በፍጥረት 18:25 ሲል እንደተማጸነ እናያለን።

እንደገናም በመጽሐፈ መሳፍንት 11:27 ላይ «ፈራጁ እግዚአብሔር በእስራኤል ልጆችና በአሞን ልጆች መካከል ዛሬ ይፍረድ» ተብሎ እንደተገለጸ እናስተውል በመዝሙረ ዳዊትና በትንቢተ ኢሳይያስ ላይ ደግሞ፦

«በእውነት በምድር ላይ የሚፈርድ አምላክ አለ ይላል።» መዝሙር 57:11

«የምድር ፈራጅ ሆይ፥ ክፍ ክፍ በል።» መዝሙር 93:2

«እግዚአብሔር ፈራጃችን ነው።» ኢሳይያስ 33:33 የሚል እናነኛለን።

እንደዚሁም ኢሳይያስ በ28:21 ላይ፥ *«እግዚአብሔርም ሥራውን ማለት እንግዳ ሥራውን ይሠራ ዘንድ፥ አድራጎቱንም ማለት ያልታወቀውን አድራጎቱን ያደርግ ዘንድ በጥራሲም ተራራ እንደነበረ ይነሳል፥ በገባዖንም ሸለቆ እንደነበረ ይቆጣል።»* ሲል በጠላቶቹ ላይ ተበቃይ መሆኑን ከገለጸ በኋላ በ33:22 ላይ ደግሞ «እግዚአብሔርም ፈራጃችን ነው» በማለት ስለ ዳኝነቱ ያበሥራል። ወደ አዲስ ኪዳን ስናመራ ደግሞ፥ ጌታችን ኢየሱስ ራሱ በዮሐንስ 3:17 ላይ የሚከተለውን እንደተናገረ እናስተውላለን፦ *«ዓለም በልጁ እንዲድን ነው እንጂ፥ በዓለም እንዲፈርድ እግዚአብሔር ወደ ዓለም አልላከውምና፥ በእርሱ በሚያምን አይፈረድበትም።»*

እንደዚሁም በ2ኛ ጴጥሮስ 3:9፥ *«ለአንዳንዶች የሚዘገይ እንደሚመስላቸው ጌታ ስለ ተሰፋ ቃሉ አይዘገይም፥ ነገር ግን ሁሉ ወደ ንስሐ እንዲደርሱ እንጂ ማንም እንዳይጠፋ ወዶ ስለ እናንተ ይታገሳል።»* በሚል መልኩ ስለ እግዚአብሔር ርኅሩኅነትና መሐሪነት ተገልፆ እናገኛለን፦ ከዚህ በላይ የተጠቀሱትና ሌሎችም ጥቅሶች ለምህረትና ለማዳን የፈጠነና ለፍርድ ግን የማይቸኩል መሆኑን ያሳያሉ። ሆኖም ግን የአዲስ ኪዳን መገለጥ በዚህ እውነት አንድ እርምጃ እልፍ ያደርገናል። የእግዚአብሔር ለፍርድ አለመቸኮል ወደፊት ፍርዱ እንደሚፈጸም ያመለክታል።

እግዚአብሔር አብና ቃሉ የሆነው ልጁ

በ1ኛ ጴጥሮስ 1:17 ላይ *«ለሰው ፊትም ሳይደላ በእያንዳንዱ ላይ እንደሥራው የሚፈርደውን አባት....»* ተብሎ እንደተገለጸው ሁሉ እግዚአብሔር አብ ሉዓላዊ እምላክ ዘላለማዊ ብርሃንና በፍጥረታቱ ሁሉ ላይ የበላይ ፈራጅ ነው።

ይህም ሆኖ ግን በእምላካዊ ጥበቡ በመመራት የዳኝነቱን ሥልጣን ለልጁ ለጌታችን ለኢየሱስ ክርስቶስ የሰጠው ስለመሆኑ በዮሐንስ 5:22-23 ላይ እንደሚከተለው ተገልፆ እናገኛለን፦ *«ሰዎች ሁሉ አብን እንደሚያከብሩት ወልድን ያከብሩት ዘንድ፥ ፍርድን ሁሉ ለወልድ ሰጠው እንጂ አብ በእንድ ሰው አንኳ አይፈርድም። ወልድን የማያከብር የላከውን አብን አያከብርም።»*

ከዚህም በተጨማሪ ጌታችን ራሱ በዚሁ በዮሐንስ ወንጌል 5:26-27 ላይ የሚከተለውን እንደተናገረ እናያለን፦ *«አብ በራሱ ሕይወት እንዳለው እንዲሁ ደግሞ ለወልድ በራሱ ሕይወት እንዲኖረው ሰጥቶታልና። የሰው ልጅም ስለሆነ ይፈርድ ዘንድ ሥልጣን አለው።»*

በዚህ ላይ የፈራጅነቱ ሥልጣን ለወልድ የተላለፈበት ሁለት ምክንያት

1. የፍርዱ ሥልጣን ፈራጁ ያለውን ክብር ያሳያል። በዚህም መንገድ ለሰች ሁሉ ለእግዚአብሔር አብ የሚያሳዩትን ክብር ለእግዚአብሔር ወልድም ማሳየት አለባቸው።

2. ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ ሁሉ የለው ልጅም ነው። በዚህም የለውን ባህርይ ይካፈላል። የለውን ድካምና ፈተና ስለሚያውቅ በፍርዱ ፍትህ ያደርጋል።

ያም ሆኖ ግን ልክ እንደ አባቱ እንደ እግዚአብሔር አብ ሁሉ፥ እግዚአብሔር ወልድም መሐሪና ይቅር ባይ እንዲሁም አዛኝና ሩኅሩኅ በመሆኑ የፍርድን ተግባር በተራው ለእግዚአብሔር ቃል በማስተላለፍ ሰጥቷል።

ስለዚህም ነው ጌታችን ኢየሱስ በዮሐንስ 12:47-48 ላይ እንደሚከተለው የተናገረው፦ *«ዓለምን ላድን እንጂ በዓለም ልፈርድ አልመጣሁምና ቃሌን ሰምቶ የማይጠብቀው ቢኖር የምፈርድበት እኔ አይደለሁም። የሚጠላኝ ቃሌን የማይቀበለው እርሱ የሚፈርድበት አለው፤ እኔ የተናገርኩት ቃል እርሱ በመጨረሻው ቀን ይፈርድበታል።»*

ይህ እንግዲህ በእዲስ ኪዳን ብቻ ሳይሆን በብሉይ ኪዳንም ጭምር የተረጋገጠ ለመሆኑ ደግሞ ዳዊት የእግዚአብሔርን የጻድቅነት ፍርድ በሚከተሉት ቃላት እንደተናገረ በመዝሙር 118:160 ላይ ሠፍሮ እናገኛለን፦ *«የቃልህ መጀመሪያ እውነት ነው። የጽድቅህም ፍርድ ሁሉ ለዘላለም ነው።»*

እንግዲህ ከእነኝህ ጥቅሶች በግልጽ የምንረዳው የእግዚአብሔር ፍርድ በቃሉ ውስጥ የታቀፈ ስለመሆኑ ነው። በመሆኑም ቃሉ የማይሻር የማይለወጥ እንደመሆኑ መጠን ፍርዱም ዘላለማዊ ይሆናል ማለት ነው።

በቃሉ ለሚከናወነው ፍርድ አራቱ መመሪያዎች

በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ የተገለጡት የመለኮታዊ ፍርድ መመሪያዎች ምን ምን ናቸው? ጳውሎስ በሚከተለው መልኩ ሊጠቃለሉ የሚችሉትን እነዚህን መመሪያዎች ይዘረዝራል። በመጀመሪያ ጳውሎስ እግዚአብሔር በእውነት መሠረት ይፈርዳል ይላል። *«ስለዚህ፥ አንተ የምትፈርድ ሰው ሁሉ ሆይ፤ የምታመካኝው የለህም፤ በሌላው በምትፈርድበት ነገር ራስህን ትኮንናለህና፤ እንተው ፈራጅ እነዚያን ታደርጋለህና። እንደዚህም*

በሚያደርጉት ላይ የእግዚአብሔር ፍርድ ዕውነተኛ እንደሆነ እናውቃለን::» ሮሜ2:1-2

ጳውሎስ በዚህ መልእክቱ በቅድሚያ የኃይማኖት ሰው ነን የሚሉትን እንደምን በሌሎቹ በሚፈርዱበት ዓይን በራሳቸው ለመፍረድ ፈቃደኛ አለመሆናቸውን በማጋለጥ ጽፏል:: ይህም እውነት ከሆነው ከማይሻርና ከማይሰወጠው ከእንዱ ከእግዚአብሔር ቃል ውጪ ስለመሆኑ አበክሮ አስገንዝቧል::

ኢየሱስ ራሱ ለአብ *«ቃልህ እውነት ነው»* ብሏል:: ዮሐንስ 17:17 ይህ የሚገልጠው የእግዚአብሔር እውነት *መ*መዘኛ ልክ እንደሚፈረድበት ሰው ሁሉ በሚፈርደውም ላይ እንደሚውል ነው:: ,

በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ እግዚአብሔር ማንኛውንም ሰው እንደሥራው እንደሚፈርድበት ገልጾአል::

በምዕራፍ 2:6 ጳውሎስ፤ *«እርሱ ለእያንዳንዱ እንደሥራው ያስረከበዋል»* በማለት በማጠናከር እንዳሳሰበ እናስተውላለን::

እንደዚሁ ሁሉ በራዕይ 20:12 ላይ የሚከተለውን እናነባለን:- *«ሙታንንም ታናናሾችንና ታላላቆችን በዙፋኑ ፊት ቆመው አየሁ፥ መጻሕፍትም ተከፈቱ፤ ሌላ መጽሐፍም ተከፈተ እርሱም የሕይወት መጽሐፍ ነው:: ሙታን በመጻሕፍት ተጽፎ እንደነበረ እንደሥራቸው መጠን ተከፈሉ::»*

ከዚህ ጋር በተገናኘ «መጻሕፍት» የሚለው ቃል አትኩሮትን የሚስብና ሌላ ሐሳብ የሚያጭር ነው:: መጽሐፍ ማለት በአንድነት የተጠረዙ ገጾች ስብስብ ነው:: በመጀመሪያው አዲስ ኪዳን ዘመን መጽሐፍ በብራና ወይም በሌላ ዕቃ የሚሠራና ተጠቅልሎ የሚቀመጥ ነበር:: እንዲህ ዓይነቱ ጥቅልል በራዕይ መጽሐፍ ላይ በምሳሌነት እንደተጠቀሰው ተከታታይ የሆኑ ሰባት ማህተሞች ይኖሩታል::

በዘመናዊ ቴክኖሎጂ ከተፈበረኩት ውስጥ ከጥንታዊው ጥቅልል ጋር ተመሳሳይነት ያለው ኤሌክትሮ ማግኔቲክ መቅረጫ ቴፕ ነው:: ይህ ቴፕ እንደጥንታዊው ጥቅልል ተጠቅልሎ የሚቀመጥ ሲሆን በውስጡ ያሰውን ለመለማት ደግሞ በማጫወቻው አማካኝነት ጥቅልሉ ይፈታል:: ይህን በአእምሮአችን በማድረግ ስለ እያንዳንዱ ሰው መላ ሕይወት የተቀረጸበት መጽሐፍ በሰማይ መኖሩን እንመለከታለን:: በዚህ መጽሐፍ መሠረት የእያንዳንዱ ሰው ሥራ በዚህ ሰማያዊ ጥቅልል ሰፍሯል:: አንድ ቀንም ለፍርድ ይቀርባል::

ይህ ቃል የሚፈርደው ደግሞ በውጪያዊው ምግባራችንና ሁኔታችን ብቻ ሳይሆን በውስጣችንም በምንጠነሰሰው ተንኮልና መሰሪነት ጭምር ለመሆኑ ጳውሎስ በሮሜ 2:6 ላይ እንደሚከተለው ገልጾታል:- *«እርሱ ለእያንዳንዱ*

እንደ ሥራው ያስረክበዋል:: ..... ለእውነት በማይታዘዙትና በአድመኞች ላይ ግን ቁጣና መቅሰፍት ይሆንባቸዋል:: ስለዚህም በጨለማ የተሰወረውን ደግሞ ወደ ብርሃን የሚያወጣ የልብንም ምክር የሚገልጥ ጌታ እስኪመጣ ድረስ ጊዜው ሳይደርስ አንዳች አትፍረዱ፤ በዚያን ጊዜም ለእያንዳንዱ ምስጋናው ከእግዚአብሔር ዘንድ ይሆናል::» 1ኛ ቆሮንቶስ 4:5

ይህንኑ ተመሳሳይ እውነት ማለትም የእግዚአብሔር ቃልን ፈራጅነት የሚያስገነዝበን በዕብራውያን 4:12-13 ላይ የሰፈረው ቀጣዩ መልዕክት ነው::

«የእግዚአብሔር ቃል ሕያው ነውና፥ የሚሠራም ሁለትም አፍ ካለው ሠይፍ ሁሉ ይልቅ የተሳለ ነው ነፍስንና መንፈስን ጅማትን ቅልጥምንም እስኪለይ ድረስ ይወጋል፥ የልብንም ሰሚትና አሳብ ይመረምራል፤ እኛን በሚቆጣጠር በእርሱ ዓይናቸ ፊት ሁሉ ነገር የተራቆተና የተጋለጠ ነው እንጂ በእርሱ ፊት የተሰወረ ፍጥረት የለም::»

ስለሆነም የለምችን ተግባር የሚመዘገበው የእግዚአብሔር የፍርድ መጽሐፍ የሚመዘገበው ውጫዊ የሚታየውን ተግባር ብቻ ሳይሆን ጥልቅ የሆነውን የልባቸውን ዝንባሌ፥ የልባቸውንና የአይምሯቸውን መሻት ጭምር ነው:: በሰዎች ላይ የእግዚአብሔር ፍርድ እንደ ሥራቸው የሚሆነው እነዚህን ሁሉ በማጠቃለል ነው::

ሦስተኛው የእግዚአብሔር ፍርድ *መ*መሪያ በሮሜ 2:11 ላይ ተቀምጧል:: *«እግዚአብሔር ለለው ፊት አያደላም»* አያደላም የሚለው ቃል ልዩነት አያደርግም የሚል ሃሳብ አለው:: ይህም አገላለጥ የሚያመለክተው እግዚአብሔር በሚፈርድበት ጊዜ በሰው ውጪአዊ ባህርይ ላይ የሚመረኮዝ አለመሆኑን ነው:: ምክንያቱም አፍአዊ ድርጊቱ የሰውን እውነተኛ ባህርይና አኗኗር የግድ ስለማያመለክት ነው:: ሰዎች ብዙውን ጊዜ በፍርዳቸው ውስጥ አፍአዊ በሆኑ ነገሮች ለምሳሌ እንደ ዘር፤ ኃይማኖት፥ ሥራ፥ በኀብረተሰብ ውስጥ ባላቸው ቦታ፥ በተከሰ ሰውነት፥ በሃብት፥ በትምህርትና በሌሎችም ላይ ይመሰረታሉ:: ሆኖም የእግዚአብሔር ፍርድ ግን በእነዚህ ነገሮች ምክንያት አይጣመምም በእነርሱ ተጽዕኖ ሥርም አይወድቅም::

«ሰው እንዳያይ እግዚአብሔር አያይምና . . . ሰው ፊትን ያያል፥ እግዚአብሔር ግን ልብን ያያል::» 1ኛ ሳሙኤል 16:7

በሰዎች ሁኔታ የማይለዋወጠው እግዚአብሔር ብቻ አይደም:: እርሱ ራሱ በሰዎች ላይ ለመፍረድ የሚቀመጡ ሁሉ እንዲህ ዓይነት ተፅዕኖ ሥር እንዳይወድቁ በጥብቅ አዝዟል:: ይህም ዘጠኝ ጊዜ በብሉይ ኪዳን ሰባት ጊዜ በአዲስ ኪዳን ታዝዟል::

አራተኛው የእግዚአብሔር የፍርድ *መ*መሪያ *«በብርሃን መሠረት ነው»* ይህም በሮሜ 2:12 ላይ ተገልጦአል:: *«ያለ ሕግ ኃጢአት ያደረጉ ሁሉ ያለ*

ሕግ ደግሞ ይጠፋሉ፤ ሕግም ሳላቸው ኃጢአት ያደረጉ ሁሉ በሕግ ይፈረድባቸዋል።» ይህ ማለት ሰው ሁሉ አብርሃምን በሥነ ምግባር መለኪያነት አብርሃምን እንደሚፈርድበትና ይህንንም ማስተዋል እንደተሰጠው ያመለክታል። በሙሴ ሕግ በኩል ሙሉው የእግዚአብሔር የሥነ ምግባር ሕግ የተገለጠላቸው በዚያው ሕግ ይፈረድባቸዋል። ነገር ግን ሙሉውን የሙሴ ሕግ መገለጥ የሌላቸው በዚያው በሙሴ ሕግ ይፈረድባቸዋል። ነገር ግን የሚፈረድባቸው እግዚአብሔር ለሰው ዘር ሁሉ በፍጥረት በኩል በሰጠው አጠቃላይ መገለጥ አማካኝነት ነው። *«የማይታየው ባህርይ እርሱም የዘላለም ኃይሉ ደግሞም አምላክነቱ ከዓለም ፍጥረት ጀምሮ ከተሠሩት ታውቆ ግልጥ ሆኖ ይታያልና»* ሮሜ 1:20።

በዚህ ቦታ ላይ ጳውሎስ የሚናገረው በአጠቃላይ መገለጥ በኩል የሚታወቀውን የእግዚአብሔርን ባሕርይ ነው። ይኸውም ዘላለማዊ ኃይሉና እምላክነቱ በፍጥረቱ በኩል በየትም ቦታ ለሰዎች ሁሉ ዘርና ኃይማኖት ሳይለይ ማንም ሰው እንዲያስተውለው ነው።

ስለዚህም ይህ አጠቃላይ መገለጥ ሁሉም ሰዎች ፍርድ የሚቀበሉበት መሠረታዊ መመዘኛ ነው። ሆኖም ተጨማሪ ልዩ መገለጥ በእግዚአብሔር በኩል የተቀበሉ በተሰጣቸውና በሚበልጠው የሞራል እውቀት መመዘኛ ይፈረድባቸዋል። ስለሆነም ፍርድ የሚሆነው ለሰው ሁሉ በተሰጠው በሥነ ምግባር እውቀት መለኪያ ብርሃንነት ነው።

ይኸው መመሪያ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዘሙኑ ለነበሩ ሰዎች በተናገራቸው ቃላት ተገልጾአል።

«በዚያን ጊዜ የሚበዙ ተዓምራት የተደረገባቸውን ከተሞች ንስሐ ስላልገቡ ሊነቅፋቸው ጀመረ፤ እንዲህም አለ፦ ወዮልሽ ኮራዚ፥ ወዮልሽ ቤተ ሳይዳ፥ በእናንተ የተደረገው ተዓምራት በጢሮስና በሲዶና ተደርጎ ቢሆን ማቅ ለብሰው አመድም ነስንሰው ከብዙ ጊዜ በፊት ንስሐ በገቡ ነበር። ነገር ግን እላችኋለሁ፥ በፍርድ ቀን ከእናንተ ይልቅ ለጢሮስና ለሲዶና ይቀላቸዋል። አንቺም ቅፍርናሆም እስከ ሰማይ ከፍ አልሽን? ወደ ሲዖል ትወርጂያለሽ፤ በአንቺ የተደረገው ተዓምራት በሰዶም ተደርጎ ቢሆን፥ እስከ ዛሬ በኖረች ነበር። ነገር ግን እላችኋለሁ በፍርድ ቀን ከአንቺ ይልቅ ለሰዶም አገር ይቀልላታል።» ማቴዎስ 11:20-24።

ኢየሱስ በዚህ ሥፍራ የገለጠው ኃጢአተኞች የነበሩት የጢሮስ፥ የሲዶናና የሰዶም አገሮች ሁሉ በተገለጠላቸው እውነት መሠረት እንደሚፈረድባቸው ነው። በሌላ ጎኑ ደግሞ በእርሱ ዘመን የነበሩት ኮራዚን፣ ቤተ ሳይዳና ቅፍርናሆም ጌታ ኢየሱስ ራሱ ተገኝቶ በገለጠው እውቀትና አገልግሎት መሠረት ይፈረድባቸዋል። ከዚህም የተነሳ በኋለኞቹ ከተሞች ላይ የሚመጣው ቁጣ በፊት ከተጠቀሱት የባሰ ነው። ይህንን መመሪያ ወደ ዘመናችን ሶር ዉጣው የሚፈረድብን በዘመናችን በተገለጠልን ብርሃንና እውቀት

መሆኑ ግልጽ ነው። በተለይ የብዙ ዓመታት የክርስትና ታሪክ ተሸክመን በምንኖር በኢትዮጵያውያን በምድር ላይ ከተፈጸሙ ታሪኮች በላቀ ሁኔታ የክርስትና ብርሃን በመብራቱ ፍርዳችንም የዚያኑ ያህል ነው። ከዚህም የተነሳ የሚፈረድብን በዚያው መጠን ይሆናል። የሚከተሉት የጌታ ኢየሱስ ቃላት ለእኛ ትውልድ የሚያስተላልፉት መልዕክት አለ፦ *«ብዙም ከተሰጠው ሰው ሁሉ ከእርሱ ብዙ ይፈለግበታል ብዙ አደራም ከተሰጠው ከእርሱ አብዝተው ይሹበታል።»* ሉቃስ 12:48

እንግዲህ እነዚህን ከመሳሰሉት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ማስረጃዎች በመነሳት የምንደመድመው የእግዚአብሔር ቃል በእነዚህ አራት መመሪያዎች መሠረት ፍርድን እንደሚያስተላልፍ ነው።

1ኛ፦ በእውነት መሠረት
2ኛ፦ በምግባር መሠረት
3ኛ፦ ያለ አድልዎ
4ኛ፦ በተገለጠላቸው ብርሃን መጠን ይፈርዳል።

49

የእግዚአብሔር ፍርድ በታሪክ ውስጥ

በምዕራፍ 48 ላይ ስለ መለኮታዊ ፍርድ አጠቃላይ መመሪያዎች ከተነጋገርን እግዚአብሔር በሰዎች ላይ ፍርድን የሚያስተላልፈው በዘፈቀደ ሳይሆን በሁለት ደረጃ በተከፋፈለ መልኩ ለመሆኑ ደግሞ እንደሚከተለው እናያለን::

ጊዜያዊው ፍርድ ከዘላለማዊው ፍርድ ጋር ሲነፃፀር

ከሁለቱ የፍርድ ደረጃዎች የመጀመሪያው በተወሰነ የጊዜ ገደብ ውስጥ ወይም በሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ የሚፈጸም ነው:: ሁለተኛው ግን በጊዜው ያልተገደበና በዕብራውያን 6:2 ላይ (ዘለዓለማዊ ፍርድ) ተብሎ የተገለጸው ነው:: በመሆኑም ይህ ሁለተኛው ፍርድ ከሰው ልጆች ታሪካዊ ሂደት ጋር ግንኙነት የሌለው፥ ታሪክና ዘመን ከተዘጋ በኋላ በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ የሚፈጸም ነው::

ተቀዳሚው ዓላማችን መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ዘለዓለማዊ ፍርድ የሚያስተምረውን ለመመርመር ነው:: ሆኖም ግን በታሪክ ውስጥ የእግዚአብሔርን ፍርድ በመመርመር መጀመሩ ጠቃሚ ይሆናል:: በዚህ

መንገድ መጽሐፍ ቅዱሳዊና አመክንዮአዊ (ሎጂክ) በሆነውና የእግዚአብሔር ፍርድ በታሪክ ውስጥ እና የእግዚአብሔር ፍርድ በዘለዓለም ያላቸውን ልዩነት በጥንቃቄ ስንመረምር ነው:: እርስ በእርሳቸው የሚቃረኑ የሚመስሉትን አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባባት ማስታረቅ እንችላለን:: ለምሳሌ እግዚአብሔር እስራኤላውያንን በማስጠንቀቅ የሰጣቸውን የሚከተለውን ትዕዛዝ እንመለከት:- *«ከላይ በሰማይ ካለው፥ በታችም በምድር ካለው ከምድር በታች በውኃ ካለው ነገር የማናቸውንም ምሳሌ፥ የተቀረጸውን ምስል ለአንተ አታድርግ አትስገድላቸው፥ አታምልካቸውምም፥ በሚጠሉኝ እስ ሦስትና አራተኛ ትውልድ ድረስ የአባቶችን ኃጢአት በልጆች ላይ የማመጣ፥ ለሚወዱኝ ትዕዛዜንም ለሚጠብቁ እስከ ሺህ ትውልድ ድረስ ምሕረትን የማደርግ እኔ እግዚአብሔር አምላክህ ቀናተኛ አምላክ ነኝና::»* ዘፀአት 20:4-9::

ኤርምያስ እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን የሰጣቸውን ቃል ኪዳንና ማስጠንቀቂያ እንደገና ያስታውሳል:: *«ለብዙ ሺህ ምህረት ታደርጋለህ፥ የአባቶችንም በደል ከእነርሱ በኋላ በልጆቻቸው ብብት ትመልሳለህ ስምህ ታላቅና ኃያል አምላክ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ነው::»* ኤር. 32:18

እነዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባባትና እነርሱን የመሰሉ ሌሎችን ምንባባት ግልጽ እንደሚያደርጉት በተወሰኑ ምክንያቶች የአንድ ትውልድ ኃጢአቶች በሚቀጥሉት ሦስትና አራት ትውልዶች ላይ የእግዚአብሔር ፍርድ እንዲመጣ ምክንያት እንደሚሆኑ ነው:: በተቃራኒው ደግሞ የአንድ ትውልድ ጽድቅ በሺዎች ለሚቆጠሩ የእነርሱ ዘሮች በረከት ማግኘት ምክንያት እንደሚሆን ነው:: እነዚህ ምንባባት እንደሚያመለክቱት የእግዚአብሔር ፍርድ በጊዜያት ማለትም በታሪክ ውስጥ እንደሚሆን ነው::

ስለእግዚአብሔር አጠቃላይ ፍርድ የተሟላ ምስል እንዲኖረን ስለ እግዚአብሔር ዘላለማዊ ፍርድ የሚያወሱ አንዳንድ የመጽሐፍ ጥቅሶችን እንመለከታለን:: በዚህም ረገድ በቅድሚያ የምንመለከተው በትንቢተ ሕዝቅኤል 18:1-4 ላይ የሰፈረውን ይሆናል:- *«የእግዚአብሔርም ቃል ወደ እኔ እንዲህ ሲል መጣ ስለ እስራኤል ምድር አባቶች ጮርቃ የወይን ፍሬ በሉ፥ የልጆችም ጥርሶች ጠረሱ፥ ብላችሁ የምትመስሉት ምሳሌ ምንድር ነው? እኔ ሕያው ነኝና ከእንግዲህ ወዲህ ይህም ምሳሌ በእስራኤል ዘንድ አትመስሉትም፥ ይላል ጌታ እግዚአብሔር እነሆ፥ ነፍሳት ሁሉ የእኔ ናቸው፥ የአባት ነፍስ የእኔ እንደሆነች ደግሞ የልጅ ነፍስ የእኔ ናት፤ ኃጢአት የምትሠራ ነፍስ እርስዋ ትጠፋለች::»*

ከዚህ ጥቅስ የምንረዳው እንደምን እስራኤላውያን በደለኛነታቸውና ኃጢአታቸው በአባቶቻቸው ላይ ለማመካኘት መሞከራቸውንና ነገር ግን ይህ በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት እንዳጣ ነው:: ምንም እንኳን ለእጠቃላዩ ለእስራኤል ድክመት የወላጆች እጅ ያለበት ቢሆንም፥ ዳሩ ግን እያንዳንዱ እስራኤላዊ በእግዚአብሔር ዘንድ የሚጠየቀው በየግል እምነቱና ምግባሩ ነው:: እሁንም ሕዝቅኤል በ18:20 ላይ በማጠናከር የገለጸው ይህን መለሱን እውነታ

ነበር፡- *«ኃጢአትን የምትሠራ ነፍስ እርስዋ ትሞታለች፥ ልጅ የአባቱን ኃጢአት አይሸከምም፥ አባትም የልጁን ኃጢአት አይሸከምም፥ የጻድቁ ፅድቅ በራሱ ላይ ይሆናል፥ የኃጢአተኛውም ኃጢአት በራሱ ላይ ይሆናል።»*

ከዚህ የምንረዳው እንግዲህ የእግዚአብሔር ፍርድ በጭፍልቁ በአንድ ሕዝብ ወይም መንግሥት ላይ ላይሆን በእያንዳንዱ ግለሰብ ላይ መሆኑን ነው። ያን መስሉም ፍርድ ዘላለማዊነት ያለው ይሆናል። ይህንንም በማብራራት ነው እንደገና ሕዝቅኤል በቁጥር 24 ላይ የሚከተለውን የሚለን፡- *«ጻድቁ ግን ከፅድቁ ቢመለስ ኃጢአትንም ቢሠራ ኃጢአተኛውም እንደሚያደርገው ርኩሰት ሁሉ ቢያደርግ፥ በሕይወት ይኖራልን? የሠራት ፅድቅ ሁሉ አትታሰብለትም፤ ባደረገው ዓመፅና ኃጢአት በዚያች ይሞታል።»*

የጥቅሱ ማጠቃለያ ቃላት ማለትም «በሠራት ኃጢአት በዚያች ይሞታል» የሚያመለክተው እያንዳንዷ ነፍስ ከጊዜ ወደ ዘላለም በምን ሁኔታ እንደምትሻገር እግዚአብሔር መናገሩን ነው። በዚህ ቅጽበት ያለው የነፍስ ሁኔታ በዘላለም ውስጥ ያለውን ሁኔታዋን ይወስናል። አሁን በኃጢአት የሞተች ነፍስ በዘላለም ውስጥ በእግዚአብሔር ሕልውና ዘንድ ልትገኝ አትችልም። በመከብብ የተቀመጠው የሚወድቅ ዛፍ ምስል ይሄንኑ እውነታ የሚገልፅ ነው። *«ዛፍም ወደ ደቡብ ወይም ወደ ሰሜን ቢወድቅ ዛፉ በወደቀበት በዚያ ይኖራል።»* መክብብ 11:3

የዛፉ መውደቅ የሚሞት ሰውን ያመለክታል። ዛፉ የወደቀበት አቅጣጫ የት እንደሚጋደም ይወስናል። ሰው የሚሞትበት ሁኔታ ማለትም በሞቱ ጊዜ የነፍሱ ሁኔታ በዘላለም ውስጥ የሚኖረውን ሁኔታ ይወስናል። በዚህ አኳኋን እያንዳንዷ ነፍስ ለራሷ ብቻ እና ስለ ራሷ ሁኔታ መልስ ትሰጣለች፤ ኃላፊነትም አለባት። በሕዝቅኤልና በመክብብ ላይ ያየናቸው እነዚህ ምንባባት በእያንዳንዱ ሰው ላይ የእግዚአብሔር ዘላለማዊ ፍርድ እንዴት እንደሆነ ያሳያል። የእያንዳንዱ ሰው መዳረሻ የሚወሰነው በሞቱ ጊዜ ያለው ሁኔታ ነው። በሌላ በኩል ከአራት ዘጸአትና ከትንቢተ ኤርምያስ በመጥቀስ ያሰፈርናቸው ሁለት ጥቅሶች በታሪክ ውስጥ እግዚአብሔር ከትውልድ ወደ ትውልድ፥ በቤተሰብ፥ በሃገርና በዘሮች ሁሉ የሚያከናውነውን ፍርድ ያመለክታሉ።

በእነዚህ ምንባባት ብርሃንነት ስንመለከት በሁለቱ የእግዚአብሔር ፍርድ አቀራረቦች መካከል ተቃርኖ እንደሌለ እያናለን። በታሪክ ውስጥ የአንድ ትውልድ ባህርይው በሚቀጥሉት ትውልዶች ላይ በንም ይሁን ክፉ ተጽዕኖ አለው። ይህ እግዚአብሔር በታሪክ ውስጥ የሚፈርደው ፍርድ አካል ነው። በዘላለም ውስጥ ግን ማለትም ጊዜያትና ታሪክ ከተዘጉ በኋላ እያንዳንዱ ሰው ስለራሱ ጠባይና አኗኗር ብቻውን ለእግዚአብሔር መልስ ይሰጣል። ማንም ሰው በሌላው ሰው ጽድቅ አይጸድቅም። በሌላው ሰው ኃጢአትም አይኮነንም። ይህ በዘላለም ውስጥ የእግዚአብሔር ፍርድ ነው።

የታሪካዊ ፍርድ ምሳሌዎች

በመቀጠልም እግዚአብሔር ስላስተላለፋቸው እንዳንድ ታሪካዊ ፍርዶች ከመጽሐፍ ቅዱስ አለፍ አለፍ ብለን በመጥቀስ እንመለከታለን። በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ እንደነዚህ ዓይነት ፍርዶች የተመዘገቡ ሲሆን በተወሰኑ የኃጢአት ድርጊቶች ወይም ሁኔታዎች የእግዚአብሔርን ዝንባሌ የሚያመለክቱና ግልጽና ተውኔታዊ በሆነ መንገድም ለሚቀጥሉት ትውልዶች እነዚህን ዓይነት ኃጢአቶች ለመከተል እንዳይፈተኑ በማስጠንቀቂያነት የሚያመለክቱ ናቸው። ለዚህም በመግቢያነት የመጽሐፍ ቅዱስ የመጀመሪያው ክፍል ከሆነው ከአሪት ዘፍጥረት 19:24-25 እንደሚከተለው እንጠቅሳለን፡- *«እግዚአብሔርም በሰዶምና በገሞራ ከእግዚአብሔር ዘንድ ከሰማይ አሳትና ዲን አዘነበ፥ እነዚያንም ከተሞች በዙሪያቸው ያለውን ሁሉ የምድሩንም ቡቃያ ገለበጠ።»*

የእዲስ ኪዳን ጸሐፊዎችም ይህንን ሁኔታ በተደጋጋሚ ጠቅሰውታል፡- *«(እግዚአብሔር) ኃጢአትንም ያደርጉ ዘንድ ላሉት ምሳሌ ለድርጎ ከተማዎችን ሰዶምንና ገሞራን አመድ እስኪሆኑ ድረስ አቃጥሎና ገልብጦ (ፈረደባቸው)» 2ኛ ጴጥሮስ 2:6።*

ጴጥሮስ የሚያመለክተን የሰዶምና የገሞራ ድንገተኛና ፍጹማዊ አወዳደቅ እነዚህ ከተሞች ለሰሩት ኃጢአት ያለውን የእግዚአብሔርን አመለካከት የሚያሳዩ ተደርገው የተቀመጡ ምሳሌዎች ናቸው። ሕዝቅኤል በሚያስገርም ሁኔታ ለሰዶም ውድቀት ምክንያት የሆኑትን ማህበራዊና ሥነ ምግባራዊ ሁኔታዎች እግዚአብሔር ለኢየሩሳሌም በተናገረው ንግግር ውስጥ አስቀምጦአል። *«እነሆ የእህትሽ የሰዶም ኃጢአት ይህ ነበረ፥ ትዕቢት አንጀራን መጥገብ፥ መዘለልና ሥራ መፍታት በአርስዋና በሴቶች ልጆችዋ ነበረ። የችግረኛውንና የድሃውን እጅ አላጸናችም።»* ሕዝቅኤል 16:49

ከዚህ የምንረዳው፥ ለሰዶም የሥነ ምግባር ውድቀት እራት ምክንያቶች እንዳሉ ነው። እነርሱም ትዕቢት፥ ጥጋብ፥ ሥራ መፍታት፣ ለድሆች አለመጨነቅና በመካከላቸውም ሳሉ መጨቆናቸው ናቸው። ይህ መሰሉ ጥጋብ ነበር ለዶምን ለዚያ መሰሉ ጸያፍ የወሲብ ኃጢአት ያደረሳት። እነሆም ኃጢአቱም «ግብረ ሰዶም» ተብሎ በታሪክ ሲዘከር ለመቆየት የበቃው ከዚሁ ከስተማዋ ልቅና ጸያፍ ምግባር በመነሣት ነበር።

እጅግ አስደናቂ የሆነው የመጽሐፍ ቅዱስ ትክክለኛነት፥ በዘመናዊ ሥልጣኔዎቻችን ማዕከላት በሆኑ ከተሞች ተመሳሳይ የሆኑት ማህበራዊና ሥነ ምግባራዊ ኃጢአቶች ተመሳሳይ የሆኑ ወሲባዊ ኃጢአቶችን እያፈሩ እንደሆነ አንድ ጊዜ እንደገና እረጋግጦልናል። መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ዓይነቱ ኃጢአት ተመሳሳይ የሆነ ፍርድን ሁልጊዜ እንደሚያመጣ አይናገርም። ነገር ግን ስለነዚህ ኃጢአቶች እግዚአብሔር የማይለወጥ አመለካከት እንዳለውና ለእንዴና

ለሁልጊዜ ለዶምን በፈረደባት ፍርድ እንደሚገለጥ ያስተምረናል። በዚህ በተገለጠው የእግዚአብሔር ፍርድ ብርሃንነት ወደዚህ ዓይነት ኃጢአት የሚመለሱ ሁሉ ያለምንም ይቅርታ ይጣላሉ። ምንም እንኳ ግልጥ የሆነ የእግዚአብሔር ፍርድ በታሪክ ውስጥ ባይደርስባቸውም በዘላለም ውስጥ ያለው ፍርዳቸው እጅግ አስፈሪ ነው።

ሌላው የእግዚአብሔር ፍርድ የተገለጠው በአናንያና በሰጲራ ታሪክ ውስጥ ነው (ሐዋርያት ሥራ 5:1-10 ተመልከት)። አናንያና ሚስቱ ሰጲራ እኛ ሃይማኖታዊ ግብዞች እንደምንላቸው ያሉ ነበሩ። ያላቸውን ንብረት ሸጠው በኋላ የዋጋውን ግማሽ ለእግዚአብሔር ሥራ እንደ ሥጦታ ወደ ሐዋርያት አመጡ። ይህ በራሱ የሚደገፍ ነው። ሆኖም ግን እንደ ኃጢአት የተቆጠረባቸው የሸጡትን ሙሉ ዋጋ ማምጣት አለመፈለጋቸው ነው። ግማሹንም ያመጡት ውዳሴና መገለ ከሐዋርያትና ከሌሎችም ክርስቲያኖች ለማግኘት ነበር።

ሆኖም ግን ልዕለ ተፈጥሯዊ በሆነ የመንፈስ ቅዱስ መገለጥ ጴጥሮስ ግብዝነታቸውን አወቀባቸው። በመቀጠልም በመጀመሪያ አናኒያ ቀጥሎም ሰጲራ በውሸታቸውና መንፈስ ቅዱስን ለማታለል በመሞከራቸው ወቀሳቸው። ይህ የኃጢአት ወቀሳ በላያቸው ላይ ሲመጣ እያንዳንዳቸው በጴጥሮስ እግር ሥር ወድቀው ሞቱ። ይህን የእግዚአብሔር ፍርድ በለሙት ለምች ሁሉ ላይ ታላቅ ለውጥን አምጥቷል። *«በቤተ ክርስቲያን ሁሉና ይህንም በሰሙ ሁሉ ላይ ታላቅ ፍርሃት ሆነ»* የሐዋርያት ሥራ 5:11።

በእርግጥ እግዚአብሔር ይህን ዓይነት ባህርይ የሚያሳዩ ክርስቲያኖችን ሁል ጊዜ በዚህ ዓይነት ሁኔታ እንደሚቀጣ የሚያመለክት ነገር የለም። ነገር ግን በሐሰትና በግብዝነት ላይ የእግዚአብሔር የማይለወጠው አመለካከት በዚህ ሁኔታ መገለጡ ለሚቀጥሉት የቤተ ክርስቲያን ትውልዶች እንደ ማስጠንቀቂያ ሆኗል።

ወደ እሥራኤል ታሪክ መለስ ስንል ደግሞ፥ ከዚህ መለሱ የሕዝብ ጥጋብና ለባዕድ አምልኮ መገዛት የተነሳ፥ በዚያች አገር ላይ በተከታታይ ታሪካዊ ፍርድ እንደደረሰበት እንረዳለን። ለምሳሌ በዘሌዋውያን ምዕራፍ 26 ላይ እንደለፈረው፥ ምንም እንኳን እግዚአብሔር እስራኤላውያንን ከኃጢአታቸው እንዲመለሱ ቢያስጠነቅቃቸውም አሻፈረን በማለታቸው፥ ቤት ንብረታቸውን ለቀው እንዲሰደዱ ወስኖባቸው ነበር። በተለይም ስለዚህ ስለ እግዚአብሔር ፍርድ በማብራራት ከቁጥር 27-33 የለፈሩትን ቃላት እንደሚከተለው እንጠቅሳለን፦ *«አስከዚህ ድረስ ባትሰሙኝ፥ በእንቢተኝነትም ብትሄዱብኝ፥ እኔ ደግሞ በቁጣ እሄድባችኋለሁ፤ ስለ ኃጢአታችሁም ሰባት እጥፍ አቀጣችኋለሁ የወንዶች ልጆቻችሁንም ሥጋ ትበላላችሁ፥ የሴቶች ልጆቻችሁንም ሥጋ ትበላላችሁ። የኮረብታ መስገጃዎቻችሁንም አፈርሳለሁ፥ የፀሐይ ምስሎቻችሁንም አጠፋለሁ፥ ሬሳችሁንም በጣዖቶቻችሁ ሬሳ ላይ እጥላለሁ፥ ነፍሴም ትጸየፋችኋለች። ከተሞቻችሁንም ባድማ አደርጋለሁ፥*

መቅደሶቻችሁንም አፈርሳለሁ፥ መልካሙንም መዓዛችሁን አላሸትትም። ምድሪቱንም የተፈታች አደርጋለሁ፥ የሚቀመጡባት ጠላቶቻችሁም በእርስዋ የተነሳ ይደነቃሉ። እናንተም ከአሕዛብ መካከል እበትናችኋለሁ፥ ሠይፍንም አስመዘዝባችኋለሁ፥ ምድራችሁም የተፈታች ትሆናለች፥ ከተሞቻችሁም ባድማ ይሆናሉ።»

ይህ የዚህ ትንቢት እያንዳንዱ ነጥብ በ70 ዓ.ም. አሥራኤል በሮም ወታደሮች በመወረሯና በሌሎችም ወረራዎች ቃል በቃል ተፈጸሚነት አግኝቷል።

ኢየሩሳሌም በቲቶ በተከበበችበት ወቅት አስራኤላውያን ከረሃባቸው የተነሳ ቃል በቃል የወንዶችና ሴቶች ልጆቻቸውን ሥጋ በልተዋል። ከዚህ በኋላ መለዊያዎቻቸውና የኃይማኖት ማዕከሎቻቸው ሁሉ ተደመሰሱ። በብዙ የሚቆጠሩ ለምችም ተጨፈጨፉ። ሌሎችም በባርነት ተሸጡ፤ በስደት ተበተኑ። በዙሪያቸው የነበሩት አሕዛብ ባድማ የሆነውን መሬት ለመያዝ መጡ። የሚገርመው ደግሞ የእግዚአብሔር ቃል በዚህ መለሱ ትንቢታዊ ፍርድ ሳይገታ፥ ሕዝቡ ከተሠደዱም በኋላ ቢሆን በአሕዛብ መንግሥታት ስለሚፈጸምባቸው ግፍና በደል ጭምር ማተቱ ነው። ይህንንም በዘሌዋውያን 26:36-37 ላይ እንደሚከተለው ለፍሮ እናገኘዋለን፦ *«ለጠላቶቻቸውም ምድሮች ሳሉ ከአናንተ ተሰይተው በቀሩት ላይ በላባቸው ድንጋጤን አሰድድባቸዋለሁ፤ በነፋስም እንደሚሸሹ ይሸሻሉ፥ ማንም ሳያሳድዳቸው ይወድቃሉ።»*

እንግዲህ ታሪክን ጠለቅ ብለን ስንመረምር ይህ ዓይነቱ ድርጊት በእሥራኤል ላይ ተመልሶ መድረሱን እናረጋግጣለን። ይሁን እንጂ ትንቢቱ ከመዘጋቱ በፊት እግዚአብሔር እንደገና ምህረቱን ፈፅሞ ከእሥራኤል እንደማይወስድ ሲናገር እናያለን፦ *«ነገር ግን እኔ እግዚአብሔር አምላካቸው ነኝና እነርሱ በጠላቶቻቸው ምድር ሳሉ፥ አስካጠፋቸው ድረስ ከእነርሱም ጋር ያሰኘኝ ቃል ኪዳን አስካፈርስ ድረስ አልጥላቸውም አልጸየፋቸውምም።»* ዘሌዋውያን 26:44

የእግዚአብሔር የፍርዱ ማስጠንቀቂያ እንደተፈጸመ ሁሉ እንደዚሁ በፍርድ መካከል ቢሆንም እንኳ የምህረቱ ቃል ኪዳን ይፈጸማል። በመጽሐፍ ቅዱስ ተንቢት ብርሃንነትም መላው የአስራኤል ታሪክ በዓለም አቀፍ ደረጃ እግዚአብሔር በፍርድ መካከል እንኳ ምህረትን ማድረግ እንደሚያስደስተው የሚያመለክት የእግዚአብሔርን ፍርድና ምህረት የሚያሳይ ነው። በፍርድ መካከል ስላለው የእግዚአብሔር ምህረት እጅግ አስደናቂ የሆነው ምሳሌ በኢያሱ ምዕራፍ 2 እና 6 የተመዘገበው የረአብ ታሪክ ነው። ከታሪካዊ መሠረቱና ከእካባቢው አንጻር ሁሉም ነገር ረአብን የሚቃወም ነው። ረአብ ሴተኛ አዳሪ ለፍርድ ከተለጠ ዘር የሆነች ለመጥፋት በተዘጋጀ ከተማ የምትኖር ነበረች። ሆኖም በትህትናዋና በእምነቷ ራሷን በእግዚአብሔር ምህረት ላይ መጣል

ፈለገች። በውጤቱ እርሷና መላው ቤተሰብዋ ከጥፋት ዳኑ። ከእሥራኤላዊ ጋር በመጋባትም የኢየሱስ ክርስቶስ የትውልድ ሐረግ ቀጥተኛ አካል ሆነች።

ይህ የረአብ ሁኔታ የሚያሳየን ማናቸውም በቀደመ ታሪኩና በአካባቢው ምክንያት የግድ እንደማይፈረድበት ነው። ያለፈው ጊዜ አስከፊ ጨለማ ቢሆን ያለበት ሁኔታም የቱንም ያህል የተበላሸ ቢሆን፤ ግላዊ የሆነ ንስሐና እምነት ማናቸውንም የእግዚአብሔር ፍርድ ከመሰረዙ በላይ በዚህ ፋንታ የእግዚአብሔርን ምህረት ያስገኛል።

መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚያሳየው፤ ታሪክ የእግዚአብሔር ፍርድና የእግዚአብሔር ምህረት በሰው ሕይወት ውስጥ በሚያከናውኑት ድርጊት የታጀበ ሆኖ እናገኘዋለን። እጅግ አስደንጋጭ በሆኑ ፍርዶች መካከል እንኳ የእግዚአብሔር የማይናወጡ ዓላማዎቹ ጸጋና ምህረት ናቸው። በዚህ ምክንያት በታሪክ ውስጥ የሚሰራው የእግዚአብሔር መገለጥ በመዝሙር 107:43 ላይ ተጠቅሷል፦ *«ጥበበኛ የሆነና ይህን የሚጠብቅ ማነው? እርሱ የእግዚአብሔርን ምህረት ያስተውላል።»*

አማኝ በታሪክ ውስጥ የሚያገኘው ትልቁ ትምህርት የማይለወጠውንና ታማኝ የሆነውን የእግዚአብሔርን የጸጋና የምሕረት ቃል ኪዳን ክንውን መገለጥን ነው። ሆኖም ግን ሙሉ የሆነና አጠቃላይ ፍርድ በሁሉም የሰዎች ተግባር ላይ በታሪክ ውስጥ ይፈጸማል የሚል የስህተት አመለካከት አንዳይኖረን ጳውሎስ በ1ኛ ጢሞቴዎስ 5:24-25 ላይ ያስጠነቅቀናል። *«የአንዳንድ ሰዎች ኃጢአት የተገለጠ ነው። ፍርድንም ያመለክታል። ሌሎች ግን ይከተላቸዋል። እንዲሁም መልካም ሥራ ደግሞ የተገለጠ ነው። ያልተገለጠም ከሆነ ሊሰወር አይችልም።»*

ለዚህም ነው በመጽሐፈ መክብብ 8:11 ላይ፤ *«በክፉ ሥራ ላይ ፈጥኖ አይፈርድም ስለዚህ በሰው ልጆች ውስጥ ልባቸው ክፉን ለመሥራት ጠነከረ»* የሚለው ማስጠንቀቂያ የሰፈረው።

እነዚህ ምንባቦች እንደሚያስጠነቅቁን የእግዚአብሔር ፍርዶች በጊዜ ውስጥ በሙላት አልተገለጡም። ይህም ስለ ኃጢአተኞች ቅጣትና ስለ ጻድቃን ብድራትም ያመለክታል። ስለ እግዚአብሔር አጠቃላይ ፍርድ ሙሉ መገለጥን ለማግኘት ከጊዜ ወደ ዘላለም ማለፍ ይኖርብናል።

50

የክርስቶስ የፍርድ መንበር

ዘላለማዊው ፍርድ በሦስት ራሳቸውን በቻሉ ደረጃዎች እንደሚፈጸም በአዲስ ኪዳን ውስጥ ሰፍሮ እናገኛለን። እነዚህም ሦስት የፍርድ ክንውኖች እርስ በእርሳቸው የሚለያዩት በቅድሚያ ፍርዱን የሚያስተላልፈው ዳኛ ከተቀመጠበት መንበር በመነሳት ነው።

በመጀመሪያው የፍርድ ክንውን ዳኛው የሚቀመጥበት «የክርስቶስ የፍርድ መንበር» ተብሎ ይጠራል። በዚህም ወቅት ለፍርድ የሚቀርቡት የክርስቶስ ተከታዮችና አገልጋዮች ብቻ ይሆናሉ።

በሁለተኛው የፍርድ ክንውን የዳኛው መቀመጫ፤ «የክርስቶስ የክብሩ ዙፋን» በመባል የሚታወቀው ሲሆን በዚህን ወቅት የሚዳኙት ደግሞ የአሕዛብ መንግሥታት ይሆናሉ። ይኸውም የሚፈጸመው በታላቁ የመከራ ዘመን ማብቂያ ላይ ሲሆን ወዲያውኑም በማከታተል የክርስቶስ የሺህ ዓመቱ ምድራዊ መንግሥት ይመሠረታል።

ሦስተኛውና የመጨረሻው የፍርድ መንበር ደግሞ «ታላቁ ነጭ ዙፋን» በመባል የሚታወቀው ሲሆን፥ ይኸውም በሺህ ዓመቱ የምድራዊ መንግሥት ማብቂያ ላይ፥ በትንሣኤ ሙታን የሚነሱት ነፍሳት ሁሉ ለፍርድ የሚቀርቡበት ነው።

በቅድሚያ ክርስቲያኖች ለፍርድ ይቀርባሉ

ይህ በክርስቶስ የፍርድ መንበር ፊት የሚፈጸመው የመጀመሪያው ፍርድ ሲሆን፥ በዚህም ወቅት ለፍርድ ስለሚቀርቡት ክርስቲያኖች በ1ኛጴጥሮስ 4:17-18 ላይ የሚከተለውን ሠፍሮ እናገኛለን፦ *«ፍርድ ከእግዚአብሔር ቤት ተነሥቶ የሚጀምርበት ጊዜ ደርሶአልና፥ አስቀድሞም በእኛ የሚጀምር ከሆነ ለእግዚአብሔር ወንጌል የማይታዘዙ መጨረሻቸው ምን ይሆን? ጻድቅም በጭንቅ የሚድን ከሆነ ዓመጸኛውና ኃጢአተኛው ወዴት ይታይ ዘንድ አለው?»*

በዚህ ቦታ ጴጥሮስ እንደ ክርስቲያን ፍርድ ከእኛ ማለትም ከእግዚአብሔር ቤት ይጀምራል በማለት ይጽፋል። በእነዚህ ሁለት ሐረጎች ክርስቲያኖችን እንደሚያመለክት ግልጽ ነው። ይህንኑ የሚያረጋግጥልን በተቃርኖ የሚያስቀምጣቸው «ለእግዚአብሔር ወንጌል የማይታዘዙ» ማለትም የማያምኑትን ነው። ስለዚህ ጴጥሮስ ግልፅ የሚያደርገው የመጀመሪያው ፍርድ የሚከናወነው ለእውነተኞች ክርስቲያኖች ነው።

ይህ ፍርድ የት እንደሚከናወን ጳውሎስ በተመሳሳይ ቋንቋ በተለያዩ መልዕክታት ሁለት ጊዜ ገልጾታል።

«ለንተም በወንድምህ ላይ ስለምን ትፈርዳለህ? ወይስ አንተ ደግሞ ወንድምህን ስለምን ትንቃለህ? ሁላችን በክርስቶስ ፍርድ ወንበር ፊት እንቆማለንና ..... እንግዲያስ እያንዳንዳችን ስለ ራሳችን ለእግዚአብሔር መልስ እንሰጣለን።» ሮሜ 14:10-12

በእነዚህ ሁለት ቁጥሮች «ወንድምህን» የሚለው ቃል ሁለት ጊዜ ተጠቅሷል። «እያንዳንዳችን» የሚለው ቃል ጳውሎስ የሚናገረው ስለ ክርስቲያኖች ፍርድ እንደሆነ ግልጽ ያደርገዋል። በዚህ ላይ የጳውሎስ ትምህርት እንደ ክርስቲያን አንዳችን በእንዳችን ላይ ለመፍረድ መፈለግ እንደሌለብን ነው። ምክንያቱም ክርስቶስ ራሱ በእያንዳንዳችን ላይ ይፈርዳል፥ እያንዳንዳችንም ለራሱ ለክርስቶስ መልስ እንሰጣለን።

እንደ ሁልጊዜው ይህም ስለ ዘላለማዊ ፍርድ የምንመለከተው ስለሆነ የእያንዳንዱ ግለሰብ ጉዳይ ነው። ጳውሎስ ተመሳሳይ ቋንቋ በመጠቀም ይህን የክርስቲያኖች ፍርድ በሌላ ምንባብ ላይ ገልጾታል።

«መልካም ቢሆን ወይም ክፉ እንዳደረገ እያንዳንዱ በሥጋው የሠራውን ቡድራት ይቀበል ዘንድ ሁላችን በክርስቶስ በፍርድ ወንበር ፊት ልንገለጥ ይገባናልና።» 2ቆሮንቶስ 5:10

እንደገና አውደ ምንባቡና የቋንቋ አጠቃቀም ግልጽ እንደሚያደርግልን ጳውሎስ የሚናገረው ስለ ክርስቲያኖች ብቻ ነው። እዚህም እንደገና በእያንዳንዱ ግለሰብ ላይ አጽንኦት ይሰጣል። ጳውሎስ እንደሚያስቀምጠው ወደ ፍርድ የሚቀርበው እያንዳንዱ ክርስቲያን በምድራዊ ሕይወቱ «በሥጋ የሠራውን» ተግባርና ባሕርይ ነው። ክርስቲያን በዚህ በምድራዊ ሕይወቱ የሚያከናውነው ሁሉ በሁለት እንደሚከፈል ጳውሎስ ያመላክታል። እርሱም «መልካም» ወይም «ክፉ» ነው። ሌላ ሦስተኛ ሁኔታ የሚገለጥ ዋጋ እሰው። ይህም እሉታዊ ወይም እዎንታዊ ሲሆን ይችላል። በእምነትና መታዘዝ የማይገለጥ ነገር ግን ለእግዚአብሔር ክብር ተብሎ የሚቀርብ ማናቸውም ተግባር በእግዚአብሔር ፊት ተቀባይነት ስለማይኖረው ክፉ ነው። በዚህ ግልጥ በሆነ ሃሳብ መሠረት እያንዳንዳችን ክርስቲያኖች በእግዚአብሔር የፍርድ ወንበር ፊት እንደምንቆም እናውቃለን።

በእነዚህ ምንባባት ውስጥ ክርስቶስ በክርስቲያኖች ላይ ስለሚፈርድባቸው ቦታ ሲናገር ጳውሎስ «የክርስቶስ የፍርድ ወንበር» የሚል ሐረግ ይጠቀማል። የፍርድ ወንበር ተብሎ በዚህ ቦታ የተተረጎመው የግሪክ ቃል «ቤማ» ነው። ይህ ቃል የሚያመለክተው ከፍ ያለና ሰሕዝብ ንግግር የሚጠቀሙበትን መድረክ ነው። በሌሎች የአዲስ ኪዳን ምንባባት ቃሉ የሚያመለክተው የሮማ ቄሳር ወይም ተወካዮቹ ችሎት የሚያስችሰበትና ክስ የሚሰሙበትን ቦታ ነው።

ስምላሌ ጳውሎስ እንደ ሮማ ዜግነቱ በንጉሥ ፊት ለፍርድ እንደሚቆም እንዲህ ሲል ተናግሯል፦ *«ለቄሳር ፍርድ ወንበር ፊት ቆሜአለሁ»* (የሐዋርያት ሥራ 25:10)። ጳውሎስ በዚህ ሥፍራ ስለ ፍርድ ወንበር የተጠቀመበትን <ቤማ> የሚለውን ቃል የክርስቶስን የፍርድ ወንበር በተመለከተ ተጠቅሞበታል።

ክርስቲያኖች ለፍርድ ሳይሆን ለሽልማት ስለ መቅረባቸው

ክርስቲያኖች በክርስቶስ የፍርድ ወንበር ሥር ፊት የሚዳኙት በምን ዓይነት የፍርድ ባህርይ ነው? በመጀመሪያ በግልጽና በእጽንኦት የምናስቀምጠው የክርስቲያኖች ፍርድ የኩነኔ ፍርድ አይደለም። ይህ ታላቅና አስፈላጊ እውነት ቢሆንም፥ በክርስቶስ ያለ እውነተኛ አማኝ ከኩነኔ ፍርሃት ነጻ እንደሆነ በብዙ የአዲስ ኪዳን ምንባቦች ተረጋግጧል።

«በእርሱ በሚያምን አይፈረድበትም፥ በማያምን ግን በአንዱ በእግዚአብሔር ልጅ ስም ስላላመነ አሁን ተፈርዶበታል» በማለት ኢየሱስ ተናግሯል። ዮሐንስ 3:18

ከዚህ ጥቅስ የምንረዳው በክርስቶስ ስም ያመነው እንደማይፈረድበትና ዳሩ ግን ያላመነው ሰዘላለም ቅጣት እንደሚዳረግ ነው። ክርስቶስም ይህንኑ ዋስትና በዮሐንስ 5:24 ላይ እንደገና እንዳረጋገጠልን እንመለከታለን።

«እውነት እውነት እላችኋለሁ፥ ቃሌን የሚሰማ የላከኝንም የሚያምን የዘላለም ሕይወት አለው። ከሞትም ወደ ሕይወት ተሻገረ እንጂ፥ ወደ ፍርድ አይመጣም።»

በዚህ ቦታ ላይ ክርስቶስ ቃሉን በወንጌል አማካኝነት በእምነት ሰሚቀበል አማኝ ሁሉ ሦስት ዋስትናዎችን ይሰጣል። ይህ ዓይነቱ አማኝ የዘላለም ሕይወት አለው፥ ከመንፈሳዊ ሞት ወደ ዘላለም ሕይወት ተሻግሯል። ወደ ፍርድም ፈፅሞ አይመጣም። ጳውሎስ የሚደግመው ይህንኑ ዋስትና ነው። *«እንግዲህ በክርስቶስ ኢየሱስ ላሉት አሁን ኩነኔ የለባቸውም»* ሮሜ 8:1።

እነዚህ ምንባቦች ግልጽ እንደሚያደርጉት እውነተኛ አማኞች ፍጻሜው የዘላለም ኩነኔ የሆነ ፍርድ አያጋጥማቸውም። በእርግጥ በክርስቶስ ያለ አውነተኛ አማኝ ስለሠራው ኃጢአት ይፈረድበት ዘንድ አያስፈልግም። ኃጢአተኛ ለው እንደ ኃጢአተኛ በእምነት ወደ ክርስቶስ ሲመጣና አዳኝ አድርጎ ሲቀበለው ጌታው አድርጎም ሲያውጀው ያለፈው ኃጢአቱ ወዲያውኑ እና ለዘላለም በእግዚአብሔር ይደመሰስለታል፤ ዳግመኛም ፈጽሞም አይታሰብም። በኢሳይያስ መጽሐፍ በሁለት ምዕራፎች በተከታታይ ለሁለት ጊዜ እግዚአብሔር ለተቤዣቸው ሕዝቦች ቃል ኪዳንን ይሰጣል። *«መተላለፍህን፦ ስለ እኔ ስል የምደመስስ እኔ ነኝ፤ ኃጢአትህን አላስብም።»* ኢሳይያስ 43:25 *«መተላለፍህን እንደ ደመና ኃጢአትህንም ደመሰሼአለሁ»* ኢሳይያስ 44:22።

በእነዚህ ምንባባት መተላለፍና ኃጢአት ተጠቅሰዋል። ኃጢአት ህጉን ባለማወቅ የሚፈጸም የስህተት ተግባር ነው። መተላለፍ ደግሞ የሚታወቀውን ህግ ግልጽ በሆነ አለመታዘዝ በመጣስ ስህተት መፈጸም ስለሆነም ኃጢአት ከደመና ጋር ሲነጻጸር መተላለፍ ደግሞ ከጭጋግ ጋር ተያይዟል። ከዚህ በመነሳት መተላለፍ ከኃጢአት ይልቅ የጠቆረ ነው ማለት ይቻላል። ሆኖም ግን የእግዚአብሔር ጸጋና ኃይል ሁለቱንም ለመደምሰስ ከበቂ በላይ ነው።

ባለፈው ምዕራፍ እያንዳንዱ ሰው በምድር ስለሚመራው ሕይወት የሚዘግብ መጽሐፍ በሰማይ እንዳለ ገልጸናል። ይህን ዓይነቱን መጽሐፍም ከኤሌክትሮኒክ መቀረጫ ቴፕ ጋር አስተያይተናል። ይህ እንጻራዊነት የሚዘልቀው ለመቅረፁ ወይም ለመመዝገቡ ብቻ ላይሆን ለመደምሰሱም ነው።

በቴፕ ላይ የተሠራ ስህተት ካለ የቴፕ መቅረጫውን በማሽከርከር በጥቂት ደቂቃ መደምሰስ ይቻላል። ሌላው ቀርቶ የተቀዳውን አጠቃላይ ቴፕ በጥቂት ሰከንዶች የሚደመስስ ማጥፊያ መሣሪያ አለ። በዚህ መሣሪያ አማካይነት ፍጹም ንጹህ የሆነና በፊት የነበረው መልዕክት የሌለበት አዲስ ቴፕ ማግኘት እንችላለን። በሰማይ ባለው የኃጢአተኛው ሕይወት መዝገብም እንደዚሁ ነው።

ኃጢአተኛው ሰመጀመሪያ ጊዜ በእምነትና በንስሐ ወደ ክርስቶስ ሲመጣ እግዚአብሔር ፍጹም ኃጢአቱን የሚደመስስለትን «መሣሪያ» በጥቅም ላይ ያውላል። በመዝገቡ ላይ የለፈረውን የኃጢአተኛውን ያለፉ ኃጢአቶች በቅጽበት ፈጽሞ ያጠፋውና አዲስ የእምነትና የጽድቅ ህይወት የሚመዘገብበት ንጹህ «ቴፕ» ያደርገዋል። ከዚህ በኋላ በማናቸውም ጊዜ ዳግመኛ በኃጢአት ቢወድቅ የሚያስፈልገው ነገር ንስሐ መግባትና ኃጢአቱን መናዘዝ ነው። እግዚአብሔር የቴፑን የተበላሸ ክፍል በመደምሰስ እንደገና ቴፑን ንፁህ ያደርገዋል።

ከዚህ ከክርስቶስ ቃል ኪዳን የምንገነዘበው ማናቸውም አማኝ ሦስት የተረጋገጡ ተስፋዎች እንዳሉት ነው። ይኸውም በቅድሚያ የዘላለም ሕይወት እንዳለው፥ ከምድራዊ ሞትም ወደ መንፈላዊ ሕይወት እንደተሸጋገረና፥ ዳግመኛም ለፍርድ እንደማይቀርብ ነው።

ይሁን እንጂ አንድ ክርስቲያን ላይታወቀው ኃጢአት ፈጽሞ ቢገኝ አንኳ ኃጢአቱ በሚከተለው መልኩ እንደሚሰረይለት በ1ኛ ዮሐንስ 1:9 እና 2:1-2 ላይ እንደሚከተለው ተረጋግጧል፦ *«ቢኃጢአታችን ብንናዘዝ ኃጢአታችንን ይቅር ሊለን ከአመፃም ሁሉ ሊያነጻን የታመነና ጻድቅ ነው» «ልጆቼ ሆይ፥ ኃጢአትን እንዳታደርጉ ይህን እፅፍላችኋለሁ። ማንም ኃጢአትን ቢያደርግ ከአብ ዘንድ ጠበቃ አለን፥ እርሱም ጻድቅ የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። እርሱም የኃጢአታችን ማስተሠሪያ፥ ለኃጢአታችንም ብቻ አይደለም፥ ነገር ግን ለዓለሙ ሁሉ ኃጢአት እንጂ።»*

እነዚህ ምንባቦች በክርስቶስ የሚያምን ሰው ኃጢአትን ቢያደርግ በኋላም ንስሐ ቢገባና ኃጢአቱን ቢናዘዝ የሠራው ኃጢአት ሁሉ ተደምስሶለት ከማናቸውም ነገር የነጻ እንደሚሆን ያስተምራል። እውነተኛ አማኝ የመጨረሻዋን ፍርድ (ኩነኔ) መፍራት የሌለበትም ለዚህ ነው። ኃጢአተኛው የሚነጻበትንና ወደ ፍርድ የሚያቀርበው እንዳች ኃጢአት እስከማይቀር ድረስ በኃጢአት መዝገብ ያለው ኃጢአቱ የሚደመሰስበትን ሁኔታ እግዚአብሔር አዘጋጅቷል።

እውነተኛ አማኝ የመጨረሻው ፍርድ በማናቸውም ሁኔታ የማያገኝ ከሆነ ክርስቲያን በፍርድ ወንበር ፊት የሚቀርበው ሰምን ዓላማ ነው ቢባል መልሱ ሽልማቱን እንዲቀበል ነው። እውነተኛ አማኝ በክርስቶስ የፍርድ ወንበር ፊት የሚቆመው ከጽድቅ አኳያ ላይሆን ለክርስቶስ ካበረከተው አገልግሎት አኳያ ነው። አማኝ ከጽድቅ አንጻር በፍርድ ወንበር ፊት

የማይቆምበት ምክንያት ግልጥ ነው። ይኸውም የአማኙ ጽድቅ የራሱ የአማኙ ሳይሆን በእምነቱ ምክንያት እግዚአብሔር በአማኙ ላይ ያስቀመጠው የክርስቶስ ጽድቅ ነው።

በዚህ እስደናቂ ልውውጥ እኛ በክርስቶስ የእግዚአብሔር ጽድቅ ሆነናል። ስለሆነም አማኝ በዚህ ጽድቅ መሠረት ደህንነትን ሲቀበል አማኙን በፍርድ ወንበር ፊት ማቆም ወይም ከራሱ ከእግዚአብሔር የተገኘውን ጽድቅ ክጥያቂ ውስጥ ማስገባት ለእግዚአብሔር ምክንያታዊ አይደለም። «. . . *ከእግዚአብሔር ዘንድ ጥበብና ጽድቅ ቅድስናም ቤዛነትም በተደረገልን በክርስቶስ ኢየሱስ . . .* » «*እኛ በእርሱ ሆነን የእግዚአብሔር ጽድቅ እንሆን ዘንድ ኃጢአት ያላወቀውን እርሱን ስለ እኛ ኃጢአት አደረገው።*» 1ኛ ቆሮንቶስ 1:30፤ 5:21

ለማጠቃለል ክርስቲያኖች በፍርድ ወንበር ፊት የሚቀርቡት ስለ ጽድቃቸው ሳይሆን ለክርስቶስ ስላቀረቡት አገልግሎት ነው። የፍርዱም ዓላማ አማኙን ለማጽደቅ ወይም ለመኮነን ሳይሆን አማኙ በምድር ላለ ለክርስቶስ ላበረከተው አገልግሎት የሽልማቱን ዋጋ እንዲቀበል ነው።

በእሳት መፈተን

አማኞች ለሽልማት ስለሚቀርቡበት የፍርድ ዓይነት በማስመልከት ጳውሎስ በ1ኛ ቆሮንቶስ 3:11-15 ላይ እንዲህ ይላል፦ «*ከተመሠረተው በቀር ማንም ሌላ መሠረት ሊመሠርት አይችልምና፤ እርሱም ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ማንም ግን በዚህ መሠረት ላይ በወርቅ ቢሆን በብርም በከበረ ድንጋይም በእንጨትም በሣርም ወይም በአገዳ ቢያንጽ፤ የአያንዳንዱ ሥራ ይገለጣል። በእሳት ስለሚገለጥ ያ ቀን ያሳያልና፤ የአያንዳንዱም ሥራ እንዴት መሆኑን እሳቱ ይፈትነዋልና። ማንም በእርሱ ላይ ያነጸው ሥራ ቢጸናለት ደመወዙን ይቀበላል፤ የማንም ሥራ የተቃጠለበት ቢሆን ይጎዳበታል፤ እርሱ ራሱ ግን ይድናል፤ ነገር ግን በእሳት እንደሚድን ይሆናል።*»

በዚህ መልዕክት ውስጥ አንድ ግልጽ የተደረገልን ነገር ቢኖር በእሳት የሚፈተነው የአያንዳንዱ ሰው ነፍስ ሳይሆን ሥራው ስለመሆኑ ነው።

የሰውየው ሥራ በአጠቃላይ ቢቃጠልም እንኳ ነፍሱ ግን ይድናል። የአማኙ ነፍስ ሰምን እንደሚድን ጳውሎስ በዚህ ምንባብ የመጀመሪያ ቁጥር ላይ ያብራራል። «*ከተመሠረተው በቀር ማንም ሌላ መሠረት ሊመሠርት አይችልምና፤ እርሱም ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።*» (ቁጥር 11)

ይህ ፍርድ የሚመሰክተው እምነታቸውን በሥራቸው ወይም በጽድቃቸው ላይ ሳይሆን ነገር ግን በክርስቶስ መሠረትነትና በእርሱ ጽድቅ ላይ ያደረጉትን ብቻ ነው። እምነታቸው በዚህ መሠረት ላይ የማይናወጥ እስከሆነ ድረስ ነፍሳቸው ሰዘላለም ከማናቸውም ኩነኔ የተጠበቀ ነው። የእማኞች ሥራ

ወደሚገመገምበት ሁኔታ ስንመጣ ጳውሎስ በሁለት ምድብ ክፍሏቸው እናገኛለን። በእንድ በኩል «ወርቅ፤ ብር፤ የከበሩ ድንጋዮች» ሲናሩ በሌላ በኩል ደግሞ «እንጨት፤ አገዳና ሣር» እሱ።

እነዚህ ሁለት ምድቦች የተለያዩበት ምክንያት በእሳት ሊፈተኑ ጸንተው የሚቆሙበት ችሎታቸው ነው። በመጀመሪያው ምድብ ውስጥ ያሉት ነገሮች ማለትም ወርቅ፤ ብር፤ የከበሩ ድንጋዮች ምንም ዓይነት ጉዳት ሳይደርስባቸው በእሳት ውስጥ ማለፍ ይችላሉ። በሁለተኛው ምድብ ውስጥ ያሉት እንጨት፤ አገዳና ሣር ግን በእሳቱ ይበላሉ።

እነዚህን ሁለት ምድቦች በማነጻጸር አንድ ሰው ክብዛት ይልቅ ጥራት ለእግዚአብሔር ይበልጥ ያስፈልገዋል ብሎ ሊያስብ ይችላል። በተለምዶ እንደምናውቀው ወርቅ፤ ብርና የከበሩ ድንጋዮች በእነስተኛ ብዛት የሚገኙ ሲሆን ነገር ግን ክፍ ያለ ዋጋ አላቸው። እንጨት አገዳና ሣር ብዙ ቦታዎችን የሚሸፍኑና በብዛትም ሊገኙ የሚችሉ ሲሆን በእንጻሩ ግን እነስተኛ ዋጋ ያላቸው ናቸው።

በመቀጠል ደግሞ የሚነሳው ጥያቄ ለመሆኑ የዚህ የመፈተኛው እሳት ባህርይ ምን ዓይነት ነው? ጠቀሜታውስ? የሚለው ይሆናል።

እማኞች የሚፈተኑት ቃል በቃል እንደተገለጸው በነዳጅ እሳት ሳይሆን በእባቱ ዙፋን ከተቀመጠው ከክርስቶስ በሚንጸባረቀው ብርሃን ነው። ይህንንም የሚያረጋግጥልን በፍጥሞስ ደሴት ላይ በግዞት የነበረው ዮሐንስ ያየው ራዕይ ነው። በዚያም ራዕይ 1:14-15 ላይ ስለ ክርስቶስስ ግርማና ሞገሥ የሚከተለውን ገልጾአል፦ «*ራስና የራሱ ጠጕርም እንደ ነጭ የበግ ጠጕር እንደ በረዶም ነጭ ነበሩ፤ ዓይኖቹም እንደ እሳት ነባልባል ነበሩ፤ እግሮቹም በእቶን የነጠረ የጋለ ናስ ይመስሉ ነበር፤ ድምፁም እንደ ብዙ ውኃዎች ድምፅ ነበረ።*»

በዚህ ራዕይ ውስጥ የክርስቶስ እግር «የነጠረ ናስ ይመስል» እንደ ነበርና በምድጃ ውስጥ ይኸውም ኃጢአተኞችንና ክፉ ተግባራት ያከናወኑትን ሰዎች በሚቀጣበት የመከራ እሳት ውስጥ ቆሞ እንደ ነበር ሊገለጽ ዓይኑም እንደ «እሳት ነበልባል» ይኸውም በእይታ የገዛ ወገኖቹን (እማኞችን) ሥራቸውን የሚመረምርበትና የሚፈትንበት ሆኖ ታይቷል።

እንግዲህ በዚህ መልኩ የተገለጸው ከክርስቶስ የሚወረወረው ብርሃን ነው እያንዳንዳችንን እንደ እሳት በመቦርቦር የሠራነውን ሥራ ሁሉ የሚመረምረው። ክዚህ መሰሉም ፈተና ለማምለጥ ነው ክርስቶስን ክልብ ልናገለግለው መነሣሣት ያስብን። ይህን የፍርድ ሂደት ስናስተውል እያንዳንዳችን ራሳችንን መጠየቅ የሚገባን ነገር አለ። ይኸውም በዚያ ቀን በዚያ የፈተና እሳት ውስጥ ሥራዬ እንዲያልፍ በሕይወቴ ክርስቶስን እንዴት ላገልግለው? ማለት አለብን።

ራሳችንን ስለ መመርመር ሦስት ነጥቦች አሉ። እነርሱም፡- ዓላማ (የልብ ዝንባሌ)፥ መታዘዝ እና ኃይል ናቸው።

በቅድሚያ፡- ስምን ዓላማ ነው? የሚለውን ጥያቄ ልናብላላው ይገባል። ዓላማችን ለራሳችን ክብርና ዝናን ለማትረፍ ወይም ለየት ያለ ጠቀሜታ ለማግኘት ነው? ወይንም የክርስቶስን ፈቃድና ትዕዛዝ ለመፈጸም ነው? ስንል እራሳችንን ልንጠይቀውና መልሱን ልንሰጥ ይገባል።

ሁለተኛ፡- መታዘዝን በተመለከተ ደግሞ ራሳችንን የምንመረምርበት ነጥብ አለ። በእግዚአብሔር ቃል ይተገለጡት ዘዴዎችና መመሪያዎች ክርስቶስን ለማገልገል እንፈልጋለን? ወይስ ከክርስቶስ ስም ጋር በማቆራኘት የአዲስ ኪዳን ቃላትን በመጠቀም የራሳችንን የአምልኮ እካሄድና አገልግሎት ለማቆም እንወዳለን?

በሦስተኛ ደረጃ ደግሞ፡- ኃይልን በተመለከተ ራሳችንን ልንመረምር ይገባናል። ጳውሎስ እንደሚያሳስበን *«የእግዚአብሔር መንግሥት በኃይል ነው እንጂ በቃል አይደለም»* (1ቆሮ. 4:20)። እግዚአብሔርን ማገልገል የምንፈልገው ደካማ በሆነው ሥጋዊ ጉልበታችን ነው? ወይስ በመንፈስ ቅዱስ እየታደስንና እየተሞላን?

እንግዲህ አገልግሎታችንን በመንፈስ ቅዱስ ኃይል እስካከናወንን ልክ ሐዋርያው ጳውሎስ በቆላስያስ መልዕክቱ 1:29 ላይ፥ እንደተናገረው *«ለዚህም ነገር ደግሞ፥ በእኔ በኃይል እንደሚሠራ እንደ አሠራሩ እየተጋደልሁ እደክማለሁ»* ብለን ለመናገር እንችላለን።

በዚያ ቀን በክርስቶስ ወንበር ፊት ስንቆም የሚኖረን ነገር ለእነዚህ ሦስት ጥያቄዎች ማለትም ስለ ልብ ዝንባሌያችን ስለ መታዘዛችንና ስለምናገለግልበት ኃይል በምንለጠው መልስ የተመረኮዘ ይሆናል።

51

የክርስቲያን አገልግሎቱና ሽልማቱ

ከላይ በተጠቀሱት ሁለት ምሳሌዎች አማካይነት ክርስቶስ ያስተላለፈው መልእክት ተመሳሳይ ሲሆን ነው። ሁለቱም ምሳሌዎች የሚያመለክቱት እንድ ከበርቴ ለአገልጋዮቹ የተወሰነ ገንዘብ በአደራ በመስጠት ራቅ ወዳለ ሥፍራ መሄዱን ነው። ታዲያ በሁለቱም ምሳሌዎች ውስጥ የተጠቀሰው የአገልጋዮቹ ብዛት ሦስት ሦስት ሲሆን፥ ከእነዚህም ሁለቱ ታማኞች፥ ሦስተኛው ግን ለእምነት የማይበቃ ሆኖ እናገኘዋለን። ይህንንም ለማብራራት ያስችለን ዘንድ በቅድሚያ በማቴዎስ 25 ላይ ከቀረበው የመክሊት ምሳሌ ቁጥር 15ን ብቻ እንጠቅሳለን። *«ለአያንዳንዱ እንደ አቅሙ፥ ለአንዱ አምስት መክሊት ለአንዱ ሁለት ለአንዱም አንድ ሰጠና ወደ ሌላ አገር ወዲያው ሄደ።»*

(በዚህ ቦታ መክሊት ተብሎ የተጠቀሰው የተወሰነ የገንዘብ መጠን ሲሆን ምናልባትም አንድ መክሊት የአስራ አምስት ዓመት ደመወዝ ያህል ይሆናል)።

ከዚህ ጥቅስ ውስጥ በቅድሚያ ልብ ልንለው የሚገባው ነጥብ የመክሊቶቹ እከፋፈል በዘፈቀደ ሳይሆን ለአያንዳንዱ እንደ አቅሙ መሆኑን ነው። ይህም የሚያመለክተን እግዚአብሔር ለማንኛችንም ቢሆን በተመሳሳይ መልኩ እንደ አቅምና እንደ ችሎታችን ኃላፊነትን የሚጥልብን መሆኑን ነው።

እግዚአብሔር ለየትኛውም አማኝ ከአቅሙ በታች ወይንም ከአቅሙ በላይ አይሰጠውም። በዚህ ምሳሌ ውስጥ የመጀመሪያዎቹ ሁለት አገልጋዮች እያንዳንዳቸው መቶ እጅ ትርፍ አግኝተዋል። አምስት መክሊት የተቀበለው አምስት መክሊት ሲያተርፍ ሁለት የተቀበለው ሁለት አትርፏል። ጌታ የእነዚህን አገልጋዮች ታማኝነት የመዘነው በአገኙት የተጣራ ትርፍ ሳይሆን በመቶኛ (በፐርሰንት) ነው። አምስት መክሊት ያተረፈው ሰው ምንም እንኳ ከፍ ያለ የተጣራ ትርፍ ቢያገኝም ሁለት መክሊት ካተረፈው ይልቅ ታማኝ አይደለም። ይልቁንም እነዚህ አገልጋዮች ሁለቱም በእኩል ታማኞች ናቸው። ምክንያቱም ሁለቱም ያተረፉት ከተቀበሉት መቶ እጅ ነው። ይህም እውነታ በማቴዎስ 25:21 እና 23 ላይ የተዘገቡትና ሰሁለቱም አገልጋዮች የተነገሩት የምሥጋና ቃላቶች ተመሳሳይ መሆናቸው ተገልጧል። *«. . . መልካም፥ አንተ በጎ ታማኝ ባሪያ፥ በጥቂቱ ታምነሃል፥ በብዙ እሾምሃለሁ።»* ማቴዎስ 25:21 እና 23

እያንዳንዳቸው አቅማቸው የሚፈቅድላቸውንና በሚገባ የሚጠቀሙበትን መክሊት ተቀብለዋል። እያንዳንዳቸውም ሊያተርፉ የሚችሉበትን ያህል ማለትም መቶ እጅ አትርፈዋል። እንደ ተገለጠው ፍርዳቸው የተመለረተው በታማኝነታቸውና በትርፋቸው የመቶኛ ስሌት ነው እንጂ ከመጀመሪያው አምስትና ሁለት መክሊት በመቀበላቸው አይደለም።

አንድ መክሊት የተቀበለው ሦስተኛ አገልጋይ ግን የተቀበለውን መክሊት ደብቆ ከቆየ በኋላ ጌታው ሲመለስ ያንኑ መክሊት በተቀበለበት ሁኔታ ለጌታው ሊለጥ እናያለን። በዚህም ምክንያት ያ አገልጋይ ከሽልማት መገለል ብቻ ሳይሆን ከጌታው ፊት እንዲወጣና እንዲጣል ተደርጓል። *«ጌታውም መልሶ እንዲህ አለው አንተክፉና ሃኬተኛ ባሪያ፥ ካልዘራሁበት አንዳጭድ ካልበተንሁበትም እንድሰበስብ ታውቃለህን? ስለዚህ ገንዘቤን ለለዋጮች አደራ ልትሰጠው በተገባህ ነበር። እኔም መጥቼ ያለኝን ከትርፉ ጋር እወስደው ነበር። ስለዚህ መክሊቱን ውሰዱበት፥ አሥር መክሊትም ላለው ስጡት፥ ላለው ሁሉ ይሰጠዋልና ይበዛለታልም ስሌለው ግን ያው ያለው እንኳ ይወሰድበታል። የማይጠቅመውን ባሪያ በውጭ ወዳለው ጨለማ አውጡት በዚያ ልቅሶና ጥርስ ማፋጨት ይሆናል።»* ማቴዎስ 25:26-30

የእነዚህ ቃላት ትርጉም ምን እንደሆነ ለማንም ግልጥ ነው። ይህ አገልጋይ ከማናቸውም ሽልማት ከመገለሉ ሌላ ከመጀመሪያውም የተቀበለውን አንድ መክሊት ተነጥቋል። ራሱም ከጌታው ፊት እንዲወጣ ተደርጓል።

በሉቃስ 19 ላይ በተጠቀለው ሌላ ምሳሌም እንደምን አንድ መኮንን ወደ ሩቅ አገር እንደሄደና ለሦስቱ ባሪያዎቹ አሥር ምናን እንዳከፋፈላቸው ተጥቅሶ እናገኛለን። (ምናን የሦስት ወር ደመወዝ ያህል የሚያክል ገንዘብ ነው።) በዚህ ምሳሌ ውስጥ አሥር አገልጋዮች የተጠቀሱ ሲሆን በጥልቀት የተገለጠው ግን የሦስቱ ብቻ ነው። በመጀመሪያ አሥሩም የተቀበሉት ጌታቸው ለእነርሱ እንዳደላቸው አንዳንድ ምናን ነው። ሁኔታቸው በጥልቀት ሸተገለፀው ሦስት

አገልጋዮች መካከል የመጀመሪያው አሥር ምናን ሲያተርፍ ሁለተኛው አምስት ምናን አትርፏል። ሦስተኛው ግን ምናኑን ደብቆ በኋላ ያንኑ ምናን ለጌታው አቅርቧል። ክምሳሌው እንደሚታየው ሦስቱም የተቀበሉት ምናን እኩል እንደመሆኑ መጠን ችሎታቸውም እኩል ነው። ሆኖም ታማኝነታቸው እኩል አይደለም። የመጀመሪያውን ያተረፈው የሁለተኛውን እጥፍ ነበር። በዚህ ምክንያት የተቀበለው ሽልማት ሁለት እጥፍ የሚበልጥ ነበር። *«የፊተኛውም ደርሶ፦ ጌታ ሆይ፥ ምናንህ አሥር ምናን አተረፈ አለው። እርሱም መልካም አንተ በጎ ባሪያ በጥቂት የታመንህ ስለሆንህ በአሥር ከተሞች ላይ ሥልጣን ይሁንልህ አለው። ሁለተኛውም መጥቶ፦ ጌታ ሆይ፥ ምናንህ አምስት ምናን አተረፈ አለው። ይህንም ደግሞ አንተም በአምስት ከተሞች ላይ ሁን አለው።»* ሉቃስ 19:16-19

የመጀመሪያው አገልጋይ ሽልማት ከሁለተኛው የበለጠበትን ምክንያት በሁለት መንገድ እናያለን። በመጀመሪያ፥ ይህ አገልጋይ በጌታ ዘንድ መልካም አገልጋይ ተብሎ ተጠርቷል። ሁለተኛው አገልጋይ ግን እንዲህ ዓይነት አጠራር አልተሰጠውም። ሁለተኛ፥ የመጀመሪያው አገልጋይ በአሥር ከተሞች ላይ ሥልጣን ሲሰጠው ሁለተኛው አገልጋይ የተሾመው ግን በአምስት ከተሞች ላይ ነው። ስለሆነም ሽልማቶቻቸው ባገኙት ትርፍ አንጻር ነበር ማለት ይቻላል።

ከዚህ ምሳሌ የምንረዳው ባሁኑ ዘመን ክርስቶስን በታማኝነት የማገልገላችን ሽልማት በሚመጣው ዘመን በሚኖረው የክርስቶስ መንግሥት ውስጥ የሚኖረንን ኃላፊነትና ሥልጣን ያመላክታል። በሌላ ቋንቋ በዚህ ዘመን የሆነ ታማኝ አገልግሎት በሚመጣው ዘመን ለሚኖሩ የአገልግሎት እድሎች ይመራል። በእውነት ክርስቶስን ለሚያፈቅሩ ክርስቶስን በቀጣይነት ከማገልገል የሚበልጥ እድልና ደስታ የላቸውም ታማኞች ለሆኑት ይህ እድል የሚጀምረው አሁን ሲሆን ለዘላለምም ይቀጥላል።

እንደ መክሊቱ ምሳሌ በዚህም በምናን ምሳሌ ውስጥ ሦስተኛው አገልጋይ ታማኝ ባለመሆኑና የተሰጠውን ምናን ጥቅም ላይ ባለማዋሉ ይፈረድበታል።

«እርሱም፥ አንተ ክፉ ባሪያ ሳፍህ በተናገረው እፈርድብሃለሁ፥ እኔ ያላኖርሁትን የምወስድና ያልዘራሁትን የማጭድ ጨካኝ ሰው እንደሆንኩ አወቅህ ምነው ገንዘቤን ለለዋጮች አደራ ያልሰጠኸው? እኔም መጥቼ ከትርፉ ጋር እወስደው ነበር አለው። በዚያም ቆመው የነበሩትን ምናኑን ውሰዱበት፥ አሥሩ ምናን ላለውም ስጡት አላቸው።» ሉቃስ 19:22-24

እንደ መክሊቱ ምሳሌ በዚህም ምሳሌ ውስጥ ታማኝ ያልሆነው አገልጋይ ሽልማት የሌለው ብቻ ሳይሆን መጀመሪያ የተሰጠውን አንድ ምናን እንኳ ከእርሱ ተወስዶበታል። የዚህ ባለ አንድ ምናን አገልጋይ መጨረሻ በዚህ ምሳሌ አልተገለጠም። ሆኖም ግን በመክሊቱ ምሳሌ ላይ እንዳለው ታማኝ

አገልጋይ ይህም ከጌታ ፊት ወደ ውጪ እንደሚጣል መደምደሙ ትክክል ይመስላል። በሁለቱም ምሳሌዎች ውስጥ የተሰጠውን መክሊት ወይም ምናን በጥቅም ላይ ያላዋለው አገልጋይ ክፉ በሚል ጠንካራ ቃል ተለንዝሮበታል። ጌታም በዚህ ታማኝ ያልሆነ አገልጋይ ላይ ትርጉም ሊያስተላልፍ የተጠቀመበት ሐረግ «አንተ ክፉ ባርያ» የሚል ነው።

ከዚህ የምንማረው በእግዚአብሔር መመዘኛ አንጻር ክፋት የሚመለረተው ክፉ ተግባርን በመፈጸም ብቻ ሳይሆን መልካም የማድረግ ኃይል እያለን ባለማድረግም ጭምር ነው። *«አንግዲህ በጎ ለማድረግ ለውቆ ለማይሠራው ኃጢአት ነው።»* ያዕቆብ 4:17

በሌላ አነጋጋር የመተው ኃጢአት ከድርጊት ኃጢአት ባነሰ ሁኔታ አይታይም።

ተመሳሳይ የሆነ ሃሳብ ሚልክያስ የእግዚአብሔር ፍርድ መገለጥን ትንቢት በተናገረበት ውስጥ እናገኛለን። *«ተመልሳችሁም በጻድቁና በኃጢአተኛው መካከል፤ ለእግዚአብሔር በሚገዛውና በማይገዛው መካከል ትለያላችሁ።»* ሚልክያስ 3:18

በዚህ ቦታ ላይ በጻድቁና በኃጢአተኛው መካከል፤ እግዚአብሔር ያስቀመጠውን ልዩነት በግልጥ እናገኛለን። ጻድቅ በዚህ ቦታ ላይ የተገለጠው እግዚአብሔርን እንደሚያገለግል ሰው ሲሆን ኃጢአተኛው ደግሞ እግዚአብሔርን እንደማያገለግል በመሆን ነው። ትምህርቱ ግልጽ ነው፤ እግዚአብሔርን አለመማገልገል በራሱ ኃጢአት ነው።

ባጠናናቸው በሁለቱ ምሳሌዎች ውስጥ ታማኝ ያልሆነውን አገልጋይ ወደ ፍርድና ወደ ውጭ መጣል የመራው ይህ ኃጢአት ነው። በሁለቱ ምሳሌዎች ውስጥ ይህ የተጣለው አገልጋይ ምንም ዓይነት ክፋት አልሠራም። ወደ ውጭ የመጣሉ ምክንያት ማድረግ እየቻለ መልካም አለማድረጉ ነው። በሁለቱ ምሳሌዎች ክርስቶስ ያመለከተን ያው የፍርድ መመሪያ በክርስቶስ አገልጋዮችና ተከታዮች ላይ እንደሚሆን ነው።

ባለፈው ምዕራፍ በፍርድ እሣት ውስጥ የክርስቲያን ሥራዎች እንደሚቃጠሉና ክርስቲያኑ ግን እንደሚድን የሚናገር ምንባብን እይተናል (1ኛ ቆሮንቶስ 3:11-15)። በሌላ በኩል ደግሞ አሁን በተመለከትናቸው ምሳሌዎች ውስጥ ታማኝ ያልሆነው አገልጋይ ከሽልማት ገለል የሚደረግ ብቻ ሳይሆን ከጌታው ፊትም ወደ ውጪ እንደሚጣል ተገልጧል።

ይህም እጅግ አስፈላጊ የሆነውን ጥያቄ እንድንጠይቅ ይመራናል። ይህም ጥያቄ በነዚህ ሁለት ሁኔታዎች ላይ ያለው የእግዚአብሔር አይታ ልዩነት ምንድን ነው? ጳውሎስ በገለጠው ሁኔታ ላይ የለውየው ሥራ እንደሚቃጠል ነገር ግን ለውየው ራሱ እንደሚድን፤ ኢየሱስ በተናገረው

የአገልጋይ ምሳሌ ላይ ግን ታማኝ ያልሆነው አገልጋይ ሽልማቱን የሚያጣ ብቻ ሳይሆን እርሱ ራሱም ወደ ውጭ የሚጣል ለምን ይሆን? ልዩነቱ ይህ ነው። ጳውሎስ በገለጠው ሁኔታ ላይ ለውየው እንድ ነገር ለጌታው ሊያደርግ ይሞክራል። የአንጨቱ፤ የሣሩና የአገዳው ምሳሌ እንደሚያሳየን በእርግጥም ለውየው የተቻለውን ያህል አድርጓል። ሆኖም ግን ሥራው በእሣት ውስጥ የሚያልፍበትን ዓይነት ብቃት (ጥራት) አላገኘም። የሆነ ሆኖ ይህ የተሳሳተና ሽልማት አልባ ጥረቱ በተወሰነ መጠን ለክርስቶስ ያለው እምነት እውነተኛ እንደሆነ ያረጋግጣል። በዚህም ምክንያት ምንም እንኳ ሥራው ቢቃጠልም የነፍሱ ደህንነት ግን ዋስትና ያለው ነው። በሌላ በኩል ታማኝ ያልሆነው ባለ አንድ መክሊት አገልጋይ ለጌታው ምንም ነገር አላደረገም። ይህ ድርጊቱ የሚያመለክተው አምነቱና አገልግሎቱ ከንቱና ከልብ እንዳልሆነ ነው።

«ከሥራ የተለየ እምነት የሞተ ነው።» ያዕቆብ 2:26

በማናቸውም ተግባር የማይገለጥ እምነት ባዶ ጥቅም የሌለውና ከልብ ያልሆነ የሞተ እምነት ነው። ሽልማት የሚያስገኝ ሥራና አገልግሎት መፈፀም የማይችል ብቻ ሳይሆን የራሱን ነፍስ ደህንነት ዋስትና እንኳን የማያስጠብቅ ነው። በክርስቶስ እንደሚያምን የሚናገር ነገር ግን ክርስቶስን ለማገልገል የማይፈልግ ሰው ግብዝ ነው።

በዚህ ምክንያት በዚህ ዓይነት ሰው ላይ የሚመጣው ፍርድ «ልቅሶና ጥርስ ማፋጨት (ወዳለበት) በውጭ ወዳለው ጨለማ» መጣል ነው።

ተመሳሳይ የሆኑ ፍርዶችን የሚያመለክቱትን ምንባቦች በጥንቃቄ ስንመረምር (ማቴዎስ 24:51ን ሉቃስ 12:46) ስንመረምር ይህ ልቅሶና ጥርስ ማፋጨት ያለበት በውጭ ያለ የጨለማ ሥፍራ ለአስመሳዮችና ለማያምኑ ሰዎች የተጠበቀ እንደሆነ እናያለን። ለጌታው ምንም ያላደረገው ታማኝ ያልሆነው አገልጋይ በዚህ ቦታ ሥፍራውን ማግኘት አለበት። እንደ እውነታው ይህ አገልጋይ አስመሳይ የማያምን ነው። ለእርሱ የተዘጋጀለት ሥፍራ በውጭ ያለው ነው።

አስመሳዮች በመላዕክት እጅ እንደሚወገዱ

ይህ በአስመሳይ አገልጋይ ላይ የተሰጠው ፍርድ ስለ ክርስቶስ የፍርድ ወንበር ሁኔታ በሚመለከት እጅግ ጠቃሚ ወደ ሆነ ድምዳሜ ይመራናል። እውነተኞች ክርስቲያኖች በክርስቶስ የፍርድ ወንበር ከመቆማቸው በፊት በመጀመሪያ ስለ አስመሳይነታቸውና ስለ ሐሰታቸው ፍርድ ይቀበሉ ዘንድ አስመሳዮችና ሐሰተኞች ክርስቲያኖች ከእውነተኞቹ የእግዚአብሔር ሕዝቦች ይለያሉ።

ይህ በአለመሳዮች ወይም በግብዞች ላይ የሚሆነው ፍርድ *መንግሥተ ለማይን* በሚመለከት በተጠቀሱት ሁለት ምሳሌዎች ላይ ተገልጸአል (ማቴዎስ 13ን ተመልከት)። እነዚህ ሁለት ምሳሌዎች ላይ የስንዴና የእንክርዳድ ምሳሌና ወደ ባህር የተጣለ መረብ ምሳሌ ናቸው።

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ እነዚህንና ሌሎችንም ምሳሌዎች ስናጠና «መንግሥተ ለማይ» የሚለው ሐረግ ምን ማለት እንደሆነ መለየት እጅግ አስፈላጊ ነው። በማቴዎስ 12:25-28 እና ሉቃስ 11:17-20 ኢየሱስ በተቃርና ውስጥ ስላሉ ሁለት *መንግሥታት* ማቴዎስም ስለ እግዚአብሔር መንግሥት ወይም ስለ ለማይ መንግሥት እና ስለ ሰይጣን መንግሥት ይናገራል። ይህ ዘመን እስከሚያበቃ ድረስ የእነዚህ ሁለት *መንግሥታት* አብሮ መኖር ይቀጥላል የእግዚአብሔር መንግሥት ለእግዚአብሔር የፅድቅ አገዛዝ ራሳቸውን ያስገዙትን ፍጡራን ሁሉ ያጠቃልላል። የሰይጣን *መንግሥት* ደግሞ በእግዚአብሔር *መንግሥት* ላይ ያመጹትን ሁሉ ያጠቃልላል። በኤፌሶን መልዕክት ላይ ጳውሎስ ሁለት የለይጣን *መንግሥታን* ደረጃዎች ይገልጣል። በመጀመሪያ የገለጠው ለይጣን በእግዚአብሔር ላይ ሲያምፅ የተከተሉትን የክፋት መላዕክት ነው (ኤፌሶን 6:12)። በሁለተኛ ደረጃ የሚናገረው በእግዚአብሔር ላይ ስላመፁ የሰው ልጆች ነው። እነዚህን «የማይታዘዙ ልጆች» ብሎ ሲጠራቸው «በአየር ላይ ሥልጣን ላለው አለቃ» ቁጥጥር ሥር መሆናቸውንም ያመለክታል (ኤፌሶን 2:2)።

በኢየሱስና በሐዋርያቱ የተሰበከው «የመንግሥት ወንጌል» ከለይጣን *መንግሥት* እንዲያመልጡና ወደ እግዚአብሔር *መንግሥት* እንዲገቡ ለአመጸኞች ለዎች የተዘረጋ ግብዣ ነው። ይህ ሲባል ግን ግብዣው በፍጹም ለአመጸኞቹ መላዕክት አልቀረበም። ይህን ግብዣ ለመቀበል የሚፈልጉ ሁሉ ሁለት ሁኔታዎችን ማሟላት አለባቸው። ስለ አመጻቸው ንስሐ መግባት አለባቸው፥ እግዚአብሔር ገዢ አድርጎ ለሾመው ለክርስቶስ ራሳቸውን ማስገዛት አለባቸው።

እነዚህ የስንዴና የእንክርዳድ እንዲሁም ወደ ባህር የተጣለው መረብ ምሳሌዎች እንደሚገልጡት የእግዚአብሔር *መንግሥት* ወገን ሆነው የታዩ አንዳንድ ለዎች እነዚህን ሁለት ዋና ዋና ነገሮች ማለትም እምነትና ንስሐ አንዳላሟሉ ነው። ውጫዊ የሆነ የንስሐ የመገዛት ነገርን ፈፅመው ይሆናል። ነገር ግን ይህ ክልብ የሆነ አይደለም። በመቀጠልም ይህ አፋዊ ድርጊት ጥልቅና ለእግዚአብሔር *መንግሥት* ብቻ ተገቢ የሆነ የባህሪ ለውጥን አላፈራም። የእነዚህ ሁለት ምሳሌዎች ዋና ዓላማ እግዚአብሔር በዘመኑ ፍጻሜ በአለመሳዮችና በግብዞች ላይ የሚያመጣውን ልዩ ፍርድ ለመግለጥ ነው።

ከሁለቱ ምሳሌዎች በመጀመሪያው አገልጋዮቹ እንክርዳዱን እንዲነቅሉ የእርሻውን ባለቤት ሲጠይቁ እናያለን። *«እነርሱ ግን እንክርዳዱን ሰትሰቅሙ ሰንዴውን ከእርሱ ጋር እንዳትነቅሉት አይሆንም. . . . አለ።»* ማቴዎስ 13:29

ይህ እንደሚያመለክተው ስንዴን ከእንክርዳድ መለየቱ ለአገልጋዮቹ እጅግ ከባድ እንደሚሆን ነው። በግልጽ እንደሚታወቀው እንክርዳዱ በክርስቶስ የማያምኑ ለዎችን ቢወክል ኖሮ ምንም ችግር አይኖረውም ነበር። ኢየሱስ ስለ ምሳሌው ሙሉ ትርጓሜ ሲሰጥ፦ *«እርሱም መልሶ እንዲህ አላቸው መልካሙን ዘር የዘራው የሰው ልጅ ነው፥ እርሻውም ዓለም ነው። መልካሙ ዘር የመንግሥት ልጆች ናቸው፤ እንክርዳድም የክፉው ልጆች ናቸው፥ የዘራውም ጠላት ዲያብሎስ ነው። መከሩም የዓለም መጨረሻ ነው፤ አጫጆችም መላእክት ናቸው። እንግዲህ እንግክርዳድ ተሰቅሞ በእሣት እንደሚቃጠል፥ በዓለም መጨረሻ እንዲህ ይሆናል። የሰው ልጅ መላእክቱን ይልካል፥ ከመንግሥቱም እንቅፋትን ሁሉ ዓመፃንም የሚያደርጉትን ይለቅማሉ፥ ወደ እቶን እሣትም ይጥሉአቸዋል፤ በዚያ ልቅሶና ጥርስ ማፋጨት ይሆናል። በዚያን ጊዜ ጻድቃን በአባታቸው መንግሥት እንደ ፀሐይ ያበራሉ። የሚሰማ ጆሮ ያለው ይስማ።»*

ኢየሱስ እንክርዳዶቹን የጠራቸው «የክፉ ልጆች» በማለት ነው። የእነርሱ በእርሻ ውስጥ *መገኘት* ድንገተኛ አይደለም። በእርሻው መካከል አስቦ የዘራቸው ዲያብሎስ ነው። በሌላ አነጋገር አስመሳዮችና ግብዞች በእውነተኞች ክርስቲያኖች መካከል *መገኘታቸው* የሰይጣን ጥበብ አንዱ አካል ነው። የቤተ ክርስቲያንን ምስክርነት ዋጋ ለማሳጣት የሚጠቀምበት አንዱ መንገድ ይህ ነው።

ኢየሱስ በዘመነ ፍጻሜ ለለሚደረገው ፍርድ ሲናገር መላዕክት በመጀመሪያ ሐሰተኛ ክርስቲያኖችን ከእውነተኞቹ በመለየት ልቅሶና ጥርስ ማፋጨት ወደ አለበት እሣት እንደሚጥሏቸው ተናግሯል። ይህ ከተደረገ በኋላ *«ጻድቃን በአባታቸው መንግሥት እንደ ፀሐይ ያበራሉ።»* በሌላ አነጋገር ሐሰተኞች ክርስቲያኖች በመጀመሪያ ተለይተው የእሣት ፍርድ ባለበት ቦታ ይጣላሉ። ከዚህ በኋላ አውነተኞቹ ክርስቲያኖች በትንሣኤ ክብራቸው ይገለጣሉ።

ወደ ባሕር የተጣለው ምሳሌም የያዘው ይኼንኑ ተመሳሳይ መገለጥ ነው። *«ደግሞ መንግሥተ ሰማያት ወደ ባሕር የተጣለች ከሁሉም ዓይነት የሰበሰበች መረብን ትመስላለች፤ በሞላችም ጊዜ ወደ ወደቡ አወጧት፥ ተቀምጠውም መልካሙን ሰቅመው በዕቃዎች ውስጥ አከማቹ ክፉውን ግን ወደ ውጭ ጣሉት። በዓሰም መጨረሻ እንዲሁ ይሆናል፤ መላዕክት መጥተው ኃጢአተኞችን ከጻድቃን መካከል ይለዩአቸዋል። ወደ እቶን እሣትም ይጥሏቸዋል፤ በዚያ ልቅሶና ጥርስ ማፋጨት ይሆናል።»* ማቴዎስ 13:47-50

በዚህ ወደ ባሕር የተጣለ መረብ ምሳሌ ውስጥ በዓለም ሁሉ የተሰበከው *የመንግሥት* ወንጌል በምሳሌ ተጠቅሷል። በመረቡ የተያዙት የተለያዩ ፍጡራን የሚወክሉት ለወንጌል ግብዣ አወንታዊ ምላሽ የሰጡትን ሁሉ ነው። እነዚህም ሕዝቦች መልካም ወይም ክፉ፥ ጻድቅ ወይም ኃጢአተኛ ሲሆኑ ይችላሉ።

በዘመን መጨረሻ መላእክት ኃጢአተኞችን ከጻድቃን በመለየት ወደ ቅጣት ሥፍራ ይጥሏቸዋል። ከዚህ በኋላ ነው መልካሞቹና ጻድቃኑ በረከቶቻቸውንና ሽልማቶቻቸውን ለዘለዓለም ከክርስቶስ የሚቀበሉት።

በዚህ መገለጥ ውስጥ በክርስቶስ ፍርድ ወንበር ፊት የሚቆሙት ለምን ኩነኔ እንደማይደርስባቸው ሌላ ምክንያት እናያለን። ይኸውም የእውነተኞቹ አማኞች ፍርድ ከመከናወኑ በፊት፥ ቀድሞውኑ መላዕክት አስመሳዮችንና ሐሰተኞች ክርስቲያኖችን በመለየት ወደ ፍርድ ሥፍራ ጥለዋቸዋል። ስለሆነም ሽልማታቸውን ለመቀበል በክርስቶስ ቅፍርድ ወንበር ፊት የሚቆሙት የነፍሳቸው ደህንነት ዘላለማዊ ዋስትና የተገባለትና ከልብ የሆነው እምነታቸውም በክርስቶስ ጽድቅ የተመሠረተ ጻድቃንና አማኞች ብቻ ናቸው።

የኃጥአንና የጻድቃን በዚህ መልኩ የመለየታቸው ጉዳይ በአዲስ ኪዳን ብቻ ሳይሆን በብሉይ ኪዳንም የተጠቀሰ ስለመሆኑ ለማስረጃ ያህል በመዝሙረ ዳዊት 1:4-5 ላይ የሠፈረውን በመጥቀስ እንመለከታለን፦ *«ክፉዎች እንዲህ አይደሉም፥ ነገር ግን ነፋስ ጠርጎ እንደሚወስደው ትቢያ ናቸው። ስለዚህ ክፉዎች በፍርድ ኃጢአተኞችም በጻድቃን ማኅበር አይቆሙም።»*

በዚህ ትንቢት ውስጥ ክፉዎች ከትቢያ ጋር ጻድቃን ደግሞ በምልከታ ከስንዴ ጋር ታነጻጽረዋለህ። ስንዴው ከመሰብሰቡ በፊት ገለባው ከላዩ ሊወገድለት ያስፈልጋል። እንደዚሁም ጻድቃን ወደ ዘላለማዊ ሽልማቱ ከመግባታቸው በፊት ኃጢአተኞች ከመካከላቸው ሊወጡና ወደ ፍርድ ሥፍራ ሊጣሉ ይገባል።

በዚህም ምክንያት መዝሙረኛው ክፉዎች እና ኃጢአተኞች በፍርድ በጻድቃን የፍርድ ሥፍራ (በክርስቶስ የፍርድ ወንበር ፊት) እንደማይቆሙና አንዲሁም ከእውነተኞች አማኞች ማኅበር ለዘላለም እንደማይገናኙ ይናገራል።

ይህንን ምዕራፍ በሚከተለው ሁኔታ እንደመድማለን እውነተኞችና ከልብ የሆነ እምነት ያላቸው አማኞች በክርስቶስ የፍርድ ወንበር ፊት ይቆማሉ። ከዚያ በፊት ግን መላእክት አስመሳዮችን እና ሐሰተኞች ክርስቲያኖችን ለቅመው ወደ እሳት ይጥሏቸዋል።

52

ሦስቱ የመጨረሻ ፍርዶች

በምዕራፍ 50 ላይ የእግዚአብሔር ዘላለማዊ ፍርዶች በሦስት ተከታታይ የፍርድ ሂደቶችን እንደሚከናወኑ አመልክተናል። የመጀመሪያው የፍርድ ሂደት ክርስቲያን አማኞችን በክርስቶስ የፍርድ ወንበር ፊት የሚቆሙበት ሲሆን ሁለተኛው በታላቁ መከራ ፍጻሜ ላይ የአሕዛብ መንግሥታት በክርስቶስ የክብር ዙፋን ፊት የሚቆሙበት ነው። ሦስተኛው በሺህ ዓመት መንግሥት ውስጥ የሞቱትና ፍርዳቸውም በነጩ ዙፋን ፊት የሚከናወንበት ነው።

ከእነዚህ ሦስት የፍርድ ሂደቶች ውስጥ የመጀመሪያውን ማለትም በክርስቶስ የፍርድ ወንበር ፊት የሚከናወነውን የክርስቲያኖች ፍርድ የተመለከትን ሲሆን አሁን ደግሞ በታላቁ መከራ ፍጻሜ ላይ ስለሚከናወነው የአሕዛብ መንግሥታት ፍርድ እናልፋለን።

ሆኖም ግን በመጀመሪ ወደዚህ የፍርድ ሂደት የሚመሩንን ዋና ዋና ሂደቶች ማጤን ያስፈልገናል። ይህም እግዚአብሔር በአሕዛብ መንግሥታት ላይ ለምን የተለየ ፍርድ እንደወሰነባቸው ለመረዳት ያስችለናል።

ጳውሎስ እግዚአብሔር የሰው ዘርን የሚለይባቸው ሦስት ምድቦችን ይጠቅሳል። *«. . . ለአይሁድም (ለእስራኤል)፥ ለግሪክም ሰዎች (ለአሕዛብ መንግሥታት) ለእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያንም (ክርስቲያኖች) ማሰናከያ እንሁኑ።»* 1ቆሮንቶስ 10:32

አይሁድ ለራሱ ዕቅድ ክሉሎች ሕዝቦች በእግዚአብሔር የተባበሩ የተለየ ሕዝብ ናቸው። ከእስራኤል በስተቀር የተቀሩት ሕዝቦች አሕዛብ ናቸው። የእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን ደግሞ በክርስቶስ አምነው ዳግሞ በተወለዱት እውነተኛ አማኞች ሁሉ የተመሠረተች ናት። እነዚህ ምዕመናን በእግዚአብሔር ዘንድ የሚታወቁት ዳመጀመሪያው ዘግነታቸው ወይም ማንነታቸው ማለትም አይሁድ ወይም አሕዛብ በመሆን ሳይሆን በክርስቶስ እንደ አዲስ ሕዝብ ነው።

አሁን እየተመለከትን ያለውን በክርስቶስ የክብር ዙፋን ፊት የሚከናወነው ፍርድ ለአሕዛብ ብቻ እንደሆነ መጽሐፍ ቅዱስ በግልጥ ያሳያል። ከተቀሩት ሁለት ምድቦች (ከአይሁድና ከእግዚአብሔር ቤተክርስቲያን) ውስጥ ማንም ሰው በዚህ ፍርድ አይቀርብም። አይሁድም ክርስቲያኖች አይቀርቡም። ይህ እውነታ ስለ ዘመን ፍጻሜ ከሚናገረው ከመጽሐፍ ቅዱስ አጠቃላይ መገለጥ ጋር ይስማማል።

ክርስቲያኖች በዚህ የፍርድ ወቅት አይቀርቡም ምክንያቱም እነርሱም በራሳቸው በክርስቶስ የፍርድ ወንበር ፊት በሚከናወነው ፍርድ ይቀርባሉና ነው። ከዚህ ቀደም ብሎም እስራኤል እንደ ሃገር በራሷ የተለየ የፍርድ ሂደት ታልፋለችና በዚህ ፍርድ ወቅት አይሁድም አይቀርቡም። ከዚህ የተለየ ፍርድ የሚያመልጡ አይሁድ ሁሉ ኢየሱስን እንደ አዳኝና መሲህ በማወቅ ከእግዚአብሔር ጋር እርቅ ያደርጋሉ።

በዚህ ወቅት እግዚአብሔር ከእስራኤል ጋር በሚያከናውነው ነገር ለአራት ሺህ ዓመት ያህል የዘለቀው ታሪካዊ የፍርድ ሂደት ይደመደማል። በአሕዛብ መንግሥታት ላይ የሚከናወነው ቀጣዩ ፍርድ ከታሪካዊ ወደ ዘላለማዊ ፍርድ የመሸጋገሪያ ምልክት ይሆናል።

የእስራኤል የመከራ ፍርድ

በበረከትና በፍርድ ውስጥ እግዚአብሔር ከሰው ዘር ጋር የሚገናኝበት ሁለት አጠቃላይ መመሪያዎችን መመልከት ይህን የእስራኤልን የተለየ ፍርድ ለመገንዘብ ይረዳሉ። እነዚህ መመሪያዎች እንደሚከተሉት ሊገለጡ ይችላሉ።

1. የበረከት መመሪያ፦ እግዚአብሔር አሕዛብን የሚባርከው በአይሁድ በኩል ሲሆን አይሁድን ግን በቀጥታ ይባርካል።

2. የፍርድ መመሪያ፦ እግዚአብሔር አይሁድን የሚቀጣው በአሕዛብ በኩል ሲሆን አሕዛብን ግን በቀጥታ ይቀጣል።

እነዚህ ሁለት መመሪያዎች እግዚአብሔር በዘመን ፍጻሜ ከሰው ዘር ጋር ወደሚያከናውናቸው ነገሮች ያመለክታሉ።

በታላቁ መክራ ፍጻሜ ላይ በመጀመሪያ አሕዛብን እንደ መሣሪያነት በመጠቀም እግዚአብሔር ለመጨረሻ ጊዜ እስራኤልን እንደ ሃገር ይቀጣታል ይፈርድባታል። ይህ የእስራኤል የመጨረሻ ፍርድ ሲጠቃለል እግዚአብሔር ራሱ በአሕዛብ ላይ ሊፈርድ ጣልቃ ይገባል። እስራኤል ወደገዛ መሬታቸው እንደ አገር ከተሰበሰቡ በኋላ እንደ ምን የመጨረሻው ፍርድ እንደሚሆንባቸው ገልጿል።

«እነሆ፥ የሕዝቤን የእስራኤልን የይሁዳን ምርኮ የምመልስበት ዘመን ይመጣልና ይላል፥ እግዚአብሔር ለአባቶቻቸውም ወደ ሰጠኋት ምድር እመልሳቸዋለሁ፥ እነርሱም ይገዙአታል። እግዚአብሔር ስለ እስራኤልና ስለ ይሁዳ የተናገረው ቃል ይህ ነው። እግዚአብሔር እንዲህ ይላልና፦ የሚያስፈራ ድምፅ ሰምተናል፥ የፍርሃት ነው እንጂ የሰላም አይደለም። ጠይቁ፥ ወንድ ይወለድ እንደሆነ ተመልከቱ፥ ስለምን ሰው ሁሉ እንደ ወላድ እጁን በወገቡ ላይ አድርጎ ፊቱም ሁሉ ወደ ጥቁረት ተለውጦ እየሁ? ወዮ! ያ ቀን ታላቅ ነውና፥ ነገር ግን ከእርሱ ይድናል። በዚያ ቀን እንዲህ ይሆናል ይላል የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር፥ ቀንበርን ከአንገትህ እሰብራለሁ፥ እስራትህንም እበጥሳለሁ፥ ከእንግዲህ ወዲህም ለሌላ ሕዝብ እትገዛም፥ ለእግዚአብሔር ለአምላካቸው ለማስነሳላቸው ለንጉሣቸው ለዳዊትም ይገዛሉ እንጂ ሌሎች አሕዛብ እንደገና አይገዙአቸውም።» ኤርምያስ 30:3-9

በኤርምያስ አስቀድሞ የተነገረው የሁኔታዎቹ ቅደም ተከተል፦

1. እግዚአብሔር እስራኤልን ወደገዛ አገራቸው ይመልሳቸዋል።
2. ታይቶ የማይታወቅ አደጋና መከራ በእስራኤል ላይ ይሆናል።
3. ጌታ ራሱ ጣልቃ በመግባት ከባአዳን አሕዛብ ጠላቶቿ እስራኤልን ያድናል።
4. በራሱ በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ንጉሥነት በዳዊት ዙፋን ላይ የእስራኤልን መንግሥት እንደገና ይመልሳል (ይቆማል)። ይህ ጊዜ የሺህ ዓመት መንግሥት ጊዜ ይሆናል።

ይህ በመጨረሻው ዘመን የአሕዛብ መሰብሰብና የጌታ በእስራኤል ጎን መቆም በዘካርያስ 12:3 ላይ ተጠቅሷል፦

«በዚያም ቀን ኢየሩሳሌምን ለአሕዛብ ሁሉ ከባድ ድንጋይ አደርጋታለሁ የሚሸከሙትም ሁሉ አድግ ይቆስላሉ። የምድርም አሕዛብ ሁሉ በላይዋ ላይ ይሰማቻሉ።»

እንደገናም በዘካርያስ 14:2-4 እንዲህ ይላል፦

«አሕዛብንም ሁሉ በኢየሩሳሌም ላይ ለሰልፍ እሰበስባለሁ፥ ከተማይቱም ትያዛለች፥ ቤቶችም ይበዘበዛሉ፥ ሴቶችም ይነወራሉ፥ የከተማይቱም አኩሌታ ለምርኮ ይወጣል፥ የቀረው ሕዝብ ግን ከከተማይቱ አይጠፋም። እግዚአብሔርም ይወጣል፥ በሰልፍም ቀን እንደተዋጋ ከእነዚያ አሕዛብ ጋር ይዋጋል። በዚያም ቀን እግሮቹ በኢየሩሳሌም ትይዩ በምሥራቅ በኩል ባለው በደብረ ዘይት ላይ ይቆማሉ፥ ደብረ ዘይትም በመካከል ወደ ምሥራቅና ወደ ምዕራብ ይሰነጠቃል፥ እጅግም ታላቅ ሸለቆ ይሆናል፥ የተራራውም እኩሌታ ወደ ሰሜን እኩሌታውም ወደ ደቡብ ይርቃል።»

በዚህ ላይም እንደገና ይህ ዘመን የሚደመደመው የአሕዛብ መንግሥታት በእስራኤልና በኢየሩሳሌም ላይ በሚሰነዘሩት ጥቃትና ጌታ ራሱ እስራኤልን ለማዳን ጣልቃ በመግባት እንደሆነ እያናለን። ይህ የጌታ እስራኤልን የማዳን አርምጃ የመጨረሻው ደረጃ የሚደርሰው መጀመሪያ ወዳረገበት ወደ ደብረ ዘይት አካባቢ ሲመለስ ነው።

በዚህ የመጨረሻው ብሔራዊ የመከራና የፍዳ ዘመን የአመፅ ርዝራዦች ሁሉ ከእስራኤል ይጸዳሉ። በዚህ ውስጥ ተፈትነው የወጡ እስራኤላውያን ከአምላካቸው ጋር በንስሐና ራስን ዝቅ በማድረግ ለመታረቅ ዝግጁ ይሆናሉ።

ይህ የመጨረሻው እስራኤልን የማጽዳት ሁኔታ እንደገና ወደ ገዛ ምድራቸው መሰብሰባቸውን በተናገረበት በሕዝቅኤል 20:37-38 ተገልጧል፦ *«ከበትርም በታች አሳልፋችኋለሁ ወደ ቃል ኪዳንም አስራት አገባችኋለሁ፤ ከእናንተም ዘንድ አመጸኞችንና የበደሉኝን እለያለሁ ከኖሩባትም ምድር አወጣቸዋለሁ፥ ወደ እስራኤል ምድር ግን አይገቡም አኔም እግዚአብሔር እንደሆንኩ ታውቃላችሁ።»*

እዚህ ላይ «ከበትርም በታች አሳልፋችኋለሁ» ተብሎ የተጠቀሰው ሐረግ የሚያመለክተው አረኛ በጎቹን ወደ መንጋው ከመቀላቀሉ በፊት እያንዳንዱን በግ የሚመረምርበትን ሂደት ነው። የዚህም ውጤት አመጸኞች ከእስራኤል ይወገዳሉ። የቀሩት ግን በኢየሱስ ክርስቶስ በሆነ አዲስ ኪዳን ከጌታ ጋር ወደ አዲስ ግንኙነት ይመጣሉ።

ከአሕዛብ መንግሥታት እስራኤልን ለማዳን የጌታ ጣልቃ መግባትና ከእስራኤል ጋር ስለሚያደርገው የመጨረሻ አርቅ በተጨማሪ በዘካርያስ 12:9-10 እንዲህ ተገልጧል፦

«በዚያም ቀን በኢየሩሳሌም ላይ የሚመጡትን አሕዛብ ሁሉ ለማጥፋት እጋደላለሁ። በዳዊትም ቤት ላይ የሞገስንና የልመናን መንፈስ አፈሳለሁ። ወደ እርሱም ወደ ወጉት ይመለከታሉ፥ ለውም ለእንድያ ልጁ እንደሚያለቅስ ያለቅሱለታል፥ ለውም ለበኩር ልጁ እንደሚያዝን በመራራት ሐዘን ያዝኑለታል።»

በዚህ ቦታ በእንደኛ መደብ (እኔ በማለት) የሚናገረው ጌታ ራሱ ነው። «ወደ እርሱም ወደ ወጉት ይመለከታሉ» የሚለው ትንቢትም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስለ ክርስቶስ ስቅለትና መገፋት ከሚናገሩትና አጅግ ግልጥ ከሆኑት ትንቢቶች አንዱ ነው። ሆኖም ግን በመጨረሻ እስራኤላውያን ይህን አጅግ አስደንጋጭ የሆነ ስህተት በመገንዘብ በታላቅ ለቅሶና በንስሐ ከገፉት ከመሲሐቸው (ከክርስቶስ) ጋር ይታረቃሉ።

ይህን እስራኤል ከእግዚአብሔር ጋር የምታደርገውን የመጨረሻ እርቅ በአዲስ ኪዳን ውስጥ ጳውሎስ እንደሚከተለው ገልጦታል፦ *«እንደዚሁም እስራኤል ሁሉ ይድናል፤ እንዲህ ተብሎ እንደተጻፈ፦ መድኃኒት ከጽዮን ይወጣል ኀጢአተኛነትን ያስወግዳል።»* ሮሜ 11:26

እስራኤላውያን በታላቁ መከራ እሳት ውስጥ ካለፉና በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ከእግዚአብሔር ጋር እንደገና ከታረቁ በኋላ በእነርሱ ላይ ሌላ ፍርድ ለእግዚአብሔር አያስፈልገውም። ከዚህ በኋላ ማለትም ክርስቶስ ምድራዊ መንግሥቱን ሲያቋቁምና በክብሩ ዙፋን ላይ ሲቀመጥ በታላቁ መከራ ማብቂያ ላይ በምድር በሕይወት በቀሩት የአሕዛብ መንግሥታት ላይ ይፈርድባቸዋል።

የአሕዛብ መንግሥታት ለፍርድ መቅረብ

በአሕዛብ መንግሥታት ላይ ስለሚሆነው ፍርድ ኢየሱስ በትክክል የሚያሳይ ትምህርት በማቴዎስ 25:31-46 ሰጥቷል። ይህ ምንባብ ምሳሌያዊ አነጋገር እንደሆነ ምንም አያመለክትም። ይልቁንም እረኛው በመንጋዎቹ የሚያከናውነውን በአንጻራዊነት በማስቀመጥ በቀጥታ የተነገረ ትንቢታዊ ትምህርት ነው። የመከፈቻውን ሁኔታ እንመልከት፦

«የሰው ልጅ በክብሩ በሚመጣበት ጊዜ ከእርሱም ጋር ቅዱሳን መላዕክቱ ሁሉ፥ በዚያን ጊዜ በክብሩ ዙፋን ይቀመጣሉ፤ አሕዛብም ሁሉ በፊቱ ይሰበሰባሉ፥ እረኛም በጎቹን ከፍየሎቹ እንደሚለይ እርስ በእርሳቸው ይለያቸዋል። በጎቹን በቀኙ ፍየሎቹንም በግራ ያቆማቸዋል።» ማቴዎስ 25:31-33

የዚህ ፍርድ ዓላማ በጎችን (እግዚአብሔር የተቀበላቸውን) ፍየሎች (እግዚአብሔር ካልተቀበላቸው) ለመለየት ነው። በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ መግባት የተቀበሉት በጎቹ የክርስቶስ የሺህ ዓመት መንግሥት

ተዘጋጅቶላቸዋል። ፍየሎቹ ግን ለሰይጣንና ለመልእክተኞቹ ወደ ተዘጋጀው ወደ ዘላለም እሳት እንዲጣሉ ፍርድ ይፈረድባቸዋል።

እነዚህ አሕዛብ የሚላኩት ወደ ሲያል ሳይሆን አመጸኞች ሁሉ ወደሚቀጡበትና የመጨረሻው የቅጣት ቦታ ወደ ሆነው ወደ እሳት ባሕር ነው። ከዚህ ቀደም ብሎ አውሬው ሐሰተኛው ክርስቶስና ሐሰተኛው ነቢይ ይጣላሉ።

በጎችን ከፍየሎች መለየትና ፍርዱ የተመረኮዘው የኢየሱስ ወንድሞች ማለትም የአይሁድን ሕዝብ በመቀበል ላይ ነው።

ብዙዎች የመጽሐፍ ቅዱስ ምእመናን በግልጽ እንደሚያሳዩት በዚህ ዘመን መጨረሻ ላይ በአይሁድና በእስራኤል ላይ ዓለም አቀፍ ጥላቻ ይሆናል። በእስራኤል መንግሥት ላይ የአሕዛብ መንግሥታት ጥቃት የሚሰነዝሩ መሆናቸው ብቻ ሳይሆን በሌሎች አገራት የሚኖሩ አይሁዶች የተሰያዩ ስደቶች ይደርሱባቸዋል። በዚህ ሁሉ መካከል ግን፥ በግለሰብ ደረጃ ወይም በሃገር ደረጃ ከእስራኤል ጋር የሚወግኑ ይኖራሉ። እነዚህ አገሮች ወይም ግለሰቦች አይሁድን ለመታደግና መከራቸውን ለመቀነስ የተቻላቸውን ያህል ይሞክራሉ። ይህም ተግባራቸው ከፍርድ እንዲድኑና በምድር ላይ በምትቆመው የክርስቶስ መንግሥት ውስጥ እንዲገቡ ያደርጋቸዋል። በመጨረሻው ዘመን ለእግዚአብሔር ፍርድ አሕዛብ እንደሚሰበሰቡ በተመሳሳይ ሁኔታ ኢዩኤል ተናግሯል፦

«እነሆም፥ በዚያ ወራትና በዚያ ዘመን፥ የይሁዳንና የኢየሩሳሌምን ምርኮ በምመልስበት ጊዜ፥ አሕዛብን ሁሉ ሰብስቤ ወደ ኢዮሣፍጥ ሸለቆ አወርዳቸዋለሁ፤ በዚያም ስለ ሕዝቤና ስለ ርስቴ ስለ እስራኤል በአሕዛብ መካከል የበተኗቸውን ምድሬንም የተካፈሉአትን እፈርድባቸዋለሁ።» ኢዩኤል 3፡1-2

እግዚአብሔር እንዳወጀው በመጀመሪያ የኢየሩሳሌምና የይሁዳን ምርኮኞች ማለትም የተበተኑትን የአይሁድን ሕዝብ ወደ ገዛ ምድራቸው እንደገና ይሰበስባቸዋል። ከዚህ በኋላ የአሕዛብን መንግሥታት በመለብለብ ፍርድን በላያቸው ላይ ያመጣባቸዋል።

የፍርዱ መሠረት በማቴዎስ 25፡ ላይ ኢየሱስ እንደተናገረው ነው። ጌታ ከመንግሥታቱ ጋር ወደ ፍርድ የሚገባው «ስለ ሕዝቤና ስለ ርስቴ ስለ እስራኤል» ነው ይላል። በታሪክ ውስጥ ፀረ ሴማዊነት በከፍተኛ ደረጃ በተስፋፋበት በእሁኑ ወቅት የአይሁድን ሕዝብ በሚመለከቱበት ሁኔታ መሠረት እንደሚፈረድባቸው መንግሥታትን ማስጠንቀቁ አስፈላጊ ነው።

የበጎችና የፍየሎች መለየት ከተከናወነ በኋላ የአሕዛብ መንግሥታት ፍርድ ይጠቃለላል። በዚህ ወቅት ወደ ክርስቶስ የሺህ ዓመት መንግሥት ለመግባት የተዘጋጁ ሁሉ በሚያነጻው በእግዚአብሔር ፍርድ ውስጥ ያልፋሉ።

መጀመሪያ አሰራኤል በታላቁ መከራ እሳት ውስጥ ትነጻለች። ከዚህ በኋላ በታላቁ መከራ ዓጻሜ ላይ በራሱ በክርስቶስ ቀጥተኛ ፍርድ እሕዛብ ይነጻሉ።

ከነዚህ የማንጻት ፍርዶች በኋላ ክርስቶስ እንደ ንጉሥ በመላው ዓለም ላይ በመንገሥ የአንድ ሺህ የሠላምና የብልጽግና ዓመት ይሆናል።

በሺህ ዓመቱ መንግሥት ማብቂያ ላይ ሠይጣን የአሕዛብ መንግሥታትን በክርስቶስና በመንግሥቱ ላይ በተቃውሞ በማነሳሳት የመጨረሻ መከራ ያደርጋል። ነገር ግን ይህ አመጽ በእግዚአብሔር ቀጥተኛ እጅ ፍጻሜ ያገኛሉ።

በዚህ ጊዜ ሠይጣን ራሱ ለዘላለም ከምድር ላይ ይወገዳል። ቀድሞ ከተጣሉት ከሐሰተኛው ክርስቶስና ከሐሰተኛው ነቢይ ጋር እንዲሆን ወደ እሳት ባሕር ይጣላል።

በዚህ የሠይጣን የመጨረሻ አመፅ ሽንፈት በምድር ላይ የሚኖሩ አመፀኞች ሁሉ ይወገዳሉ። ከዚህ በኋላ የሚቀረው ባሰፋት በመሩት የሞቱትን ሁሉ ሰፍሮ ማቅረብ ነው። ለዚህ ዓላማ ከዚህ በፊት ትንሣኤ ያላገኙት ሙታን በሙሉ ለፍርድ ይጠራሉ። በዚህ ሁኔታ ሦስተኛው የእግዚአብሔር ዘላለማዊ ፍርድ ይከናወናል።

ታላቁ ነጭ ዙፋን

«ታላቁና ነጭ ዙፋንን በአርሱም ላይ የተቀመጠውን አየሁ፥ ምድርና ሰማይም ከፊቱ ሸሹ ሥፍራም አልተገኘላቸውም። ሙታንንም ታናናሾችንና ታላላቆቹን ብዙውን ፊት ቆመው አየሁ፥ መጻሕፍትም ተከፈቱ፤ ሌላ መጽሐፍም ተከፈተ። እርሱም የሕይወት መጽሐፍ ነው፤ ሙታንም በመጻሕፍት ተፅፎ እንደነበር እንደ ሥራቸው መጠን ተከፈሉ። ባሕርም በእርሱ ውስጥ ያሉትን ሙታን ሰጠ። ሞትና ሲኦልም በእነርሱ ዘንድ ያሉትን ሙታን ሰጡ፥ እያንዳንዱም እንደ ሥራው መጠን ተከፈለ። ሞትና ሲኦልም በእሳት ባህር ውስጥ ተጣሉ። ይህም የእሳት ባሕር ሁለተኛው ሞት ነው። በሕይወትም መጽሐፍ ተጽፎ ያልተገኘው ማንኛውም በእሳት ባሕር ውስጥ ተጣለ።» (ራዕይ 20፡11-15)

በዚህ ቦታ ላይ በልቡል እግዚአብሔር ሥልጣንና ቅድስና ላይ የተነሱ አመጸኞችና ኃጢአቶች ሁሉ ወደ ዘላለማዊ እሳት ባሕር በመጣል ዓጻሜ ያገኛሉ። ከዚህ የመጨረሻ ፍርድ የሚያመልጡት ስማቸው በሕይወት መጽሐፍ የተጻፉ ብቻ ናቸው። በዚህ መጽሐፍ ላይ ስማቸው የተጻፉት በምድር በነበሩበት የሕይወት ዘመናቸው ራሳቸውን በእምነት ለእግዚአብሔር ምህረትና ጸጋ ያቀረቡ ናቸው። እነዚህም በተለያዩ ምድብ ይከፈላሉ። በክርስቶስ የጌዜነት መሥዋዕት ላይ እምነታቸውን ያደረጉ ሁሉ በሺህ ዓመቱ መንግሥት መግቢያ

ላይ ተነስተዋል። ለእነርሱ በሚገባቸው የክርስቶስ ፍርድ ወንበር ፊት ለኩነኔ ሳይሆን ሽልማታቸውን ለመቀበል አልፈዋል።

በታላቁ የነጭ ዙፋን ፊት የሚቆሙት አብዛኛዎቹ የእግዚአብሔርን ምህረት ያልተቀበሉና ወደ እሳት ባሕር ለመጣል የሚፈረድባቸው ይመስላሉ። ሆኖም ግን በምዕራፍ 46 ላይ እንደተመለከተው በእርግጥም በትንሹ በሁለት ምድብ የሚከፈሉና ክነጩ ዙፋን ፍርድ በማምለጥ ወደ ዘላለም ሕይወት የሚገቡ ሕዝቦች አሉ።

የመጀመሪያው ምድብ የደቡብ ንግሥት (ንግሥተ ሳባ)ና የነነዌ ሰዎችን የመሰሉ እግዚአብሔር ራሱ በተወሰነ መንገድ ለገለጠላቸው ምህረት ራሳቸውን ያቀረቡ ሰዎች ናቸው። በታሪክ ውስጥ ምን ያህል ሰዎች ይህን ዓይነቱን እድል እንዳገኙ መጽሐፍ ቅዱስ አያመለክትም። ሁለተኛው ምድብ በሺህ ዓመቱ መንግሥት ወቅት በእምነት የሞቱት ናቸው።

ከታላቁ ነጭ ዙፋን እግዚአብሔር የምህረት እጁን የሚዘረጋላቸው ሌሎች ወገኖች ይኖራሉ ብለን መገመት እንችላለን? መልሱ ሁሉን እዋቂ በሆነው እግዚአብሔር ዘንድ ብቻ የሚተው ነው። በውስኑ እውቀታችንና ጠባብ በሆነው አመለካከታችን መገመቱ ሞኝነት ነው። ይልቁንም በአብርሃም የተገለጠውን ዝንባሌ ገንዘብ እናድርግ።

«የምድር ሁሉ ፈራጅ በቅን ፍርድ አይፈርድምን?» ዘፍጥረት 18:25።

የእግዚአብሔርን ወሰን የሌለው ምህረት የቀመሱ እግዚአብሔር ምህረቱን ከሚገባቸው ሰዎች እንደማይከለክል አስረግጠው ያምናሉ። ሆኖም ግን የእግዚአብሔርን ፍርዶች ሁሉ አጠቃለን እናውቃለን ብለን እንዳናስብ እንጠንቀቅ። በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ያሉት ጥናቶች የዳሰሱት በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ የተዘገቡትን ነው። ከእኛ እውቀትና ችሎታ በላይ የሆኑ ብዙ ነገሮች አሉ። በመጨረሻ ልንል የምንችለው ጳውሎስ በአድናቆትና በፍርሃት የገለጠውን ብቻ ነው።

«የእግዚአብሔር ባለጠግነትና ጥበብ እውቀቱም እንዴት ጥልቅ ነው! ፍርዱ እንዴት የማይመረመር ነው፥ ለመንገዱም ፍለጋ የለውም» ሮሜ 11:33።

ይህ የዚህ መጽሐፍ ዋና መልዕክት የሆኑትን ስድስቱን የክርስትና እምነት መሠረቶች ለማጠቃለል ተገቢ መደምደሚያ ነው።

በዚህ ጥናት መሠረት ማንኛውም ክርስቲያን በአጽንኦት ሊመሠረትባቸው የሚችልበትን የክርስትና አስተምህሮ መሠረትን ጥለናል። በዚህ መሠረት ላይ በዕብራውያን 6:1 ላይ በተገለጸው ምክር መታዘዝ እንችላለን።

«ወደ ፍጻሜው እንሂድ» በዚህ መሠረት ላይ ሕይወታችን በክርስትና አስተምህሮና ሕይወት ላይ እስኪታነጽ ድረስ እንገንባ። መሠረቱን እንዴት እንደምንጥል ያሳየን ያው የእግዚአብሔር ቃል እንዴት ወደ ፍጽምና እንደምንደርስም ያመለክተናል።

ስለሆነም ከእኔ ጋር ይህን ጥናት ለተከታተሉት ሁሉ ከሐዋርያው ጳውሎስ የተወሰደውን የመጨረሻ የምክር ቃል አቀርብላችኋለሁ።

«አሁንም ለእግዚአብሔርና ያነጻችሁ ዘንድ በቅዱሳንም ሁሉ መካከል ርስትን ይሰጣችሁ ዘንድ ለሚችል ለጸጋው ቃል አደራ ሰጥቻችኋለሁ።»